# ከፃዕረ–ሞት ትንቅንቅ

## ሲድኒ ሼልደን

From the Library of
ፍሥሐ አጥላው ወልደ ዮሃንስ
FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANNES

ሚሞሪስ ኦፍ ሚድ ናይት

ትርጉም
ሳሙኤል ማሞ ገ/ዮሐንስ

**<u>መታሰቢያነቷ</u>**

- ለኪሮስ ሳሙኤልና
- ለተክለማርያም ሳሙኤል ነው ።

- የሐሳብ ትብብር ያደረጉልኝን የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህር አቦነህ አሸግሬ (M.A )

እና

- ሥራውን ለመጀመር ያበቁኝን አቶ ልዑል አባተን ከልብ አመሰግናለሁ ።

<u>የሽፋን ሥዕል</u>
ብርሃነ ሕይወት ጌታቸው

# የተርጓሚው ማስታወሻ

"ለንተ በሲድኒ ሼልደን ጽሑፍ ተለክፈሃል መሰለኝ" ለለኝ ለንድ ወዳጄ ይህንን መጽሐፍ መጀመሬን ገና እንደተመለከተ ። ይህንን መጽሐፍ ለግኘቼ ሥራውን የጀመርኩት ለንድ ከበድ ያለና ረዘም ያለ ጊዜ የሚጠይቅ የጽሑፍ ሥራ ለቋርጬ ነው ። ይህንን ያደረግኩት ለስተያየት ሰጪዬ እንዳለው በሲድኒ ሼልደን ጽሑፎች ተለክፌ ለይደለም ። ይህኛውም ትርጉሚ በሲድኒ ሼልደን ሥራ ላይ ያተኮረው የትርከት ድር ካህኑ ሲድኒ ሼልደን በትርከት ክሽናው የለንባቢን ስሜት ገዝተው ድርሰቶቻቸው ከሚነበቡላቸው በወንጀል ፡ በወሲብና በገንዘብ ውጣ ውረድ የሚፈጠርን የሰውን ልጅ ትንቅንቅ ዓቢይ ጉዳይ በማድረግ ከሚጽፉ ዘመናዊ ደራስያን መካከል ለንዱ በመሆኑ ብቻ ነው። በሌላ በኩል ገና በዳደነት ላይ ለሚገኘው የለገራችን ሥነ ጽሑፍ የዚህና መሰል ዘመናዊ ደራሲያን ሥራዎች ወደለማርኛ ተመልሶ መቅረብ የሥነ ጽሑፍ ቴክኒክንም በማስተማር ረገድ መጠነኛ ለስተዋጽኦ ይኖራቸዋል ብዬ ሰለምንገምት ትኩረቴ በዚህ ለቀጣጫ ላይ ሊሆን ችሏል ።

ወደተነሳሁበት ፍሬ ነገር ልመለስና በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የቀናውን ገፀ ባሕርይ ሥፍራ የያዘችዋ ወጣት ሴት ከየት እንደመጣችና እንዴትስ ወዳለችበት ሥፍራ እንደተወሰደች ሳታውቀው ነበር ታሪኳ የሚጀምረው ። ማንነቷን ለማወቅ ከምታደርገው ጥረት ባሻገር ለንድ የሆነ ነገር ያስጨንቃታል፣ ያባንናታል ፡ ሰላም ይነሳታል ፡ ልትገደል መሆኗን ይገልጽላታል ። ይህ በሀሳቧ የተፈጠረው ለስጨናቂ ነገር ማንነቷን እስካወቀችበት ጊዜ ድረስ በሕልሟና በዓይነ ኅሊናዋ እየመጣ ይተናነቃታል ።

ወደ ታሪኩ ገባ ብዬ ለንዷን ለንቀጽ ላቀርብላችሁ ፦

"....ካተሪን ለሌክሳንደር ድሮ የሰማቻቸው ድምፆች እንደገና ከጆሮዋ ውስጥ ገቡ ። ሆኖም የተምታቱና የተቆራረጡ ስለነበሩ ግራ ያጋቧታል ። ..... ድምፆቹ የሚቆሙ ለይደሉም ። ያስጨንቃሉ ፡ ያሰቃያሉ ። ....." እነኚህ ሐረጎች ከላይ የጠቀስኩትን ለባባል ያጠናክራሉ ።

ደራሲው ሲድኒ ሼልደን ለጽሑፉ "ሚሞሪስ ኦፍ ሚድ ናይት" የሚል ርዕስ የሰጠው ቢሆንም ይህንን ርዕስ እንዳለ "የሌቱ ትውስታ" ወይም "የውድቀት ትዝታ" ብዬ ለማቅረብ አልፈለግኩም ።

ከታሪኩ በአንደኛው ክፍል ካተሪን "ሊገድለኝ እኮ ነበር ...." ስትል በተናገረችው አባባል ዙሪያ አብዛኛው የትርክት ድሩ ሲውጠነጠን መገኘቱን የተረዳሁ መሰለኝ ። ይህ በሕልሟም ይሁን በዓይነ ኅሊናዋ ከፊቷ ተደቅኖ የሚያስፈራራትን ነገር በበኩሌ ጻዕረ ሞት ልለው ፈለግኩ ። ያሰቃያትና ያስጨነቃትም እርሱ ነበርና ከማይታወቅ ገዳይ ጋር የተደረገውን ትግል ይበልጥ ለማንፀባረቅና ከአገራችን አንባቢያን ግንዛቤ አኳያ የመጽሐፉን ርዕስ "ከጻዕረ-ሞት ትንቅንቅ" ልል መረጥኩ ። ያ በአሳቢ ሲያስጨንቃት የነበረው ገዳይ በወቅቱ ይከሰትና ይተናነቃታል ። አሳቡስ ይሳካለታል ወይስ በምኞት ይቀራል፣ መልሱን እኔ ከወዲሁ ከምሰጥ የተወደዳችሁ አንባቢያን ከመጽሐፉ ብታገኙ የሚሻል መስሎኝ ከመናገር ተቆጥቢያለሁ ።

ተርጓሚው

ነሐሴ ፲፱፻፹፫



# መነሻ

## ኩውሉን—ሜይ 1949

"በድንገት የደረሰ አደጋ መምሰል አለበት ። እንዲህ ለማድረግ ይከብድሃል ?"

ጥያቄውን እንደሰደብ ቆጠረና ደሙ ፈላ ። መንገደኛ እንጂ በመስኩ የተካነ ሰው እንዲህ ዓይነት ጥያቄ አይጠየቅም ። በአሽሙር እንዲህ ብሎ ሊመልስለት ነበር ፦— 'የሚከብደኝ አይመስለኝም ፤ ከረጅም የፎቅ ደረጃ ላይ ወድቃ አንገቷን የተቀጨች ለማስመሰል እችላለሁ ፤ ማርሴሎስ ባለው ደናሽ አማካይነት ። ወይንም ሰክራ ፣ በገላ መታጠቢያ ገንዳዋ ውስጥ ሰጥማ እንደሞተች ለማድረግም አይሳነኝም ፤ ግስታድ ባለችው ወራሿ አማካይነት ። አሊያም ሄሮይን ከመጠን በላይ ወስዳ እንደሞተችም ለማስመሰል ይቻላል ። የተቀነባበሩላት ዘዴዎች እነኚህ ሲሆኑ ሲጋራዋን ሳታጠፋ እንቅልፍ እንደወሰዳትም ለማስመሰል አያቅተኝም ።' ፓሪስ ውስጥ በኤል ሆቴል ያለውን ሲዊድናዊውን የመረጃ ሰው አስታወሰ ። 'ከቤት ውጭ ቢሆን አይሻልም ? በመኪና ወይንም በአሮፕላን አደጋ እንድትሞት ፣ አልፎም በባሕር ውስጥ እንድትሰጥም ለማድረግም እችላለሁ ።' ሆኖም ግን ከፊትለፊቱ የተቀመጠውን ሰው በመፍራቱ አሽሙሩን ይፋ አውጥቶ ሊናገር አልቻለም ። የዚህን ሰው ብዙ አስደንጋጭ ታሪኮች ሰምቷል ። የሰማቸውን ሊያምን የቻለባቸው በርካታ ምክንያቶችም ነበሩት ።

ስለዚህ "አዎ ጌታዬ ማንም ሊደርስበት የማይችል ድንገተኛ አደጋ ላቀናብር እችላለሁ ።" ብቻ ነበር ያለው ። እሱን ራሱን ይህን ምስጢር የማወቁ ጉዳይ አሳስቦታል። ፀጥታ ሰፈነ ።

እራሳቸውን ከአረመኔያውያን እንግሊዞች ለመከላከል ሲሉ ቻይናውያን በ1840 ከገነቡት የኩውሉን የግንብ ከተማ ሕንጻ ሁለተኛ ፎቅ ላይ ነበሩ ። ግንቡ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ፍርስርሱ ወጥቷል ። አገሬው ያልሆኑ ሰዎች የሚደርሱበት ሥፍራ አይደለም ። ሰው የሚያርዱ፣ በአደንዛዥ ዕፅ ሱስ የተበከሉና፣ በጉልበት ሴት የሚዳፈሩ የተደራጁ ወንጀለኞች በየስርቻው በቂ ብርሃን በሌለው ጠባቡ የኩሪኮንች መንገድና የግምቡ መውጪያና መውረጃ ላይ ይተረማመሳሉ ። የአገር ጎብኚዎች ወደዚህ ሥፍራ እንዳይሄዱ ማስጠንቀቂያ ይሰጣቸዋል። ፖሊሶች እንኳ ከፊትለፊቱ ካለው ከቱንግ ታው ሱዊን ጎዳና አያልፉም ። የግንብ ከተማዋ ነዋሪዎች የተለያዩ ቋንቋዎች ፣ የሸክላ ፣ የጎርናና የሰላላ ድምፅ ምስቅልቅል ፤ ከመስኮቱ በኩል እየገባ ከጆሮው ይዘልቃል ።

ሰውዬው ተጠራጣሪ ዓይኖቹን በእርጋታ ተከሎበት ያጠናዋል። በመጨረሻም "መልካም እንግዲህ ፤ የዘዴውን ጉዳይ ላንተ እተዋለሁ ።" አለ ።

"እሺ ጌታዬ ። ለመሆኑ ኢላማችን እዚሁ ኩውሉን ነው ያለችው ?"

"ለንደን ። ካተሪን ትባላለች ። ካተሪን አሌክሳንደር ።"

አንድ ሊሞዚን መኪና ሁለት ጠባቂዎችን በያዘች ሌላ መኪና ታጅባ ፂም ሻ ፁይ ሰፈር ካለው ላስካር ሮው ሕንፃ ላይ ከሚገኘው ብሉ ሀውስ ሰውዬውን አደረሰች ። በብሉ ሀውስ የሚስተናገዱት ልዩ እንግዶች ብቻ ናቸው ። የመንግሥታት መሪዎች ፣ የፊልም ኮከብ ተዋንያንና የኮርፖሬሽን ፕሬዚዳንቶች ወደዚህ ሥፍራ ተመላልሰዋል ። አስተዳደሩ በአሠራሩ ላይ በሚወስደው ጥንቃቄና በምሥጢራዊነቱ ይኩራበታል ። ከሃያ ዓመት በፊት እዚህ ትሠራ የነበረች ወጣት ስለገበያ ደንበኞቿ ለጋዜጠኞች መግለጫ ሰጥታ በማግሥቱ ምላሷ ተቆርጦ ሬሳዋ በአበርዲን ወደብ ዳር ተገኝቷል ። በብሉ ሀውስ ማንኛውም ነገር ለሽያጭ ይቀርባል ። የአሥረኛው ክፍለ ዘመን የሌሺንፓ ጥበብ ከዚህ ሥፍራ በስተቀር በሌላ ቦታ አይታወቅም ። ብሉ ሀውስ ለተከለከለ ደስታ ማግኛ የታለመ ሥፍራ ነው ።

በአሁኑ ወቅት ሰውዬው መንትያ እህትማማቾች እንዲቀርቡለት አዟል ። አንዷን ከሌላዋ ለመለየት በፍጹም አይቻልም ። ሁለቱም ሰውነታቸው ያማረ ቆንጆጆች ሲሆኑ እንቢታ የሚባል ነገር አያውቁም። ባለፈው ጊዜ መጥቶ በነበረበት ወቅት ያጋጠመውን ሁሉ አስታወሰ ።



መቀመጫ የሌለው ኩርሲ ወንበር ፣ ለስላሳው የምላሳቸውና የጣቶቻቸው ዳሰሳ ፣ ሞልቶ ተርፎ ወለሉን ያጥለቀለቀው የገላ መታጠቢያው ገንዳ ውሃ ሙቀትና በትኩስ አፋቸው ገላውን ለመዳሰስ የነበራቸው እሽቅድምድም ሁሉ ትዝ አለው ። የፍትወት ሥጋ መቀስቀሻ ምልክቱ በተጠንቀቅ ሆነ ።

"መጥተናል ጌታዬ"

ከሦስት ሰዓት በኋላ ስሜቱን አርክቶ ዝግጅቱን አጠናቀቀና ወደሞዲ ጎዳና እንዲወስደው ሊሞዚኑን መኪና አዘዘ ። በሊሞዚኑ መስኮት በኩል የማታንቀላፋውን ከተማ አሸብራቂ መብራቶች አየ ። ቻይናውያኑ ጉዎ—ላንግ—ዘጠኝ ድራጎኖች ብለው ሰይመዋቸዋል ። እና ከከተማዋ በላይ ካሉት ተራሮች ላይ አድፍጠው ደካሞችንና የተዘናጉትን ወደታች ወርደው የሚያወድሙ ድራጎኖች መስለው በሕሊናው ተሳሉ ። እሱ ግን ደካማም የተዘናጋም አልነበረም ።

ሞዲ ጎዳና ላይ ደረሱ ። ቀለሙ የለቀቀ ጥንታዊያን ሩቅ ምሥራቅ ካባና ቀሚስ ለብሶ ነጭ ፂሙን እንዠርጎ በድሮ መጻሕፍት ውስጥ ያለ ሥዕል የሚመስለው የቶይስት ቄስ ይጠባበቀው ነበር ።

"ጆው ሳን ።"

"ጆው ሳን ።"

"ጌይ ዱ ቺን ?"

"ያት—ቺን ።"

"ጆው ።"

ቄሱ ዓይኖቹን ጨፍኖ በልቡ ፀሎት አደረሰና መፅሊያ የልምጭ ጉራጆችን በውስጡ የያዘውን የእንጨት ኩባያ ቺም ነቀነቀ ። አንዱ ጉራጅ መሬት ሲወድቅ መነቅነቁን አቆመ ። ፀጥታ ነገሠ ። ቶይስቱ ቄስ ወደሰንጠረዥ ዞሮ ካየ በኋላ ወደእንግዳው ተመለከተ ። በተሰባበረ እንግሊዝኛ "ከክፉ ባላንጣዎችህ ትላቀቃለህ ይሉሃል አማልክቶቼ" አለው ።

ሰውዬው በሰማው ተደስቷል ። ይሁንና ብስለቱ የቺምን ጥበብ እንደ አጉል እምነት ከመቁጠር አላገደውም ። ብልሀነቱ የሰማውን ችላ እንዲለው አድርጎታል ። ከዚህም ባሻገር ጥሩ ምልክት ይታያል ። ዛሬ የቅዱስ አጊዮስ ኩንስታንቲኖስ በዓል ነው ። የልደት ቀኑ ።

"አማልክቶች በፋንግ ሹይ ፣ ባርከውሃል ።"

"ዱ ጂህ ።"

"ሁ ዋህ ።"

ከአምስት ደቂቃ በኋላ ወደአቴንስ ሊመልሰው ከሆንግ ኰንግ አውሮፕላን ማቢያ ከሚጠብቀው የግል አውሮፕላኑ ለመሳፈር ከሊሞሲን መኪናው ገብቶ ወደ ካይ ቴክ ነጐደ ።



# ምዕራፍ አንድ

## ኢኦኒና ፣ ግሪክ — ጁላይ ፣ 1948

ዘወትር እየጮኸች ነው ከእንቅልፏ የምትነቃው ። ሁሌ የምታየውም ሕልም ያው አንድ አይነት ነው ። በአስፈሪ ማዕበል በሚናወጥ ሐይቅ መሐል ሆና ፣ አንድ ወንድና አንዲት ሴት ቅዝቃዜው አጥንት በሚሰብረው ውሃ ወስጥ ጭንቅላቷን ለማዝፈቅ ሊያስጥሟት ሲታገሉ ነው ያለመችው ። ባንና ስትነቃም በላብ ተጠምቃ በፍርሐት እየተርበደበደችና ቁና ቁና እየተነፈሰች ነበር ።

ማንነቷን ጨርሳ ዘንግታለች ። የሚታወሳትም ከቶ ምንም ነገር አልነበረም ። የምትናገረው ቋንቋ እንግሊዝኛ ቢሆንም አገሯ የት እንደሆነ እንዴትስ ወደ ግሪክ መጥታ በትንሿ ካርሜላይት የሴቶች ገዳም ውስጥ እንደገባች የምታውቀው ነገር አልነበረም ።

ውሎ ሲያድርም ቅጡ የማይታወቅ ትውስታ ለቅጽበት ብዥ—ብልጭ ብሎ እያንጓጓ ወዲያው ድርግም በማለቱም ምስሎቹን አሰባስባ

ልትጨብጥ አልተቻላትም ። ድንገት ባላሰበችውና ባልጠበቀችበት ወቅት ብቅ ብለው ያደነጋግሯታል ።

በመጀመሪያ ጥያቄዎችን አቀራርባ ነበር ። በካርሜል የሚገኙ መነኰሳት ደግና የሰው ችግር የሚገባቸው ቢሆኑም ለጥያቄዋ ምላሽ ለመስጠት እንዲናገሩ የተፈቀደላቸው ከሁሉም በዕድሜ ጠና ያሉትና ሰውነታቸው የደቀቀው የበላይዋ ሲስተር ተሬዛ ብቻ ናቸው ።

"ማን እንደሆንኩ ያውቃሉ ?"

"አላውቅም ልጄ !" አሉ ሲስተር ተሬዛ ።

"ወደዚህ ሥፍራ የመጣሁት እንዴት ነው ?"

"ከእነዚህ ተራሮች ስር ኢኦኒና የተሰኘች መንደር አለች ። ባለፈው

ዓመት ማዕበል ተነስቶ በነበረበት ወቅት በሐይቁ ላይ በትንሽ ጀልባ ውስጥ ነበርሽ ። ጀልባዋ ስትሰጥም በእግዚአብሐር ቸርነት ሁለት እህት መነኩሳት አይተውሽ ሕይወትሽን ሊያተርፉ ቻሉ ። ከዚያም ወዲህ አመጡሽ ።”

“ማን … ከዚያ በፊት የነበርኩት የት ነው ?”

“ልጄ አዝናለሁ እኔ አላውቀውም ።”

በመልሱ ልትረካ አልቻለችም ።

“ስለ እኔ የጠየቀ ሰው የለም ? ሊፈልገኝ የሞከረስ አልነበረም ?”

ሲስተር ተሬዛ ጭንቅላታቸውን በመነቅነቅ “ማንም” አሉ ።

ከጭንቀት የተነሳ ልትጮህ ፈለገች ። ቀጥላም “ጋዜጦች … ስለ እኔ መጥፋት በአምዶቻቸው ላይ ያሰፈሩት ዜና ይኖር ይሆናል” አለች ።

“እንደምታውቂው ከውጭው ዓለም ጋር ምንም አይነት ግንኙነት እንድናደርግ አይፈቀድልንም ። እግዚአብሔር ያለውን መቀበል አለብን ልጄ ። ለይቅርታው ሁሉ ልናመሰግነው ይገባናል ። በሕይወት ተርፈሻ ልና ።”

ለማግኘት የቻለችው ምላሽ ይኸንኑ ብቻ ነበር ። በመጀመሪያ ሰሞን ስለእራሷ መጨነቋ ከበሽታ ላይ ጥሏት ነበር ። ወራት እያለፉ ሲመጡ ቀስ በቀስ ጥንካሬ እያገኘችና ጤንነትዋም እየተሟላ መጣ ። ለመንቀሳቀስ ብርታት ስታገኝ መላውን ግሪክ ፯ ! የሚያደርገውን ጣፋጭ ፀሐይ እየሞቀች ፣ ነፋሻው አየር ያዘለውን የወይንና የሎሚ መአዛ እያሸተተች ፣ ውቡን የገዳም አትክልት ስትንከባከብ ቀኑን ታሳልፍለች ።

ምንም እንኳ አካባቢው ፍፁም ሰላማዊና ፀጥታ የሰፈነበት ቢሆንም የተረጋጋ መንፈስ ልታገኝ አልቻለችም ። ‘እንዲህ ጠፍቼ የትገባች ምን ሆነች ብሎ የሚያስብ ሰው ይጥፋ ?’ ብላ አሰበች ። ‘ለምን ? የፈጸምኩት በደል አለ ? ለመሆኑ ማን ነኝ ? ማን ልሆን እችላለሁ ? ኧረ እኔ ማን ነኝ ?’

ትውስታዎቹ ድንገት ብልጭ ይሉባታል ። አንድ ቀን ጠዋት ከእንቅልፏ ባንና ስትነሳ አንድ እርቃኑን የነበረ ሰው በአንድ ክፍል ውስጥ ልብሶችዋን ሲያወላልቅ በአዕምሮዋ ውልብ አለባት ። ነገሩ ሕልም ነው ? ወይንስ ባለፉት ጊዜያት በሕይወቷ ውስጥ የተፈጸመ እውነታ ይሆን ? ማነው ሰውዬው ? አግብታው የነበረ ሰው ይሆን ? ባልስ ነበራት ? የጋብቻ ቀለበት ደግሞ ከጣቷ ላይ የለም ። ሲስተር ተሬዛ ከሰጧት ጥቁር የመነኩሳት ልብስና ከንፋ የተዘረጋ ባለቀይ ዓይን ወርቅማ የወፍ ቅርጽ



ትንሽ የደረት አርማ በስተቀር ሌላ የግሏ የሆነ ነገር አልነበረም ።

ስም የሌላት በባዕዳን መካከል የምትኖር ባዳ ነበረች ። የሚረዳት ሰው የለ ። በከፍተኛ ጭንቀት የተወጠረው አእምሮዋ ፣ ጤነኛ ሆና ለመቆየት የሚችለው ፣ ዘግናኝ የቀድሞ ገጠመኝን ለማስታወስ እስካል ቃጣ ጊዜ ድረስ ብቻ መሆኑን የሚነግራት የስነ አእምሮ ሀኪም የለም ።

ምስሎቹ በፍጥነት እየተከታተሉ መታየቱን ቀጠሉ ። እንጉዷ የተበታተኑ ቁርጥራጭ ሥዕሎችንና የመልክዓምድር ካርታዎችን በየመል ካቸው ለማገጣጠም ወደሚያገለግል ሰው ሰራሹ መሣሪያ በድንገት የተለወጠ ያክል ነበር ። ቢሆንም ቅንጭብጫቢ እይታዎቹ ስሜት ሊሰጡ አልቻሉም ። የወታደር ልብስ የለበሱ ሰዎች የሞሉበት ትልቅ የሲኒማ መቅረጫ አዳራሽ ራዕይ ውልብ ይልባታል ። ፊልም በመስራት ላይ የነበሩ ሳይሆኑ አልቀሩም ። ‘የፊልም ተዋናይ ነበርኩ ይሆን ?’ ብላ እራሷን ትጠይቅና ፣ ደግሞ በኃላፊነት ቦታ ላይ የነበረች ይመስላታል ።

ግን በምን ዓይነት የኃላፊነት ቦታ ?

አንድ ወታደር እቅፍ አበባ ያበረክትላታል ። “ለዚህ ሁሉ እራስሽ መክፈል አለብሽ” ይልና ይስቅባታል ።

ከሁለት ምሽቶች በኋላ እንደገና ስለዚሁ ሰው ሕልም አየች ። በአውሮፕላን ማረፊያ ስትሰናበተው ከሱ በመለየቷ እየተንሰቀሰቀች ነበር ከእንቅልፏ የነቃችው ።

ከዚያ በኋላ ሰላም ልታገኝ አልቻለችም ። ይህ የሕይወቷ አካል ቁራሽ ፣ ያለፈው ኑሮዋ ክፍል እንጂ ሕልም ብቻ አይደለም ። ‘ማን እንደነበርኩ ማወቅ አለብኝ ፤ ለመሆኑ ማን ነኝ ?’

ሳይታሰብ በድንገት እኩለ ሌሊት ላይ ከሥውር ሕሊናዋ አንድ ስም ፍንትው አለባት ። “ካተሪን ። ስሜ ካተሪን አሌክሳንደር ነው ።”

ላይ ሰማያዊና ነጭ ቀለም ያለው የግሪክ ሰንደቅ ዓላማ ሁሌ ያውለበልባል። የሚፈለግበትን የመንግሥት ግብር ግን አይከፍልም ። በተራ ዜጎች ላይ ለሚሠራው የአገሪቱ ሕግ ተገዥ የሚሆንበትም ምክንያት ያለ አልመሰለውም ፤ በደም ሥሩ ውስጥ የሚዘዋወረው የአማልክት ደም ነውና ።

# ምዕራፍ ሁለት

## አቴንስ ፣ ግሪክ

የኮንስታንቲን ዴሚሪስ የግዛት ክልል በማንኛውም ካርታ ላይ ተከልሎ አይታወቅ እንጂ ፣ የሚያስተዳድረው ጉልት በስፋትም ሆነ በኃይል ከብዙ አገሮች የላቀ ነበር ። በዓለም ላይ ካሉት ከሁለት ወይንም ከሦስት ከማይበልጡት ታላላቅ ባለፀጋዎች መካከል አንዱ ሲሆን ፣ ተደማጭነቱና ተሰሚነቱም ያንኑ ያክል ከፍ ያለ ነበር ። የተሰጠው ማዕረግ ወይንም ሥልጣን ባይኖርም ጠቅላይ ሚኒስትሮችን ፣ መኳንንቱን ፣ አምባሳደሮችን ንና ነገሥታትን እንዳስፈለገው ያሽከረክራል ። ዴሚሪስ በበርካታ አገሮች ላይ መረቡን የዘረጋ የዋዛ ያልሆነ ሰው ነው ። ግርማ ሞገስ የተጎናፀፈ በብሩህና በበሳል አእምሮ የታደለ ከመሆኑ ባሻገር ጡንቻማው ደረቱ ፣ ሰፋፊ ትከሻዎቹና ዘንካታ ቁመናው በግድ እዩት — እዩት ያሰኛል። የቆዳው ንጣት የጠየመ ፣ ጠንካራ የግሪክ አፍንጫ ያለው ፣ ዓይኖቹ የጎመራ ወይራ ፍሬ የሚመሳሰሉ ናቸው ። የነጣቂ ጭልፊት ፊትም ዓይነት ፊት ነው ያለው ።

ነገር ያነፈነፈ ዕለት ዴሚሪስ ጨርሶ ፎለፎል ይሆናል ። ስምንት ቋንቋዎችን አጠናቆ ያውቃል ። አንደበተ ርቱዕ ነው ። በዓለም ውስጥ የታወቁ ሥዕሎች ስብስብ አለው ። በርካታ የግል አውሮፕላኖቹ ፣ ስፍር ቁጥር የሌላቸው አፓርታማዎቹ ፣ ቪላዎቹና ሕንጻዎቹ ፣ ተሰራጭተው የማይገኙበት የዓለም ክፍል የለም ። ውበት አድናቂ ከመሆኑ የተነሳ ቆንጆ ሴት አይቶ ማለፍ አይሆንለትም ። ጥሩ አፍቃሪ ነው እየተባለም በሰፊው ይነገርለታል ። ሀብት ንብረት ማካበት እንደሚሳካለት ሁሉ የሴቱም ነገር ይዋጣለታል ።

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ አገር ወዳድ ነኝ ብሎ በመኩራራት የግል ይዞታው በሆኑት በኮላናኪና በፕሳራ ደሴት ላይ በሚገኙት ቪላዎች አናት



* * *

ዴሚሪስ የሚያገኛቸው ሰዎች ሁሉ ከእርሱ አንድ ነገር ይፈልጋሉ ። ግማሾቹ ላቀዱት የንግድ ፕሮጀክት ገንዘብ እንዲሰጣቸው ፣ ግማሾቹ ለበጎ አድራጎት ድርጅት የእርዳታ እጁን እንዲዘረጋ የሚሹ ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ ጥላ ከለላ እንዲሆናቸው በወዳጅነት ይጠጉታል ። ዴሚሪስ ሰዎቹ ከእሱ የሚሹት ምን እንደሆነ መርምሮ ማወቁ ደስታን ይሰጠዋል ። ምክንያቱም አቀራረባቸው አብዛኛውን ጊዜ ቀጥተኛና ግልጽ ሳይሆን በሰበብ አስባቡ ተሸፍኖ ስለሆነ ነው ። ከተጠራጣሪነቱና ነገርን ከየአቅጣጫው ከመመርመር ባሕርይው የተነሳ የሚነገረውንና የሚታየውን እንዳለ የሚቀበል አይደለም ። የሰማውን ሁሉ የማይቀበልና፣ ማንንም የሚያምን ሰው አልነበረም። የሚመራበት ፍልስፍና “ወዳጆች ህን አቅርባቸው ፤ ጠላቶችህን ግን የበለጠ አስጠጋቸው” የሚል ነው ። ዜና መዋዕሉን የሚጽፉትም ጋዜጠኞች የሚረዱት ጨዋነቱን ፣ ቀናነቱን፣ ማራኪነቱን ፣ ዘመናይነቱን በዓለም ውስጥ ካሉት ትሑት ሰዎች አንዱ የመሆኑን የላይ ላዩ ገጽታ እንጂ ነፍሰ ገዳይ ፣ የአንገት ደም ሥር ካልበጠሰ የማይረካ ጎትጓታ ደመ ጥመኛ የመሆኑን እውነታ ለመጠርጠር ዕድል አልሰጣቸውም።

ይቅርታ የለሽ ፣ ጥቃቅኑን ነገር የማይረሳ ቂመኛ ነው ። ለጥንት ግሪካውያን “ዲካዮሲኒ” ማለትም “ፍትሕ” የሚለው ቃል “ኤክዲኪ ሲስ” ማለትም “ብቀላ” ከሚለው ቃል ጋር ተንዳኝነት አለው ። ዴሚሪስም በነኚሁ ቃላት ተለክፏል ። ቀድሞ ያስቀየሙትንና ያሰቃዩ ትን ሁሉ አይረሳም ። ሳይታደሉ ቀርተው የእርሱን ጠላትነት ያተረፉ ሁሉ ለፈጸሙት ተግባር በመቶ እጥፍ አሳር ፍዳ ከፍለዋል ። የዴሚሪስ ተአምራዊ ጭንቅላት ለብቀላ የረቀቀ ዘዴውን በሚሸርብበት ወቅት ዒላማው የሆኑት ሰዎች ቅንጣት ያህል ጥርጣሬ አያድርባቸውም ። በትእግ

ሥት ረጋ ብሎ በስፌው እያውጠነጠነ የተወሳሰበ መረቡን ይጥልባቸ ዋል። በመጨረሻም በትብትቡ ውስጥ ያፍናቸውና ጠላቶቹን ሁሉ ሲጥቀዋል። በመጨረሻም በትብትቡ ውስጥ ያፍናቸውና ጠላቶቹን ሁሉ ያደርጋቸዋል ።

ተቀናቃኞቹን ለማጥፋት አሳቡን ሲያወጣና ሲያወርድ ከፍተኛ ደስታ ይሰማዋል ። ዒላማዎቹ የሆኑትን ግለሰቦች ማንነት በሚገባ ያጠናል። ጥንካሬያቸውንና ድክመታቸውን ደህና አድርጐ ይገመግማል ።

አንድ ቀን ዴሚሪስ በእራት ግብዣ ላይ እንዳለ አንድ የተንቀሳቃሽ ፊልም አምራች "ያ ሙልጭልጭ ግሪካዊ" እያለ ሲያማው ሰማ ። ዴሚሪስ ለጊዜው ሃሜቱን ዋጥ አድርጐ ዝም ። ከሁለት ዓመታት በኋላ ይሄው ፊልም አምራች በዓለም አቀፍ ደረጃ የታወቀች አንዲት ተዋናይ ኩባንያው በሚቀርፀው አንድ ታላቅ ፊልም ውስጥ እንድትጫወት ኮንትራት ያስፈርማታል ። ዴሚሪስ የፊልሙ ሥራ ግማሽ ደረጃ እስኪደርስ ድረስ በዝምታ ይመለከታል ። ከዚያም ተዋናይዋ የጀመረች ውን የፊልም ሥራ እንድታቋርጥ በፍቅር ያጠምድና ወደ መንሸራሸሪያ ጀልባው እንድትገባ ይጋብዛታል ። "ይህ እንግዲህ የጫጉላ ጊዜያችን መሆኑ ነው" ይላታል ዴሚሪስ ተዋናይዋን ።

ጋብቻው ሳይፈፀም መሞሸሯ ነው ። በቃ ፊልሙ ሳይሰራ ቀረ ! አምራቹም ከሰረ ።

ዴሚሪስ ለጊዜው ውጤት ላላስቀጠረባቸው ግን በአእምሮው ውስጥ የሸር መረብ ለዘረጋላቸው በጣት የሚቆጠሩ ተቀናቃኞች ሊጣደፍ አልፈለገም ። ግጥሚያውን በአሸናፊነት የሚወጣበትን አሳብ ማመን ጨቱ ፣ ማቀዱና ተግባራዊ ማድረጉ ለዴሚሪስ እርካታን ይሰጡታል ። በአሁኑ ወቅት ፣ ሰው ሁሉ የዴሚሪስ ጠላት መሆን እንደማያዋጣ በመረዳቱ ያፈራው አዲስ ጠላት የለም ። ስለዚህ ዒላማው ያተኮረው ባለፈው ጊዜ በመንገዱ ላይ ቆመው በነበሩት ተፃራሪዎቹ ላይ ብቻ ነው ።

ይሁንና ኮንስታንቲን ዴሚሪስ 'ለዲካዮሲኒ' (ለፍትሕ) ያለው አመለካከት ሁለት ገጽታ ያለው ነው ። ለተፈፀመበት በደል ይቅርታ እንደማያደርግ ሁሉ የተደረገለትን ውለታ የሚረሳ አይደለም ። ዴሚሪስ ልጅ በነበረበት ወቅት መጠለያ ሰጥቶት የነበረ አንድ ድሃ ዓሣ አጥማጅ ሳያስበው የብዙ ዓሣ ማጥመጃ ጀልባዎች ባለቤት ሆኗል ።



ከድህነቱ የተነሳ በልጅነት ዕድሜው ፣ ምግብና ልብስ በነፃ ትሰጠው የነበረች አንድ ሴተኛ አዳሪ ፣ ድንገት ሳታውቀው የአፓርትማ ሕንፃ ባለቤት ሆናለች ። ሕንፃውን ማን እንደለገሣት ግን የምታውቀው ነገር የለም።

* * *

የዴሚሪስ አባት በፒሮዩስ ወደብ አካባቢ በመርከብ ላይ ተሸካሚነት ጉልበቱን ሸጦ ይተዳደር ነበር ። ዴሚሪስ አሥራ አራት ወንድሞችና እህቶች ነበሩት ። በቤታቸው ውስጥ ሆድ የሚያጠረቃ ምግብ ገበታው ላይ የቀረበበት ቀን አልነበረም ።

ከመጀመሪያውኑ አንስቶ ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ለንግድ ሥራ የነበረው ዝንባሌ ከፍተኛ ነበር ። ከትምህርት ሰዓት በኋላ ሰው የሚጠየፈውን የተላየየ ሥራ እያከናወነ ገንዘብ ያገኝ ነበር ። ዕድሜው አሥራ ስድስት በሆነበት ወቅት ገንዘብ ተጠራቅሞለት ነበርና ከአንድ በዕድሜ ገፋ ካለ ሸሪክ ጋር በወደቡ አካባቢ አነስተኛ የምግብ መሸጫ ኪዮስክ ከፈተ ። ገበያው ሲደራና ንግዱ ሲጧጧፍ ሸሪኩ ዴሚሪስን ካደውና ከሸርከናው አባረረው ። ዴሚሪስ ሰውየውን ለማጥፋት አሥር ዓመት ፈጀበት ። ወጣቱ በከፍተኛ የዕድገት ፍላጎት ይጨስ ጀመር ። ሌሊት በጨለማው ላይ ዓይኑን አፍጦ 'ሀብታም እሆናለሁ ፤ ዝነኛ እሆናለሁ ፤ አንድ ቀን ስሜ በሁሉም ዘንድ ይታወቃል' እያለ ያስባል ። ይህ ሐሳብ ብቻ ነው እሹሩሩ እያለው እንቅልፍ የሚያስወስደው ። ምኞቱ እንዴት እውን እንደሚሆን ግን አያውቅም ። ብቻ አንድ ቀን እንደሚሳካለት እርግጠኛ ነበር ።

* * *

ዴሚሪስ አሥራ ሰባተኛው የልደት በዓሉን ሲያከብር ስለሳዑዲት ዓረብ የነዳጅ ዘይት በጋዜጣ ላይ የወጣውን አነበበ ። የዕድሉ በር ፣ ወለል ብሎ ሲከፈት ታየው ።

ወደ አባቱ ሄዶ "ወደ ሳዑዲት ዓረብ መጓዜ ነው ። በነዳጅ ዘይት ማምረቻ ውስጥ ተቀጥሬ ልሠራ" አለ ።

“ስለነዳጅ ዘይት ማምረቻ ምን ታውቅና?”
“ምንም አላውቅም አባባ ። ወደ ፊት ልማር ነው ።”
ከአንድ ወር በኋላ ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ወደዚያው ተጓዘ ።

* * *

ከውጭ የሚመጡ ተቀጣሪዎችን የሁለት ዓመት የሥራ ኮንትራት ውል ማስፈረም የትራንስ ኮንትኔንታል የነዳጅ ዘይት ኮርፖሬሽን ደንብ ነው ። ቢሆንም ኮንትራቱን መፈረሙ ዴሚሪስን ምንም ያህል አላሳሰበ ውም ። የወደፊት ዕድሉ እስኪሰምርለት በሳውዲት ዓረብ ውስጥ ለመቆየት አቅዷል ። ሰምቶት የነበረው ማራኪ የጥንታዊ አረቦች ጀብድ አፈ-ታሪክ ፣ ትንግርት ያላቸው ሴቶችና አስደናቂዋ ምድር ፣ እንዲሁም ከመሬቱ ውስጥ ስለሚፈልቀው ጥቁር ወርቅ በሚያጓጓ ሁኔታ በሕሊናው ስሎ ነበር ። ደርሶ ሲያየው ግን የሚሰቀጥጥ ሆኖ ነው ያገኘው ።

በበጋው ወራት አንድ ቀን ጠዋት ዴሚሪስ በበረሃው መሐል ከሚገኘው ቀፋፊ የፉዲሊ ካምፕ ደረሰ ። በካምፑ ውስጥ ያሉ የድንጋይ ቤቶች በባራስቲስ በጥሻ በተሠሩ ጐጆዎች ተከበው ለዓይን ያስጠላሉ ። አነስተኛ ክፍያ የሚያገኙ በሺህ የሚቆጠሩ ሠራተኞች በሥፍራው ይሠራሉ ። አብዛኛዎቹ የሳውዲ ዜጎች ናቸው ። በአቧራማው ጥርጊያ ጐዳናዎች ላይ የሚጓዙት ሴቶች ፊት በመርገፍ ተሸፍኗል ።

ዴሚሪስ ፣ የኮርፖሬሽኑ አስተዳደር ሥራ አስኪያጅ የጄ ጄ ማክልንታይር ቢሮ ወደሚገኝበት ሕንፃ አመራ ።
ማክልንታይር ቀና ብሎ
ወጣቱ ልጅ ወደ ቢሮው እንደገባ
“ተቀጥረህ መምጣትህ ነው?” ሲል ጠየቀው ።
“አዎ ጌታዬ ።”
“ከዚህ በፊት በነዳጅ ማምረቻ መስክ ሠርተህ ታውቃለህ ልጄ?”
ዴሚሪስ ለመዋሸት ትንሽ ቃጣውና “አይ ጌታዬ” ብሎ መለሰ ።
ማክልንታየር ፈገግ አለ ። “አይዞህ ትንሽ ስትሰነብት ሥፍራውን ትወደዋለህ ። በእርግጥ ያለህበት ቦታ ከከተማ ሚሊዮን ማይል ርቆ ነው ያለው ። ደህና ምግብ አይገኝም ። የመጥረቢያ ሲሳይ ለመሆን ካላሻህ በቀር ሴት ለመንካት አታስብም ። ማታ ማታ የምታደርገው ምንም ነገር የለም ። ቢሆንም ክፍያው ጥሩ ነው ። እሺ?”



“እኔም ትምህርት ልቀስም ነው አመጣጤ” ሲል መለሰ ዴሚሪስ በትህትና ።

“እረ? ደግ ፣ እንግዲህ በመጀመሪያ መማር የሚገባህ ምን እንደሆነ ልንገርህ ። ያለኸው በእስላሞች አገር ውስጥ ነው ። አልኮል መጠጣት ክልክል ነው ። ሲሰርቅ የተያዘ ቀኝ እጁ ይቆረጣል ። ለሁለተኛ ጊዜ ከሰረቀ ግራ እጁ ይደገማል ። ሰው ከገደልክ ደግሞ አንገትህ ይቀነጠሳል።”

“ማንንም የመግደል እቅድ የለኝም ።”

“ቆይ” አለ ማክልንታየር ኮስተር ብሎ ። “ገና እዚህ መድረስህ አይደል?”

ቅጥር ግቢው ከተለያዩ አገሮች የመጡ እንደባቢሎን ግምብ ሠራተኞች ሁሉም በየፊናው የየራሱን የተለያየ ቋንቋ የሚናገርበት ነው ። ዴሚሪስ ጥሩ የመስማት ችሎታ ያለው ሲሆን ቋንቋም ቶሎ የማወቅ ተሰጥኦ አለው ። በዚያ በረሃ ውስጥ የመንገድ ሥራና ቤት እነፃ ይካሄዳል ። የኤሌክትሪክና የስልክ መሥመር ይዘረጋል ። የዐውደ ጥናት ማካሄጃ ተቋም ፣ የምግብና የመጠጥ ማከፋፈያ ፣ የቱቦ ቀበራ ቅየሳ ፣ እንዲሁም የሕክምና ግልጋሎቶች ዝግጅት ሲከናወን ይታያል ። ሌሎችም በርካታ የተለያዩ ተግባሮች ሲከናወኑ ወጣቱ ዴሚሪስ ተመልክቷል ። ሰዎቹ በመቶ ዲግሪ ፋራናይት የሙቀት መጠን እየተቀቀሉና በዝንብ፣ በትንኝና በአቧራ እየተሰቃዩ ተግባራቸውን ያከናውናሉ ። ትኩሳትና ተቅማጥ በየጊዜው ይፈራረቅባቸዋል ። በዚህ በረሃ ውስጥ እንኳ በሰዎች ግንኙነት መካከል የደረጃ መበላለጥ አለ ። በከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙት ነዳጅ ዘይቱ የት እንደሚገኝ ፍለጋ የሚያደርጉት ናቸው ። ከታች ያሉት የኮንስትራክሽን ሠራተኞች ሲሆኑ እነኝህም “ወዝ አልባ” በሚል ልዩ ስያሜ ይታወቃሉ። በጽሕፈት ሥራ ለተሠማሩትም “አብረቅራቂ ግሮ ጥሮ” የሚል ቅጽል ተሰጥቷል ።

በአጠቃላይ በዘይት ቁፋሮው ተግባር ላይ የተሠማሩት ማለትም የሥነ አፈር ተመራማሪዎች ፣ ቀያሾች ፣ መሐንዲሶችና የዘይት ኬሚስቶች በሙሉ አሜሪካውያን ናቸው ። ምክንያቱም ዘመናዊ የነዳጅ ዘይት ማውጫዎች መሣሪያ በዩናይትድ ስቴትስ በመፈልሰፉና አሜሪካኖች በዚህ መሣሪያ የመጠቀም ልምድ አላቸው ተብሎ ስለሚታመንበት

ነው። ወጣቱም ከተሰጠው የሥራ ድርሻ ወጣ እያለ ከእነኚሁ ሰዎች ጋር ወዳጅነት ለመመስረት ጥረት ጀመረ ።

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ አብዛኛውን ጊዜውን በእነኚህ ቆፋሪዎች አካባቢ በማሳለፍ የተለያዩ ጥያቄዎችን ያቀርብላቸው ነበር ። ልክ ምቃቱ አሸዋ ውሃ እንደሚመጥ ሁሉ የሚያገኛቸውን መልሶችና መረጃዎች በአእምሮው እየመጠጠ ያጠራቅማል ።

130 ጫማ ርዝመት ያለውን በጣም ግዙፍ የመቆፈሪያ መሣሪያውን ተሸክሞ ያለውን ባለብዙ ማገር የብረት ምሰሶ የሚያንቀሳቅሱትን ባለሙያዎች ተጠጋና የቁፋሮው ተግባር ለምን በሁለት በተለያዩ መንገዶች በመከናወን ላይ እንዳለ አልገባኝም" ሲል ጠየቀ ።

ቆፋሪውም "ልጄ ፣ አንዱ ባለሽቦ መደርመሻ ሲሆን ሌላው ደግሞ ሹል ጫፍ ኖሮት በፍጥነት እየተሽከረከረ የሚቆፍረው ሮተሪ ነው ። በዛሬው ጊዜ በአብዛኛው ሮተሪ ነው የሚመረጠው ። ሁለቱም ቢሆኑ ለአገልግሎት ሲጠመዱ አጀማመራቸው ላይ ተመሳሳይነት አላቸው ።"

"ተመሳሳይነት አላቸው?"

"የባለሽቦ መደርመሻውም ሆነ ሮተሪው የሚገጠምበት ይህን የሚመስል ዴሪክ ነው ። መቼም ዴሪክ ሲሰራ አይተሃል ። ትልልቅ ሕንፃ ሲሰራ እየተሽከረከረ ከባድ ዕቃ ሲያቀብል ። እይ ፣ ግዙፍ የብረት ማማ ነው አይደል? እና ዴሪክ መተከል አለበት" አለና ቆፋሪው በጉጉት መልሱን ይጠብቅ ወደነበረው ወጣት ፊት ተመለከተ ። ቀጠለና "መሣሪያው ዴሪክ ለምን እንደተባለ እንደማታውቅ እርግጠኛ ነኝ" አለው ።

"አላውቀውም ጌታዬ ።"

"ዴሪክ በአስራ ሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ወንጀለኞችን ይሰቅል የነበረ ሰው ስም ነው ።"

"ገባኝ ።"

"ባለሽቦ መደርመሻው ቀደምትነት አለው ። ከመቶ ዓመታት በፊት ቻይናውያን የውሃ ጉድጓድ ይቆፍሩ የነበሩት በዚህ መሣሪያ ነበር ። እጅግ በጣም ከባድ የሆነ ሹል መሣሪያ በወፍራም ሽቦ ላይ አስረው ወደ ላይ ካንጠለጠሉ በኋላ ወደ መሬት ሲለቁት ይቦድሳል ። በዛሬው ጊዜ ግን ሰማንያ አምስት በመቶው የጥልቅ ጉድጓዶች ቁፋሮ ተግባር የሚከናወነው በሮተሪ ነው ።"



"ይቅርታ ፣ የሮተሪ አቆፋፈር የሚከናወነው እንዴት ነው?"

ሰውየው ዝም ካለ በኋላ "መልካም ፣ ጉድጓድ ለመቆፈር መሬቱን ከመቅደድ ይልቅ ቀስ በቀስ ትቦረቡራለህ ። ይህን ታየለህ? በዴሪኩ መካከል በመሣሪያ አማካይነት የሚሽከረከር ክብ ብረት አለ ። ይህ ክብ ብረት ቧንቧውን ነክሶ በመያዝ እያሽከረከረ መሬት ውስጥ ያዘልቀዋል ። ከቧንቧው ጫፍ ላይ ጠንካራ የብረት ምላጭ ተሰክቷል ።"

"ይሄ ቀላል ይመስላል ።"

"እንደምታየው ቀላል ሳይሆን ውስብስብ ነው ። ቁፋሮውን በምታካሄድበት ወቅት አፈሩን ከሥር የምታስወጣበት ዘዴ መኖር አለበት ። ጉድጓዱ እንዳይደረመስ ጥንቃቄ ማድረግ ያሻሃል ። በጥግና ጥግ ጋዝና ውሃ ሲመነጭ ማሸግ ይኖርብሃል ።"

"ታዲያ ያ ሁሉ ጥልቀት ሲቆፈር ሮተሪው አይዶለዱምም?"

"ልክ ነህ በሚዶለዱምበት ጊዜ መቦርቦሪያውን ሰበን እናወጣውና አዲስ ምላጭ ቧንቧው ጫፍ ላይ አጉርሰን መልሰን ወደ ጉድጓዱ እንጨምረዋለን ። እንዴት ነው ቆፋሪ ለመሆን ትለፍጋለህ እንዴ?"

"አይ ጌታዬ የነዳጅ ዘይት ጉድጓዶች ባለቤት ለመሆን ነው የምፈልገው"

"ጎሽ! በል ፣ ወደ ሥራዬ ልመለስ ።"

አንድ ቀን ጠዋት መቆፈሪያው ከጉድጓዱ ውስጥ ሲከተት እየ። መሣሪያውም ወደ ታች እንደመቦርቦር ፈንታ የጉድጓዱን ግድግዳ በስቶ ድንጋይ ይዞ ሲወጣ ዴሚሪስ ተመለከተ ።

"ይቅርታ እንዲህ የሚደረገው ለምንድን ነው? " ሲል ዴሚሪስ ጠየቀ።

ቆፋሪው ቀና ብሎ ቅንድቡን ጠረገና "ነዳጅ ዘይት መኖር አለመኖሩን የምንረዳው ድንጋዩን በመመርመር ነው" አለ ።

"ገባኝ።"

ሥራው በደህና ሁኔታ በመከናወን ላይ እያለ ቆፋሪዎቹ "ወደ ቀኝ በኩል መታጠፌ ነው" እያሉ ሲጮሁ ዴሚሪስ ይሰማል ። ትርጉሙ ጉድጓድ እያበጀን ነው ማለት ነው ። ዴሚሪስ ስፋታቸው ከሁለትና ሦስት ኢንች የማይበልጡ በጣም ብዙ ጉድጓዶች በየቦታው መማሳቸውን ልብ ብሏል ።

"ይቅርታ ፤ እነኚህ ደግሞ ለምን የሚሆኑ ናቸው?" ሲል ጠየቀ ወጣቱ ። "እነኚህ ተስፋ ያላቸው ጉድጓዶች ናቸው ። ከሥራቸው ምን እንዳለ ይታወቃል ። እንዲህ አነስ — አነስ አድርጎ በመቆፈር የኩባንያውን ጊዜና ገንዘብ መቆጠብ ይቻላል ።"

"ገባኝ ።"

ወጣቱ በሚያየው ነገር በመገረሙ ጥያቄ አከታተለ ።

"ይቅርታ የት ቦታ መቆፈር እንደሚገባችሁ የምታውቁት እንዴት ነው?"

"በጣም በርካታ የሆኑ የሥነ አፈር መርማሪዎች አሉን ። እነኝህም የአፈሩንና የድንጋዩን ናሙና ወስደው ጥናትና ምርምር ያካሂዳሉ ። ከዚያ በኋላ ቆፋሪዎቹ...."

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ከጠዋት ጀምሮ ጀምበር እስክትጠልቅ ድረስ በዚያ ቃጠሎ በረሃ ውስጥ የተለያዩ ዕቃዎችን ከወዲያ ወዲህ ሲያጓጉዝ ፣ መሣሪያዎችን ሲያፀዳዳ ፤ መርዛማ የሆነውን ጋዝ ለማቃጠል ቀንና ሌሊት ጋራው ላይ በሚንቦገቦገው እሳት አጠገብ ተሽከርካሪውን እያመላለስ ይማከናል ።

ጁ፡ጁ ማክልንታይር ለዴሚሪስ የነገረው እውነቱን ነበር ። ምግቡ መጥፎ ነው ። ኑሮው ከባድ ነው ። ማታ ማታ የሚሠራ ምንም ነገር የለም። ከተነገረው የባሰ ሁኔታ የታየው ዴሚሪስ በመላ ሰውነቱ ቆዳ ላይ ያሉት ጥቃቅን ቀዳዳዎች ሁሉ በአሸዋ የተደፈኑ መስሎ ተሰማው ። በረሃው በረሃ ነው ። ከዚያ ለማምለጥ የሚቻልበት መንገድ የለም ። የአሸዋው ቢይት ወደ ጉጆው እየቦነነ ፣ ከልብሱ ዘልቆ ሰውነቱ ላይ እየተጣበቀ ዴሚሪስን ሊያሳብደው ይቃጣል ።

አውሎ ነፋሱ ለጉድ ነው ። አሸዋማው ውሽንፍር አእምሮ እስኪያስት ድረስ ሳያቋርጥ ከወር ወር እያፏጨ ይነፍሳል ።

ዴሚሪስ በጉጆው ውስጥ ሆኖ በበሩ በኩል አሸዋማውን ቢይት እየተመለከተ "በዚህ ሁኔታ ውጭ ተወጥቶ ሥራ ይሠራል?" አለ ።

"እንዴት ተደርጎ?"

በአካባቢው ነዳጅ ዘይት የሚያመነጩ አዳዲስ ሥፍራዎች ተገኝተዋል ። በአቡ ሃድሪያህ ፣ በካቲፍና በሃራድ ፣ ነዳጅ በመፍለቁ ሠራተኞቹ



ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ሥራ በዝቶባቸዋል ። አንድ እንግሊዛዊ የሥነ አፈር ተመራማሪና ባለቤቱ በቅርቡ ተቀጥረዋል ። የሄንሪ ፓተር ዕድሜ ከስልሳ አምስት ዓመት በላይ ሲገመት ባለቤቱ ሲብል ሰላሳ አራት ዓመት ገደማ ይሆናታል ። ሲብል ፓተር ቁንጅና የሌላት ወፍራም ስትሆን በጣም የሰለለው ድምጿ ሲሰማ ለጆሮ አይጥምም ። እንደዚያም ሆኖ በፋዲሊ አካባቢ እንደ ውብ ሴት ትቆጠራለች ። ሄንሪ ፓተር ለአዲስ የነዳጅ ዘይት ፍለጋ በየጊዜው ወደሌላ ሥፍራ ስለሚሄድ ባለቤቱ ብቻዋን የምትሆን በት ወቅት በርካታ ነበር ።

ባልና ሚስቱ ወደተሰጣቸው ቤት ሲገቡ ዕቃ ማጓጓዙን እንዲረዳትና እንዲያለማምዳት ዴሚሪስ ተመድቦ ነበር ።

ሲብል ፓተር "በሕይወቴ ውስጥ እንዲህ ያለ አስከፊ ቦታ አይቼ አላውቅም" ስትል ተነጫነጨች ። "ሄንሪ ሁልጊዜ በአስቸጋሪ ሥፍራ ያነከራትተኛል ። እኔም ለምን አብሬው እንደምንከረፈፍ አይገባኝም ።"

"ባለቤትዎ እኮ በጣም የተከበረ ሥራ ነው የሚያከናውነው" ሲል ዴሚሪስ ሊያረጋጋት ሞከረ ።

ማራኪውን ወጣት ትኩር ብላ አይታው "ባለቤቴ መሥራት ያለበትን ሥራ በሙሉ በቅጡ የሚፈጽም አይደለም ። የምለው ገባህ?"

በትክክል ገብቶታል ። "አልገባኝም እሜቴ" አለ ።

"ስምህ ማነው?"

"ዴሚሪስ ፣ ኮንስታንቲን ዲሚሪስ ነው እሜቴ"

"ጓደኞችህ ማን ብለው ነው የሚጠሩህ"

"ኮስታ"

"መልካም ፤ አንተና እኔ በጣም ጥሩ ጓደኛሞች ለመሆን የምንችል ይመስለኛል ኮስታ ።"

"ሁለታችን ከእነኚህ ባዕዳን ሰዎች ጋር የምንመሳሰልበት ነገር ያለ አይመስለኝም ።"

"ወደ ሥራዬ ልመለስ" አለ ዴሚሪስ ።

ሲብል ፓተር ፣ ለጥቂት ሳምንታት በሰበብ አስባቡ ወጣቱን ታስጠራው ነበር ።

“ሄንሪ እንደገና ዛሬ ጠዋት ሄደ” አለችው ። “ያንን የማይረባ
ቁፋሮውን ሊያከናውን ነው የሄደው ።” ቀጠለችና በቀስታ “ስንት
መቆፈር የሚገባው ነገር እቤት ውስጥ እያለ” ብላ ተናገረች ።
ዴሚሪስ ምንም መልስ አልነበረውም ። የሥነ አፈር ተመራማሪው
በኩባንያው የሥልጣን ተዋረድ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ያለው በመሆኑ
ከፓተር ሚስት ጋር ተነካክቶ ከሥራው ሊፈናቀል ዴሚሪስ አልፈለገም ።
እንዴት እንደሚሆን ባያውቅም ከእለታት አንድ ቀን በዚህ ሥራ
እማካይነት ምኞቱ ከግብ ሊደርስለት እንደሚችል ግን እርግጠኛ ነበር ።
ነዳጅ ዘይት ወደፊት ተስፋ ያለውና ታዳጊም ስለሆነ እራሱም ከዚሁ
ምርት ጋር ለመቆራኘት አስቧል ። መጪው ዘመን የነዳጅ ዘይት ነው ።
እና እርሱም የዚሁ አካል ለመሆን ቆርጦ ተነስቷል ።

አንድ ቀን እኩለ ሌሊት ላይ ሲብል ፓተር ዴሚሪስን አስጠራችው ።
አጥር ግቢውን አልፎ የቤቷን በር አንኳኳ ።
“ግባ ።” ሲብል ሰውነቷን ወለል አድርጎ የሚያሳይ ስስ የማታ
ልብስ ለብሳለች ።
“እ ... እመቤቴ ፈልገውኝ ነበር?”
“አዎ ፡ ና ግባ ኮስታ ። የራስጌው መብራት ተበላሽቶብኝ ነው ።”
ዴሚሪስ ወደራስጌው መብራት አመራና ብልሹቱን ለማወቅ ብድግ
አድርጎ ማገላበጥ ጀመረ ። “አምፖል የለውም ... ።” ሰውነቷን
ከጀርባው እነካክታ በእጇ ስታሻሸው ተሰማው ። “ ሚስስ ፓተር ...”
ከንፈሯን ከከንፈሩ አጣብቃ ወደአልጋው ትገፋው ጀመር ። ከዚያ
በኋላ እራሱን ሊቆጣጠር አልቻለም ።
ልብሱን አወላልቆ እውስጧ ሰጠመ ። በደስታ ብዛት ትጮሃለች ።
“እንዲያ ነው! እ! አዎ! እንደሱ ነው ። አምላኬ ፡ ብዙ ጊዜኮ ሆኖኛል!”
ማሳረጊያውን ቁና ትንፋሽ እንደለቀቀች ሰውነቷ ተንዘፈዘፈ ። “እ
የኔ ፍቅር እወድሃለሁ!”
ዴሚሪስ ደንግጦ ተጋድሞ ቀረ ። ‘ምን ማድረጌ ነው? ፓተር ይህንን
ጉዳይ ካወቀው አለቀልኝ ማለት ነው ።’
የሚያስበውን ያወቀች ይመስል “ይህቺ ጥብቅ ምስጢራችን ናት ፡
አይደል የኔ ፍቅር?” ብላ በሳቅ ተንከተከተች ።



ያቺ ምስጢር ለብዙ ወራት በዚያው ዓይነት ቀጠለች ። ዴሚሪስ ሊተዋት የሚችልበት መንገድ አልነበረም ። ባሏ ነዳጅ ዘይት ፍለጋ ለብዙ ቀናት ከሚስቱ ስለሚለይ ዴሚሪስ ከእርሷ ጋር ወሲብ ላለመፈጸም ሊያቀርብ የሚችለው ምክንያት አልታይህ ብሎታል ። ይባስ ብሎ ደግሞ ሲብል ፓተር በዴሚሪስ ፍቅር ከንፋለች ።

“በእንዲህ ዓይነቱ ሥፍራ መሥራት የማይገባህ ግሩም የሆንክ ሰው ነህ የእኔ ፍቅር ። እኔና አንተ ወደ እንግሊዝ አገር እንመለስ” አለችው ።
“አገሬኮ ግሪክ ነው ።”

“ከዛሬ ወዲያ ግሪክ አይደለም” ብላ የፈረጠመውን ብልቱን ደባበሰች ።

“ከእኔ ጋር ወዳገሬ ትሄዳለህ ። ሄንሪን ፈትቼ አንተን አገባለሁ ።”
ዴሚሪስ በሽብር ተወረረ ። “ሲብል ፡ እኔ ... እኔ ገንዘብ የለኝም እኔ ...”

ደረቱን በከንፈሯ እያሻሸች “ያ ችግር አይደለም ፡ እንዴት ገንዘብ ማግኘት እንደምትችል እኔ አውቃለሁ የእኔ ማር” አለችው ።
“ታውቂያለሽ?”

ቀና ብላ አልጋው ላይ ተቀመጠች ። “ትናንት ማታ ሄንሪ አዲስ ትልቅ የነዳጅ ዘይት ማፍለቂያ ሥፍራ ማግኘቱን ገልጦልኛል ። ባሌ በዚህ ዓይነቱ ተግባር በጣም ጉበዝ ነው ። እና በውጤቱ በጣም ተደስቷል። የግኝቱን ሪፖርት አጠናቅቆ ወደሥራው ሲሄድ ነገ ጠዋት እንዳስረክብለት አደራ ብሎኛል ። ሪፖርቱም ከእኔ ዘንድ ነው ። ልታየው ትፈልጋለህ ?”

የዴሚሪስ የልብ ትርታ ፍጥነት ጨመረ ። “አዎ እ ... እ እፈልገዋለሁ ።” ከአልጋው ወርዳ በፍጥነት ከጥግ ወደምትገኘው ጠረጴዛ ስትሄድ ተመለከታት ። ትልቅ ፖስታ አንስታ ወደአልጋው ተመለሰች ።

“ክፈተው ።”

ዴሚሪስ ትንሽ ካቅማማ በኋላ ፖስታውን ከፍቶ ከውስጥ ያለውን ወረቀት አወጣ ። ባለአምስት ገጽ ነው ። ገረፍ ገረፍ አድርጎ አንብቦ እንደጨረሰ እንደገና ወደኋላው ተመልሶ በጥንቃቄ ማንበብ ጀመረ ።
“ዘገባው ጠቃሚነት ያለው ይመስልሃል ?”

'ዘገባው ጠቃሚነት ያለው?' በታሪክ ውስጥ እስካሁን ከተመዘገ
ቡት የነዳጅ ዘይት ማፍለቂያዎች ሁሉ ሊበልጥ ስለሚችለው የነዳጅ
ክምችት የሚያወሳ ሪፖርት ነው ።

ዴሚሪስ ስሜቱን ደበቅ አድርጐ "አዎ ፣ ጠቃሚነት … ሊኖረው
ይችላል " አለ ።

"መልካም እንግዲህ ይኸውልህ" አለች ሲብል በደስታ ። "ይኸው
አሁን ገንዘብ አግኝተናል ።"

በትካዜ "እንዲህ በቀላሉ የሚሆን ነገር አይደለም" አላት ።

"ለምን አይሆንም?"

ዴሚሪስ ሊያስረዳት ሞከረ ። "ይህ የሚጠቅመው ክምችቱ
ያለበትን መሬት ለመግዛት አቅም ላለው ሰው ነው ። ያለገንዘብ
አይሆንም። በባንክ ደብተሬ ውስጥ የተመዘገበው ሦስት መቶ ዶላር ብቻ
ነው ።"

"አይ ፣ ለዚህ አትጨነቅ ። ሄንሪ ገንዘብ ስላለው ቼክ እጽፍልሃለሁ።
አምስት ሺህ ዶላር አይበቃም?"

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ የሰማውን ለማመን አልቻለም ።

"አዎ እኔ … ምን ለማለት እንደምችል አላውቅም ።"

"ለእኛኮ ነው የኔ ፍቅር ለወደፊት ኑሮአችን ።" አልጋው ላይ
ተቀምጦ ብዙ አሰላሰለ ።

"ሲብል ፣ ይህን ሪፖርት ለአንድ ወይም ለሁለት ቀን ሳትልኪው
ልታቆዪው አትችዪም ?"

"እንዴታ ፣ እስከ ዓርብ ድረስ አቆየዋለሁ ። የኔ ፍቅር ፣ ይህ በቂ ጊዜ
ነው?" በቀስታ ጭንቅላቱን አወዛወዘና "አዎ ፣ በቂ ጊዜ ነው ይበቃኛል"
አለ።

ሲብል አምስት ሺውን ዶላር ስትሰጠው በልቡ 'ይህ ስጦታ
አይደለም ብድር ነው' አለ ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ አዲሱ የነዳጅ ዘይት
ክምችት ያለበትን ቦታ ገዛ ። ከጥቂት ወራት በኋላ ነዳጅ ዘይቱ መውጣት
እንደጀመረ ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ባንዴ ሚሊየነር ሆነ ።

ለሲብል ፖተር አምስት ሺውን ዶላር መልሶ ከፈላት ፤ አዲስ የማታ
ልብስ ገዝቶ ላከላትና ወደግሪክ ተመለሰ ። ከዚያን ጊዜ በኋላ አይታው
አታውቅም ።



# ምዕራፍ ሦስት

በተፈጥሮ ሂደት ውስጥ የተከሰተ ማንኛውም ነገር ጨርሶ አይጠ
ፋም የሚል አመለካከት አለ ። ከዚህ ቀደም ተሰምቶ የነበረ ድምጽና
የተነገረ ቃል ሁሉ ፣ አሁንም በጊዜና በሥፍራ ተወስኖ የሚኖር ሲሆን
ምናልባት አንድ ቀን በትውስታ ብቅ ይልብን ይሆናል ።

ራድዮ ከመፈልሰፉ በፊት በአካባቢያችን ያለው አየር በድምጽ ፣
በሙዚቃ በዜናና በዓለም አካባቢ በሚፈልቁ ንግግሮች የታመቀ ነው
ብሎ ማን ያምን ነበር? አንድ ቀን ወዳለፈው ጊዜ ተመልሰን ሊንኮሊን
ያደረጋቸውን ንግግሮች እናዳምጥ ይሆናል ፤ የሼክስፒሪን ድምፅ እንሰማ
ይሆናል ፤ የተራሮች ላይ ስብከቶችን …

ካተሪን አሌክሳንደር ድሮ የሰማቻቸው ድምፆች እንደገና ከጆሮዋ
ውስጥ ገቡ ። ሆኖም የተምታቱና የተቆራረጡ ስለነበሩ ግራ ያገቡዋታል ።

'ካቲ ፣ አንቺ ልዩ ሴት መሆንሽን ታውቂያለሽ? መጀመሪያ ያየሁሽ
እለት ነው ይህንን ልገነዘብ የቻልኩት ።'

'በቃ ፣ እህል ውሃችን አልቋል ። የምፈልገው ፍቺ ነው ። ከሌላ ሰው
ፍቅር ይዞኛል …'

'ምን ያህል እንዳስቀየምኩሽ ይገባኛል … ውሳኔውን ለአንቺ
ትቻለሁ …'

'ሊገድለኝ እኮ ነበር'

'ማን ?'

'ባሌ ።'

ድምፆቹ የሚቆሙ አይደሉም ። ያስጨንቃሉ ፤ ያሰቃያሉ ፣ ያለፈው
ሕይወቷ ትዝታዎች እንደሲኒማ በአዕምሮዋ ውስጥ በፍጥነት ይሮጣሉ ።

የሴቶቹ ገዳም ውብና ሰላም የሰፈነበት ገነት ቢሆንም በድንገት ወደ

እሥር ቤት ተለውጦባታል ። 'ይሄ ለኔ የሚሆን ቦታ አይደለም ። ታዲያ ለኔ የሚሆነው ቦታ የት ነው?' ለጥያቄዋ ምላሽ አልነበራትም ።

በገዳሙ ውስጥ መሰተዋት የሚባል ነገር ባይኖርም ፊትን ደህና አድርጐ የሚያሳይ ኩሬ ከአትክልት ሥፍራው አጠገብ አለ ። ካተሪን በኩሬው ውስጥ መልኳን ለማየት በመፍራቷ ሆን ብላ ትርቀው ነበር ። ዛሬ ጠዋት ግን ወደኩሬው በመቅረብ ተንበርክካ ወደታች ተመለከተች ። እጅግ ውብ የሆነች ፣ የፊቷ ቆዳ በፀሐይ ሙቀት የጠየመ ፣ ሐር የመሰለ ጥቁር ፀጉር ያላት ፣ መጐሳቆሏን ግራጫማ ዓይኗ የሚናገሩላት ሴት ምስል ውሃው ላይ አየች ። ምናልባት ውሃው የሀሰት ምስል አሳይቶ ይሆን? ለፈገግታ የተዘጋጀ ገራገር አፍና ከወደጫፉ በመጠኑ ቀና ያለ አፍንጫ ያላት ፣ ሰላሳ ዓመት ትንሽ ያለፋት የቆንጆ ሴት ነጸብራቅ ወደላይ ሲመለከታት አየች ። ምን ያደርጋል ታዲያ ፣ ያለፈውም ሆነ የወደፊት ማንነቷ የማይታወቅ ሴት … 'የሚረዳኝ ሰው ማግኘት አለብኝ ።'

ተስፋ በቆረጠ ስሜት 'የማነጋግረው ሰው ማግኘት አለብኝ ።' አለችና ወደ ሲስተር ተሬዛ ቢሮ ሄደች ።

"ሲስተር …"

"እህ ፣ የኔ ልጅ"

"እ … ሀኪም ማናገር የሚያስፈልገኝ ይመስለኛል ። ማንነቴን እንዳውቅ የሚረዳኝ ሰው ማግኘት አለብኝ ።"

ሲስተር ተሬዛ ለረጅም ጊዜ ዝም ብለው ተመለከቷትና "ቁጭ በይ" አሏት ።

ካተሪን ከጥንታዊው መቀመጫ ማዶ ካለው ደረቅ ወንበር ላይ ተቀመጠች ።

ሲስተር ተሬዛ በእርጋታ "ወዳጄ ፣ ሐኪምሽ እግዚአብሔር ነው! እሱ እንድታውቂው የሚገባሽን ሁሉ ቀስ ብሎ ያሳውቅሻል ፣ ከእኛ ውጭ ሌላ እንግዳ ወደዚህ ገዳም ሊገባ እንደማይፈቀድለት ታውቂ የለ?"

ካተሪንን ወዲያው አንድ ትውስታ ብልጭ አለባት ። … ይህ ነው ልትል የማትችለው ሰው በገዳሙ አትክልቶች ውስጥ ሲያነጋግራት—የሆነ ነገር ሲሰጣት … ከዚያም እልም ሲል ።

"ይህ የእኔ መኖሪያ አይደለም ።"

"ታዲያ የት ነው ያንቺ መኖሪያ?"

"ችግሩ ይሄ አይደል? ምን አውቄ ። አንድ ለማወቅ የምፈልገው ነገር ስላለ ነው ። እባክዎን ሲስተር ተሬዛ ይቅርታ ያድርጉልኝ ፣ ቦታዬ እዚህ እንዳልሆነ ግን አውቃለሁ ።"

ሲስተር ተሬዛ ትኩር ብለው ፊቷን በጥሞና አጠኑ ።

"እሺ ከዚህ ብትለቂ ወዴት ነው የምትሄጂው?"

"አላውቀውም ።"

"ልጄ እስቲ ላስብበትና በቅርቡ እንደገና እንነጋገርበት ።"

"አመሰግናለሁ ሲስተር ።"

ካተሪን እንደወጣች ሲስተር ተሬዛ ለረዥም ጊዜ ፈዝዘው ተቀመጡ። በጣም አስቸጋሪ ከሆነ ውሳኔ ላይ መድረስ ሊኖርባቸው ነው ። በመጨረሻም ወረቀትና ብዕር አንስተው መጻፍ ጀመሩ ።

"ክቡር ጌታዬ ፣" ብለው ጀመሩ ። "አንድ ነገር ስላጋጠመኝ ላሳውቆት ብዬ ነው ። ወዳጃችን ገዳሙን ለመልቀቅ የምትፈልግ መሆኗን ስለገለጠችልኝ ምን ማድረግ እንዳለብኝ እባክዎ ይምከሩኝ ።"

ማስታወሻውን አንዴ እንዳነበበው ወንበሩ ላይ ወደኋላ ተለጥጦ መልዕክቱ ሊያስከትል ስለሚችለው መዘዝ አውጠነጠነ ። እና ፣ ካተሪን አሌክሳንደር ከሞት ለመመለስ ትሻለች ። በጣም መጥፎ ነገር ። እርሷን ማስወገድ አለብኝ ። በጥንቃቄ ፣ በጣም ጥንቃቄ በተመላበት ዘዴ ።

የመጀመሪያው እርምጃ እርሷን ከገዳሙ ማስወጣት ነው ። ዴሚሪስ ሲስተር ተሬዛን መጐብኘት እንዳለበት ወሰነ ።

በሚቀጥለው ቀን ጠዋት ዴሚሪስ እየተሾፈረ ወደ ኢኦኒና አመራ ። ጎጠሩን አቋርጦ በሚጓዝበት ወቅት ከመኪናው ውስጥ ሆኖ ስለካተሪን ያስብ ነበር ። ድሮ በመጀመሪያ ሲያገኛት ምን ያህል ቆንጆ ሴት እንደነበረች አስታወሰ ። ብሩህ አዕምሮ የነበራት ተጫዋችና መንፈሰ ጠንካራ ልጅ መሆኗ ትዝ አለው ። ግሪክ ውስጥ በመሆኗም እንዴት እንደፈነደቀች አልረሳውም ። 'ዓለሟን አይታለች' ሲል አሰበ ። ከዚያ በኋላ አግልኩቱ በቀል ፈጸሙባት ። ካተሪን ከዴሚሪስ አውሮፕላን

አብራሪዎች አንዱን አግብታ ነበር ፤ ግን ትዳሯ ምድራዊ ሲኦል ሆነ ።
ባገባች በማግሥቱ አሥር ዓመት ዕድሜ የጨመረች ይመስል ወደለች ፤
ጠጪም ሆነች ። ዴሚሪስ ቁና ተነፈሰ ። 'አይ ክስረት!'
ቆሚሪስ ሲስተር ተሬዛ ቢሮ ውስጥ ተቀምጧል ።
"ስለዚህ ጉዳይ እርስዎን በማስጨነቄ አዝናለሁ" አሉ ሲስተር
ተሬዛ በትህትና ። "ሆኖም ልጅቷ መሄጃ የሌላት ስለሆነ ..."
"ደህና አድርገዋል" ሲል ዴሚሪስ አረጋጋቸው ። "ለመሆኑ
ስላለፈው ሁኔታዋ የምታስታውሰው ነገር አለ?"
ሲስተር ተሬዛ ጭንቅላታቸውን ነቀነቁ ። "የለም ። ምስኪን ..."
ብዙ መነኮሳት አትክልት ወደሚኰተኩቱበት በመስኮት አዩና "ያችው
ሎት ፤ እዚያ ናት" አሉ ።
ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ወደ እርሳቸው ተጠግቶ በመስኮት ወደውጭ
ተመለከተ ። ሦስት መነኰሳት ጀርባቸውን ሰጥተውታል ። ላፍታ ያህል
እንደቆመ አንደኛዋ ዞር ስትል ፊቷን አየ ። ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ አለ ።
በጣም ቆንጆ ነበረች ግን ያቺ ወፍራም ጐስቋላ ሴት የት ገባች?
"ከመካከል የቆመችዋ እርሷ ናት" አሉ ሲስተር ተሬዛ ።
"ልክ ነዎት" ሲል ዴሚሪስ ጭንቅላቱን አወዛወዘ ። የሲስተር
ተሬዛ ቃላት ራሳቸው ካላቸው እውቀት በላይ ትክክል ነበሩ ።
"ምን ላድርጋት አሁን?"
ጠንቀቅ! "እስቲ ላስብበት" አለ ዴሚሪስ ። "እንገናኛለን ።"
ኮንስታንቲን ዴሚሪስ አንድ የሚወስነው ነገር አለ ። የካተሪን
አሌክሳንደር መልክ እጅጉን አስገርሞታል ። እንዳለ ተቀይራለች ።
'መቼም ያቺ ሴት ናት ብሎ ለመጠራጠር የሚችል ማንም የለ' ሲል አሰበ።
አሳቡ መልሶ እራሱን አሳቀው ። ያን ዕለት ማታ ለሲስተር ተሬዛ
ማስታወሻ ጽፎ ላከላቸው ።

'ተአምር ነው' ስትል አሰበች ካተሪን ። 'ሕልሙ እውን ሲሆን!'
ሲስተር ተሬዛ ከትንሿ ጐጆአቸው ውስጥ ፀሎት አድርሰው ሲመለሱ ወደ
ካተሪን ጐራ አሉ ።
"ልጄ ሆይ ፤ አንድ የምነግርሽ ነገር አለ ።"
"ምን ነበር?"



ሲስተር ተሬዛ ቃላቶቻቸውን በጥንቃቄ በመምረጥ "የምሥራች! ለአንድ የገዳማችን ወዳጅ ስለአንቺ ሁኔታ ጽፌለት ሊረዳሽ ፈቃደኛ ሆኗል ።"

ካተሪን ልቧ በኃይል ሲመታ ተሰማት ። "ሊረዳኝ — እንዴት ?"

"እንዴት እንደሚረዳሽማ የሚነግርሽ እርሱ ነው ። ሰውዬው በጣም ደግና ሩህሩህ ሰው ነው ። ከገዳሙ መውጣትሽ ነው ።" የሰማቻቸው ቃላት በድንገተኛ ቅዝቃዜ ብርክ አስያዟት ። ልታስታው ሰው እንኳ ወዳልቻለችው እንግዳ ዓለም ልትገባ ነው ። ማን ይሆን ሊረዳት የተነሳሳው ሰው?

ሲስተር ተሬዛ "ለሰው የሚያስብ ሰው ነው ። ልታመሰግኚው ይገባል ። መኪናው ሰኞ ጠዋት እዚህ ድረስ ይመጣልሻል ።"

ለሚቀጥሉት ሁለት ቀናት እንቅልፍ በካተሪን ዓይን ላይ ዞር አልል አለ ። ከገዳሙ ወጥቶ ወደውጭው ዓለም የመሄዱ ነገር ሲታሰባት ያስፈራታል ። እርቃኗን ያለችና ያለቀላት መስሎ ተሰማት ። "ምንነቴን አለማወቁ ይሻለኝ ይሆን? እባክህ አምላኬ ጠብቀኝ ።"

ሰኞ ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ላይ ሊሞሲን መኪና ከገዳሙ ቅጥር ግቢ በር ላይ ቆመች ። ካተሪን ሌሊቱን ሳትተኛ ከፊቷ ስለተደቀነውና ስለማይታወቀው የወደፊት ሁኔታዋ ስታስብ ነበር ያነጋችው ።

ሲስተር ተሬዛ ካተሪንን ወደውጭ ዓለም እስከሚያስወጣው በር ድረስ ሸኟት ።

"እንፀልይልሻለን ። ልብ በይ ፤ ወደ እኛ ተመልሰሽ ለመምጣትም ከፈለግሽ በደስታ እንቀበልሻለን ።"

"አመሰግናለሁ ሲስተር ፤ አልረሳም ።" የካተሪን ልቦና ግን ተመልሳ እንደማትመጣ እርግጠኛ ነበር ። ካተሪን ፤ ከኢኦኒና እስከ አቴንስ በሚወስደው ረጅሙ መንገድ ስትጓዝ በተምታቱ አሳቦች ውስጥ ትዋኘ.ቃለች ። ከገዳሙ መውጣት ልዩ ስሜት ያሳደረባት ቢሆንም ውጪው ዓለም የሆነ መጥፎ ነገር እንዳለበት ይሰማታል ። ባለፈው ሕይወቷ ውስጥ ስለተፈጸመው አስቃቂ ነገር ትረዳ ይሆን? ሰው በህይቅ ውስጥ ሲያሰምጣት ያየችው ተደጋጋሚ ሕልም ከዚህ ጋር ግንኙነት ይኖረው ይሆን?

ገጠሩን ዘልቀው ትንንሽ መንደሮችን ካለፉ ከቀትር በኋላ ከአቴንስ ከተማ መግቢያ ላይ ደረሱ ። ቀጥለውም ውካታ ወደበዛበት ወደመሃል ከተማው ገቡ ። ነገሩ ሁሉ ለካተሪን እንግዳና ሕልም መስሎ ቢታያትም በሌላ በኩል ደግሞ ሥፍራውን የምታውቀው ይመስላታል ። 'ከዚህ ቀደም እዚህ ነበርኩ' ስትል በግርምታ አሰበች ።

ሾፌሩ ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ አመራ ። ከአሥራ አምስት ደቂቃ በኋላ በጋራ ላይ ወደሚገኝ ሰፊ ርስት ደረሱ ። ረዥሙን የአጥር ፣ የብረት በርና የዘበኛ ማደሪያ ቤት እንዳለፉ በሚያማምሩ ትላልቅ ዛፎች መሐል አቋርጠው በተዋቡ በርካታ ሀውልቶች ካጌጠ ነጭ የተንጣለለ የሜዲትራ ኒያን ቪላ ፊት ቆሙ ።

ሾፌሩ የመኪናውን በር እንደከፈተላት ካተሪን ወረደች ። ከዋናው በር ላይ ቆሞ ሰው ይጠብቃት ነበር ።

"ካሊሜራ" "እንደምን አደርክ" የሚል ቃል ከካተሪን አፍ ሳይታወቃት አፈተለከ ።

"ካሊሜራ"

"ወዳንተ..... ወዳንተ ነበር የተላኩሁት?"

"የለም ፣ አይደለሁም ። ሚስተር ዴሚሪስ በቤተ መጻሕፍት ውስጥ እየጠበቁሽ ነው ።"

"ዴሚሪስ!" ይህን ስም ከዚህ ቀደም ሰምታ አታውቅም ። ለምን ሊረዳት ፈለገ ግን!

ካተሪን የእልፍኝ አሽከሩን ተከትላ ወደ ሰፊው ክብ ሕንጻ ገባች ። የጣሪያው ጉልላት በውብ ጣውላ ያማረ ነው ። በጣሊያን እብነበረድ የተነጠፈው ወለል ያብረቀርቃል ።

ሳሎኑ ትልቅ ነው ። ጣሪያው ረዝሞ ወደመሬት የቀረቡ ምቹ ሶፋና ወንበሮች ክፍሉን ሞልተውታል ። ትልቅ ስዕል አንዱን ግድግዳ ሸፍኖታል ። ቤተ መጻሕፍቱጋ እንደደረሱ የእልፍኝ አሽከሩ ቆም አለ ።

"ሚስተር ዴሚሪስ እውስጥ እየጠበቁሽ ነው ።"

የመጻሕፍት ቤቱ ግድግዳ ነጭና ወርቅማ ቀለም ተቀብቷል ። ግድግዳውን ተጠግተው በሚገኙት መደርደሪያዎች ላይ ያሉት መጻሕ ፍት ሽፋን በቆዳ ተለብደው ርዕሳቸው በወርቅማ ቀለም ተጽፏል ። ከትልቅ ጠረጴዛ አጠገብ አንድ ሰው ተቀምጧል ። ካተሪን እንደገባች ቀና ብሎ አያትና ብድግ አለ ። የምታስታውሰው ነገር እንዳለ ለማወቅ ፊቷን



ለማንበብ ሞክሮ ነበር ፣ ግን ምንም አላገኘባትም ።

"እንኳን ደህና መጣሽ ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ እባላለሁ ። የአንቺስ ስም ማነው ?"

ጥያቄውን ያለምንም ሌላ ምክንያት የተሰነዘረ ለማስመሰል ሞከረ። 'ስሟን አስታውሳው ይሆን?'

"ካተሪን አሌክሳንደር ።"

የሰማው ያልጠበቀው በመሆኑ የስሜቱን ለውጥ ተቆጣጠረ ።

"ካተሪን አሌክሳንደር እንኳን ደህና መጣሽ ። እባክሽን ቁጭ በይ!"

ፊትለፊትዋ ካለው ጥቁር የቆዳ ሶፋ ላይ ተቀመጠ ። ከቅርብ ሆነው ሲያዩዋት ይበልጥ ታምራለች ። 'ውብ ፍጡር ናት' አለ በልቡ ። 'ደግሞ ያን ጥቁር የመነኩሳት ቀሚስ ነው የለበሰች ። ቆንጆን ማጥፋት ብልግና ነው ። ሌላው ቢቀር ደስተኛ ሆና ትሞታለች ።'

"ልት .... ልታነጋግረኝ በመፈለግህ በጣም ደስ ብሎኛል ።" አለች ካተሪን ። "ግን ለምን..."

ፈገግ አለ ። በቀላሉ ለመመለስ ያህል "እኔ ሲስተር ተሬዛን አልፎ አልፎ እረዳቸዋለሁ ። ገዳሙ የገንዘብ ችግር ስላለበት የአቅሜን ያህል እደጉማቸዋለሁ ። አንቺን መርዳት እችል እንደሆነ ጽፈው እንደጠየቁኝም ደስ ብሎኝ እንደምሞክር አሳውቅኳቸው ።"

"መቼም በጣም...." ምን ብላ እንደምትጨርስ ግራ ተጋብታ አቋረጠች ።

"ሲስተር ተሬዛ ነግረውሃል?...የማስታወስ ችሎታ እንደሌለኝ?"

"አዎ ፣ እንስተውልኝ ነበር መሰለኝ?"

ንግግሩን ቆም አድርጎ እንደገና "ምን ያህል ለማስታወስ ትችያለሽ ?" ብሎ ጠየቃት ።

"ስሜን አውቀዋለሁ ፣ ግን ከየት እንደመጣሁና ማን እንደሆንኩ ለይቼ አላውቅም ።" ተስፋ በተሞላበት አነጋገር "እዚህ አቴንስ ውስጥ የሚያውቀኝን ሰው አገኝ ይሆናል" አለች ።

በኮንስታንቲን ዴሚሪስ አእምሮ የማስጠንቀቂያ ደወል አንቃ ጨለ። ከምንም በላይ የፈለገው ይህን ነበር ። "አዎ ምናልባት ታገኚ ይሆናል" አለ በጥንቃቄ ። "ጠዋት ተገናኝተን ለምን አንወያይበትም ? እንዳጋጣሚ ሆኖ አሁን ስብሰባ አለብኝ ። የመኝታ ክፍል እንዲዘጋጅልሽ አድርጌአለሁ ። ምቾት እንደሚሰጥሽ ተስፋ አደርጋለሁ ።"

"ም...ምን ብዬ እንደማመሰግንዎት አላውቅም ።"

እጁን አወዛወዘና "አስፈላጊ አይደለም ። በሚገባ እንክብካቤ ይደረግልሻል ። ልክ እቤትሽ እንዳለሽ ቁጠሪው" አላት ።

"አመሰግናለሁ ፣ ሚስተር..."

"ወዳጆቼ ኮስታ ብለው ይጠሩኛል እና አንቱታውን ተይ ።"

የእልፍኝ አሽከሩ ካተሪንን ወደ ውቡ መኝታ ክፍል ወሰዳት ። ሰፊው አልጋ ውድ የሐር ልብስ ተጐናጽፎ ተዘርግቷል ። ምቾት ያላቸው ነጭ ሶፋዎች ፣ ወንበሮች ፣ ጥንታዊ ጠረጴዛዎችና የራስጌ መብራቶች ክፍሉን አሳምረውታል ። ግድግዳው በሥዕሎች አሸብርቋል ። ረዥሙ ባለውሃ ሰማያዊ ቀለም የመስኰት መስተዋት መሸፈኛ የፀሐይ ብርሃን ሙሉ በሙሉ ወደ ውስጥ እንዳይገባ ከልሎታል ። ካተሪን ፣ በመስኮቱ አቆልቁላ አረንጓዴ ሰማያዊውን ባሕር ከሩቅ ለማየት ትችላለች ።

የቤት ሠራተኛው "ሚስተር ዴሚሪስ ልብስ እንድትመርጪ የተለያዩ የልብስ ዓይነቶች ወደዚህ እንዲላኩ አዘዋል ፣ ደስ የሚልሽን እንድትመርጪ እንግዲህ ።"

ይሄኔ ነበር ካተሪን የመነኰሳት ልብስ መልበሷን ለመጀመሪያ ጊዜ ያወቀችው ።

"አመሰግናለሁ ።" በለስላሳው አልጋ ላይ ሰመጠች ። በሕልም ዓለም ውስጥ ያለች መስሎ ተሰማት ። 'ይሄ የማታውቂው ሰው ማን ይሆን ? ለምንስ እንዲህ ደግ ሆነልሽ ?'

ወዲያው ከአንድ ሰዓት በኋላ ልብስ የጫነ ትልቅ መኪና ከተፍ አለ። አንዲት የቤት ልብስ ሰፊም ወደካተሪን መኝታ ክፍል ተስተናገደች።

"ማዳም ዲማስ እባላለሁ ። እስቲ ልክሽን ልወቅ ። አንዴ ልብስሽን ታወልቂ ?"

"ምን...ምን አሉኝ ?"

"አንዴ ልብስሽን ታወልቂ ? ልብስ ለብሰሽ ልክሽን ለማወቅ ይቸግረኛል ።"



ከሰው ፊት ራቁቷን ከቆመች ምን ያህል ጊዜ ሆኗት ይሆን?

ካተሪን ዝግ ብላ እያስተዋለች ማውለቅ ጀመረች ። ከሴትዮዋ ፊት እርቃኗን እንደቆመች ማዳም ዲማስ በሰለጠነው ዓይኗ ከላይ እስከታች ቃኘቻት ። በቁመናዋ ተደነቀች ።

"ጥሩ ቅርጽ ነው ያለሽ ፣ ጥሩ ነገር ልናዘጋጅልሽ እንችላለን ።"

ሁለት ሴት ረዳቶቿ ሙታንታዎችን ፣ ሸሚዞችን ፣ ረዥምና ጉርድ ቀሚሶችንና ጫማዎችን የያዙ ሻንጣዎችን አንጠልጥለው ገቡ ።

"የምትፈልጊውን ምረጪ" አለቻት ልብስ ሰፊዋ ። "ሁሉንም ለብሰሽ ሞክሪያቸው"

ከእ... ከእነዚህ ውስጥ አንዱንም መግዛት የሚያስችል አቅም የለኝም" ብላ በፍርሃት ተናገረች ። "ገንዘብ የለኝም ።"

ሰፊዋ ሳቀች ። "የገንዘብ ችግር የለም ። ሚስተር ዴሚሪስ ኃላፊነቱን ይወስዳሉ ።"

'ግን ለምን ? ...' ብላ አሰበች ።

ልብሶቹን ስታይ ድሮ ለብሳቸው የነበሩት ልብሶች ትዝ አሏት ። የተለያዩ ውብ ቀለማት ካሏቸው የሐር ፣ የጥጥና የሱፍ ጨርቅ የተሰፉ ናቸው ።

ሦስቱ ሴቶች በጣም ፈጣኖች ስለነበሩ ከሁለት ሰዓታት በኋላ ካተሪን በርከት ያሉ ማራኪ ልብሶች ልትመርጥ ችላለች ። የምታደርገው ግራ ገብቷት እዚያው ቁጭ ብላ ቀረች ።

'እንግዲህ ለባብሻለሁ ።' አለች በልቧ ። 'ለመሆኑ ግን ምን መሄጃ ቦታ አለ?' ግን እኰ የሚኬድበት አለ ፤ ወደ መሐል ከተማ ። ባለፈው ጊዜ ለተፈፀመባት እንቆቅልሽ መፍቻ ቁልፉ ያለው አቴንስ ውስጥ ነው ። ይህንን አምና ተቀብላለች ። ተነስታ ቆመች። 'አይዞሽ አንቺ እንግዳ ፍጡር ማንነትሽን ለማወቅ እንጥራለን ።'

ካተሪን ወደ አዳራሹ ብቅ እንዳለች የልፍኝ አገልጋዩ ወደ እርሷ ቀርቦ "ምን ልርዳዎ እመቤቴ?" አለ ።

"እ ... ወደ ከተማ ለመሄድ እፈልጋለሁ ። ታክሲ ልትጠራልኝ ትችላለህ?"

"ታክሲ መጥራት ምን ያስፈልጋል? ባስፈለግዎት ጊዜ እንዲጠቀ

ሙበት ሊሞሲን ተዘጋጅቷል ። ሾፌር አዘጋጅልዎታለሁ ።”

ካተሪን አቅማማችና “አመሰግናለሁ” አለች ። ወደከተማ ብትሄድ ሚስተር ዴሚሪስ ይናደድ ይሆን ? አትሂድ አላለ ።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ከሽንጣሙ ሊሞሲን የኋላ መቀመጫ ተቀምጣ ወደ አቴንስ እምብርት ተጓዘች ። ካተሪን ባየቻቸው የጥንት የሕንፃና የሀውልት ፍርስራሾች እንዲሁም በከተማው ግርግርና ሁካታ ተደነቀች ።

ሾፌሩ በኩራት መንፈስ ጣቱን ቀስሮ “ ያ በአክሮፖሊስ ጫፍ ላይ የታነፀው የፖርቴኖን መቅደስ ነው” አላት ።

ካተሪን በነጭ እብነበረድ የተሠራውን ድንቅ ሕንፃ ተመለከተች ። “ለጥበብ አምላክ ለአቴና የተሠራ መቅደስ” ስትል ለእራሷ ተናገረች ።

ሾፌሩ የአባባሏን ትክክለኝነት ለመግለጽ ፈገግ አለ ። “ሚስስ ፣ የግሪክ ታሪክ ተማሪ ነሽ?” ።

የስጋት እንባ በዓይኗ አቀረረ ። “እኔ እንጃ” አለች በለሆሳስ ፣ “እኔ እንጃ ።”

ከሌላ ፍርስራሽ አጠገብ ሲያልፉ “ያ የሄሮደስ አቲክስ ትያትር ነው። እንደምታዩው የቤቱ ክፊል ግድግዳ አሁንም አልፈረሰም ። በአንድ ወቅት ትያትሩ በአንዴ ከአምስት ሺህ ተመልካቾች በላይ ያስተናግድ ነበር” አላት ።

“ስድስት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሳ ሰባት” አለች ካተሪን ቀበል አድርጋ ። በፍርስራሹ መሐል ዘመናዊ የሆቴልና የቢሮ ሕንፃዎች ተቀላቅለው በየቦታው ይታያሉ ። የጥንቱና የዛሬ ድብልቅ ። ሊሞሲኗ በከተማዋ እምብርት ካለው መናፈሻ መሃል እየጋለበችና እየተብረቀረቀች ወደላይ ከሚፈሰው ሰው ሰራሽ ፏፏቴ አጠገብ አለፈች ። በመናፈሻው ውስጥ በርከት ያሉ አረንጓዴና ብርቱካንማ ቀለም ያላቸው ጠረጴዛዎች ተደርድረዋል ። ሰማያዊ ቀለም ያለው ድንኳንም ተጥሏል ።

‘ይህንን ቦታ ቀደም ሲል አይቼዋለሁ’ አለች ካተሪን በልቧ ፣ እጇ ሲቀዘቅዝ እየተሰማት ። ‘አስደስቶኝም ነበር ።’

በመስክ ላይ ምግብና መጠጥ የሚሸጡ ትንንሽ መደብሮች በሁሉም ሕንፃዎች ላይ አሉ ለማለት ይቻላል ። በየጥግና ጥጉ ትኩስ ሰፍነጎች ይሸጣሉ ። ሐምራዊ ቀለም የተቀቡ የአበባ መሸጫ ሱቆች ገበያ ደርቷል ።

ሊሞሲኗ ከሲንታግማ አደባባይ ደረሰች ።



ከጥግ ላይ ከሚገኝ ሆቴል አጠገብ ሲያልፉ ካተሪን “እባክህ አቁምልኝ!” አለች ።

ሾፌሩ መኪናዋን ወደመንገዱ ጠርዝ አስጠጋ ። ካተሪን መተንፈስ አቃታት ። ‘ይህንን ሆቴል አስታውሰዋለሁ ፤ አድሬበታለሁ’ አለች በልቧ።

ስትናገር ድምጿ ይንቀጠቀጥ ነበር ። “እዚህ መውረድ እፈልጋለሁ፤ ከሁለት ሰዓት በኋላ ተመልሰህ መጥተህ ብትወስደኝ ደስ ይለኛል ።”

“በደስታ !” ሾፌሩ ፈጥኖ በሩን እንደከፈተላት ካተሪን ወደ ሞቃቱ የበጋ አየር ወጣ አለች ። እግሯ ይንቀጠቀጣል ። “ሚስስ ፣ ምን ሆንሽ?” መልስ አልነበራትም ። ከገደል ጫፍ ቁልቁል ተምዘግዝጋ ከማታውቀው ነዳይ መሬት ልትፈጠፈጥ የተቃረበች መስሎ ተሰማት ።

በተጨናነቀው ሕዝብ ግፊያና ጫጫታ መሃል እየተሽሎከሎከች መራመድ ጀመረች ። በሴቶቹ ገዳም ውስጥ ካየችው ፀጥታና መገለል አኳያ አሁን ያጋጠማት ቅዠት መሰላት ። እግሯ ወደመራት ስትጓዝ በአቴንስ እንብርት ከምትገኘው ፕላክ ከተባለች ያረጀች የከተማ ክፍል ደረሰች ። የከተማዋ መንገዶች ጠባብ ፣ ጠመዝማዛና የተሸረሸሩ ናቸው ። ወደታች የሚወስደው ደረጃ ነጭ ቀለም ወደተቀቡና ያለፕላን ወደታነፁ ሻይ ቤቶችና ቡና ቤቶች የሚወስድ ሲሆን ወደዚህም ለመሄድ የግድ በአረጁ መሰላል ቢጤ ደረጃዎች ማለፍ ያስፈልጋል ። በማታውቀውና ልትቆጣጠረው በማትችለው ደመነፍሷ እየተመራች መንገዷን አገኘች ። ከተማውን ቁልቁል ለማየት ከሚቻልበት የመዝናኛ ሥገነት አጠገብ እንደደረሰች ቆም ብላ በአትኩሮት ተመለከተች ። ‘እዚያ ወንበር ላይ ተቀምጬ ነበር ። በግሪክ ቋንቋ የተጻፈ የምግብና የመጠጥ ዝርዝር አቅርበውልኛል ። ሦስት ሰዎች ነበርን ።’

‘ምን ትበያለሽ?’ ብለው ጠየቁኝና ‘መልሼም እናንተ ብታዙልኝስ ? ለምግቡ እንግዳ ስለሆንኩ የማይሆን ምግብ እንዳላዝ ብዬ ነው !’ አልኳቸው ። ‘ሣቁ ። ግን እነማን ነበሩ?’

አስተናጋጁ ወደካተሪን ጠጋ አለ ። በግሪክኛ ‘ምን ልታዘዝ?’ ሲለኝ እኔም በግሪክኛ መልሼ ‘አመሰግናለሁ ምንም አልፈልግም’ አልኩ ። ቋንቋውን እንዴት ማወቅ ቻልኩ ? ግሪካዊ ነኝን?

ካተሪን የከተማውን አስጎብኚ እንደሚከተል ሰው በፍጥነት ስትጓዝ ወዴት እንደምትሄድ የምታውቅ ትመስል ነበር ።

ያየችው ሁሉ የምታውቀው ሆነባት ። በሌላ በኩል ደግሞ ድፍንፍን አለባት ። ‘አምላኬ!’ አለች በልቧ ። ‘አእምሮዬን ስቻለሁ መሰለኝ! እየቃዠሁ ነው ።’

“ትሬፍሊንካስ” የሚል ፅሑፍ ከተለጠፈበት ቡና ቤት አጠገብ አለፈች ። ከእንጕልዋ ጥግ ትውስታዎች ብቅ ብቅ ማለት ጀመሩ ። እዚህ ቦታ አንዳች ነገር ተፈጽሞባታል ፤ ከባድ ነገር ። ግን ምንነቱን ለማስታወስ አልተቻላትም ።

ሰው በሚበዛበት በጠመዝማዛው ጐዳና ተጉዛ ቮኩሬስቱ ከተባለው ሥፍራ ስትደርስ ወደግራ ታጠፈች ። ብዙ የሚያማምሩ ሱቆች አየች ። ‘ከእነኚህ ሱቆች ዕቃዎችን ሸምቼ ነበር’ አለች በልቧ ። መንገዱን ስታቋርጥ ሰማያዊ ሴዳን መኪናም ሊገጫት ሲል ለጥቂት ተረፈች ። ‘ግሪኮች ገና

በአንድ ወቅት የሰማችው ድምፅ እንቃጨለባት ።

ወደአውቶሞቢል ዘመን አልደረሱም ። አሁንም በልባቸው አሀያ ነጂ ናቸው ። ስለ ግሪኮች ውስጠ ሕይወት ለማወቅ ከፈለግሽ የዘመኑን የሀገሪቱን ታሪክ ሳይሆን ጥንታዊውን የግሪክ ታሪክ አንብቢ ። እኛ በጥልቅ የፍቅር ስሜት ፤ በታላቅ ደስታና ሀዘን የተሞላን ነን ። ከዘመናዊው ሥልጣኔ ጋር እነኝህን እንዴት ልናዋህዳቸው እንደምንችል ገና አልተረዳንም ።’

ማነው እንዲህ ያላት?

አንድ ሰው አተኩሮ እየተመለከታት በፍጥነት ወደሷ ገሰገሰ ። አጠገቧ እንደደረሰ ቀስ አለ ። እንዳስተዋላት ከፊቱ ይነበባል ። ሰውዬው ረዥም ጠየም ያለ ነው ። ካተሪን ከዚህ ቀደም አይታው እንደማታውቅ እርግጠኛ ነበረች ። ቢሆንም…

“ሰላም” እሷን በማየቱ የተደሰተ ይመስላል ።

“በረዥሙ ወደውስጥ ተነፈሰች ። “እንተዋወቃለን?”

ሳቅ አለ “በሚገባ ።”

ካተሪን ልቧ በኃይል ሲመታ ተሰማት ። ያለውን እውነታ በመጨረሻ ልታውቀው ነው ። ግን “እኔ ማን ነኝ?” ብሎ ሕዝብ በመላበት ጐዳና ላይ ያገኙትን እንግዳ እንዴት መጠየቅ ይቻላል ።

“ለመ … ለመነጋገር እንችላለን?” ብላ ጠየቀች ካተሪን ።



“የሚሻል ይመስለኛል ።”

ካተሪን ተርበተበተች ። የተደበቀው የማንነቷ ምስጢር ይፋ ሊወጣ በመሆኑ ፍርሃት ፍርሃት አላት ። ‘ማወቁ ቢቀርብኝስ? ከዚህ ቀደም ክፉ ነገር ፈፅሜ እንደሆነስ ?’

ሰውዬው ሜዳ ላይ ወደሚስተናገዱበት ሆቴል ይዟት ሄደ ። “በአጋጣሚ በመገናኘታችን ደስ ብሎኛል” አላት ።

ካተሪን ምራቋን ዋጠችና “እኔም ደስ ብሎኛል” ብላ መለሰች ። የሆቴሉ አስተናጋጅ መቀመጫ ሰጣቸው ።

“ምን ለመጠጣት ትፈልጊያለሽ?” ሲል ሰውዬው ጠየቃት ።

ጭንቅላቷን ነቀነቀች ። “ምንም!”

የሚጠየቁ ብዙ ጥያቄዎች አሏት ። ከየት ይጀመር?

“በጣም ቆንጆ ነሽ” አላት ሰውዬው “የዕድል ነገር አያስገርምም?”

“በጣም እንጂ” ግራ በመጋባቷ ልትንቀጠቀጥ ምንም አልቀራትም። አየር ወደ ውስጥ በኃይል ሳበች ። “እ… ከዚህ ቀደም የት ነበር የተገናኘነው?”

ፈገግ አለ ። ‘ጥያቄው አስፈላጊ ነው? የኔ ፍቅር ። ፓሪስ ወይንም ሮም ውስጥ በውድድር ሥፍራዎች ወይም በፓርቲ ላይ’ እጁን ዘርግቶ እጇን ተጫናት ። “በዚህ አካባቢ ካየናቸው ሴቶች መካከል አንቺ በጣም ማራኪ ነሽ ። ስንት ነው የምታስከፍይው?”

ካተሪን ምን ማለቱ እንደሆነ ስላልገባት ትኩር ብላ አየችው ። ወዲያው ደንግጣ ብድግ አለች ።

“እንዴ ፤ ምን ነካሽ? የጠየቅሺውን ያክል እከፍ…”

ካተሪን ዞር ብላ ወደመንገዱ ሮጠች ። ከሰዋራ ሥፍራም እንደደረሰች ዝግ አለች ። የተዋረደች ስለመሰላት ዓይኗ እንባ አቀረረ ።

ከፊትለፊቷ ከምታየው ሕንፃ መስኮት ላይ “ማዳም ፒሪስ — ኮከብ ቆጣሪ” የሚል ጽሑፍ አነበበች ። ካተሪን በመጀመሪያ እርምጃዋን ቀነሰች ፣ ከዚያም ቆመች ። ‘ማዳም ፒሪስን አውቃታለሁ ። ከዚህ ቀደም እዚህ ቦታ መጥቼ ነበር ።’ የልብ ትርታዋ ከፍ አለ ። እስካሁን ተሰውሮባት የቆየው ምስጢሯ ገሀድ የሚወጣው ድንግዝግዝ ካለው የቤቱ መግቢያ በር እንዳለፈች መሆኑን ተሰማት ። በሩን ከፍታ ወደ ውስጥ ገባች። ቤቱ በድቅድቅ ጨለማ በመዋጡ እውስጥ ያለውን ነገር ለማየት ጥቂት ጊዜ ፈጀባት ። ከዚህ በፊት ያየችው የሚመስላት ባንኮኒ ፣

ወንበሮችና ጠረጴዛዎችም ከጥግ ይታያሉ ። አስተናጋጁ ወደ እርሷ ተጠጋና በግሪክኛ ጥያቄ አቀረበላት ።

"ካሊሜራ"

"ካሊሜራ ፓው ኢነ ማዳም ፒሪስ?"

"ማዳም ፒሪስ?"

አስተናጋጁ በጥግ በኩል ያለ አንድ ባዶ ወንበር ሲያሳያት ካተሪን ሄዳ ተቀመጠች ። አኳኋኑን ሁሉ አስታወሰች ።

ፊቷ የተጨማደደ አሮጊት ጥቁር ልብስ ለብሳ ወደ ካተሪን ቀረበች ።

"ምን ልር...?" አቋርጣ በትኩረት የካተሪንን ፊት ተመለከተች ። ዓይኗ ተበለጠጠ ። "ከዚህ ቀደም ያየሁሽ ይመስለኛል ። ግን ፊትሽ..." ብላ ቁና ቁና ተነፈሰች ። "ተመልሰሽ መጣሽ!"

"ማን እንደሆንኩ ታውቂያለሽ?" አለች ካተሪን በጉጉት እየ ጠየቀች ።

አሮጊቷ አፍጥጣ በቁጣ "አላውቅም ። አንቺ ሞተሻል ፤ ውጪ ከዚህ!"

ካተሪንን እንደመዘረር ሞከራት ። ፀጉሯ ሲቆም ተሰማት ። "እባክሽ። እኔ እንዲሁ..."

"ውጪ ፡ ሚስስ ዶግላስ!"

"የግድ ማወቅ..."

አሮጊቷ አማተበችና ዞር ብላ እልም አለች ።

ካተሪን እየተንቀጠቀጠች ለትንሽ ጊዜ እዚያው ተቀምጣ ቆየችና በጥድፊያ ወደመንገድ ወጣች ። በጭንቅላቷ ውስጥ ያለውም ቃል ተከተላት ። "ሚስስ ዶግላስ!"

የጐርፍ ቆካ የተከፈተ ያህል ነበር ። በርካታ ትዕይንቶች ፣ የተያያዙ ሥዕላዊ ድርጊቶች ወደ አንጐሏ እየተከታተሉ ፈሰሱ ። 'ሚስስ ላሪ ዶግላስ ነኝ ።' የባልዋ ቀና መልክ ታያት ። በጣም ታፈቅረው ነበር ፤ ግን አንድ ችግር ሳይፈጠር አልቀረም ። አንድ ችግር...።

ቀጥሎ የመጣባት እይታ የእራሷ ነበር ። ሕይወቷን ለማጥፋት ሙከራ ካደረገች በኋላ በሆስፒታል ውስጥ መንቃቷ ።

ካተሪን እግሯ የማይሸከማት ስለመሰላት ፈርታ ከመሃል መንገድ ላይ ቆመች ። የተለያዩ ሥዕሎች በአእምሮዋ ውስጥ መሳሉን ቀጠሉ ።

ላሪ ከሷ በመለየቱ ብዙ መጠጥ ትጠጣ ነበር ። በኋላ ግን ተመልሶ



መጣላት ። በአፓርትመንታቸው ውስጥ እንዳሉ ላሪ "እንዳስቀየምኩሽ አውቃለሁ ። እንደገና ጠባዬን ለማሻሻል እፈልጋለሁ ካቲ አፈቅርሻለሁ ። ካንቺ በቀር ሌላ ሴት ወድጄ አላውቅም ። ሌላ ዕድል እንድትሰጪኝ እፈልጋለሁ ። በድጋሚ የጫጉላ ጊዜ እንዲኖረን ወደ ሌላ ሥፍራ ብንሄድ ምን ይመስልሻል? ኢኦኒና የተባለች በጣም ውብ የሆነች ትንሽ ከተማ አውቃለሁ" ብሏት ነበር ።

ቢቃ! ሽብር ጀመራት ።

አሁን ወደ አእምሮዋ የመጣው ትውስታ በጣም ያስፈራል ።

ከላሪ ጋር ተራራ ጫፍ ላይ ነበሩ ። ተጥመልማዩ ግራጫማው ጉም ምንም አያሳይም ። ባልዋ ከተራራው ጫፍ አሽቀንጥሮ ሊጥላት ሲል አካባቢውን ይጐበኙ የነበሩ ቱሪስቶች ደርሰው አተረፏት ።

ከዚያ በኋላ ዋሻዎቹ ።

'የሆቴሉ ፀሐፊ በዚህ አካባቢ ስላሉት ዋሻዎች አጫውቶኛል ። ሰዎች የጫጉላ ጊዜያቸውን ለማሳለፍ ወደዚያው እንደሚሄዱ ነግሮኛል ።'

አብረው ወደዚያው ተጓዙ እና ላሪ ወደዋሻው አስገብቷት እንድት ሞት እዚያው ጥሏት ተመለሰ ።

አስፈሪ የሆኑትንና በፍጥነት ነስግሰው በመምጣት አእምሮዋን ማስጨነቅ የጀመሩትን አሳቦች መግታት ትችል ይመስል በሁለት እጇቿ ጆሮዋን ሸፈነች ።

ከተጣለችበት ሥፍራ አንስተዋት ወደሆቴሉ እንደተወሰደች ሐኪሙ የእንቅልፍ መድኃኒት ሰጣት ። እኩለ ሌሊት ላይ ከእንቅልፏ ስትነቃ ላሪና እቁባቱ ማድቤቱ ውስጥ ሆነው ሊገድሏት እቅድ ሲነድፉ በጆሮዋ ሽው አላት ።

— መቼም ማንም ሰው

— እኔ እፈጽመዋለሁ ብየሻለሁ

— ተበላሸ ። ማድረግ የሚችሉት ምንም ነገር የለም

— አሁን ፣ እንቅልፍ ወስዷት እያለ።

በዚያ አስፈሪ አውሎ ነፋስ አዘል ዝናብ ውስጥ ሮጣ መውጣቷን አስታወሰች ። እነርሱም ተከትለዋት ተቀዛፊ ጀልባ ላይ ወጣች ። ነፋሱ ጀልባዋን ወደ ተናወጠው የባሕሩ ማዕበል ገፋው ፤ ጀልባዋ መስጠም ጀመረች ። ከዚያም በኋላ ሕሊናዋን ሳተች ።

ካተሪን መሄድ ተስናት መንገድ ዳር በተቀመጠው አግዳሚ ወንበር

ላይ ዘፍ አለች ። እንዲህ ከሆነ ቅዠት አልነበረም ማለት ነው ። በእርግጥ ባለቤቷና ዕቁባቱ ሊገድሏት ነበር ።

ከተጣለችበት ተገኝታ ወደ ገዳሙ እንደተወሰደች ሊጐበኛት ወዲያውኑ ስለመጣው እንግዳ ሰው እንደገና አሰበች ። ሰውዬው ልትበር የተዘጋጀች የወርቅማ ወፍ ልዩ አርማ ሰጥቷታል ። “ከእንግዲህ ማንም ሰው አይጐዳሽም ። ጠላቶችሽ ሞተዋል” አሁንም ፊቱን በግልጽ ልታየው አልቻለችም ።

ካተሪን ዞረባት ።

ከዚያም እንደምንም ከተቀመጠችበት ተነሳች ። ጥበቃና እንክብካቤ ወደሚያደርግላት ወደ ዴሚሪስ ሊመልሳት በመጠባበቅ ላይ ወዳለው ሹፌር በዝግታ አመራች ።



# ምዕራፍ አራት

“ከቤት እንድትወጣ ለምን ፈቀዳችሁላት” ብሎ ጠየቀ ኮንስታን ቲን ዴሚሪስ ።

“ጌታዬ ይቅርታ” አለ የእልፍኝ አሽከሩ ። “እንዳትወጣ ብለው አላስጠነቀቁንም ። በዚህ ምክንያት...”

ዴሚሪስ መቆጣቱ እንዳይታወቅ ስሜቱን ተቆጣጠረ ። “ግድ የለም፤ ቶሎ ትመለስ ይሆናል ።”

“ሌላ የምታዘዘው አለ ጌታዬ?”

“የለም ።”

አሽከሩ ተመልሶ ሲሄድ ዴሚሪስ በዓይኑ ተከተለው ። ከዚያም ወደ መስኮቱ ሄዶ በእንክብካቤ የተያዘውን አትክልት አሻግሮ ተመለከተ ። ‘አይቶ የሚያስታውሳት ሰው ሊኖር በሚችልበት የአቴንስ ጐዳናዎች ላይ መታየት ለካተሪን አሌክሳንደር አደገኛ ነው ። በሕይወት እንድትኖር ዝም ብዬ ልተዋት ባለመቻሌ አዝናለሁ ። በቅድሚያ ግን — በቀሌ ። እስከበቀላት በሕይወት ትቆያለች ። ማንም ሰው ሊያውቃት ወደማይችል ሥፍራ እልካታለሁ ። ለክትትል ለንደን ምቹ ቦታ ነው ። እዚያ ቢሮዬ ውስጥ ሥራ እሰጣታለሁ ።’

ካተሪን ፡ ከአንድ ሰዓት ቆይታ በኋላ ወደቤቱ ስትመለስ ኮንስታን ቲን ዴሚሪስ እፊቷ ላይ ለውጥ መኖሩን ለማንበብ ችሏል ። ካተሪን ጥቁር መጋረጃ ተገልጦላት በድንገት ነፍስ የዘራች ያክል ነበር የተሰማት ። ከሐር የተሠራ የሚያምር ሙሉ ልብስ ለብሳለች ። ዴሚሪስ ቅርጿ ምን ያህል እንደተለወጠ ተገነዘበ ። ‘ቅንዝረኛ!’ አለ በልቡ ።

“ሚስተር ዴሚሪስ...”

“አቤት”

“እኔ... እኔ ማን እንደሆንኩ አውቄአለሁ ። እና.. እና ምን እንደተፈጸመብኝ ተረድቻለሁ ።”

ከፊቱ ላይ ምንም ነገር አይነበብም ። “እውነት? እስቲ ቁጭ በይና

ንገሪኝ ወዳጄ ።”

ካተሪን ስሜቷ ተቀስቅሶ ስለነበረ ለመቀመጥ አልቻለችም ። ብርክ እንደያዛት በምንጣፉ ላይ ከወዲያ ወዲህ እያለች “ባለቤቴና እቁባቱ ፣ ኖኤሌ ሊገድሉኝ ሞክረው ነበር” አለች ። ቆም ብላ በጉጉት ዓይን ዓይኑን አየች ። “ዘባርቄ ይሆን? እ... እኔ እንጃ ምናልባት ሊሆን ይችላል።”

“ቀጥይ ወዳጄ” አለ በለሆሳስ ።

“በገዳሙ የሚገኙ መነኮሳት ናቸው ሕይወቴን ያተረፉት ። ባለቤቴ ለአንተ ተቀጥሮ ይሠራ ነበር አይደል?” ብላ እቅጩን አፈረጠች ።

ዴሚሪስ እያመነታ የሚናገራቸውን ቃላት በጥንቃቄ መረጠና “እሺ” አለ ። ምን ያህል ይንገራት? “ከአውሮፕላኖቼ ነጂዎች አንዱ ነበር። ስለአንቺም ኃላፊነት ተሰማኝ ። ብቻ ...”

ቅጭም አለች ። “ግን ማን እንደሆንኩ እያወክ ዛሬ ጠዋት ፣ እንዴት ሳትነግረኝ ቀረህ?”

“ትደነግጪያለሽ ብዬ ስለሰጋሁ ነው” አለ ዴሚሪስ በለሰለሰ አነጋገር ።“አንቺ እራስሽ ብትደርሺበት ይሻላል ብዬ በማሰብም ነው።”

“ባሌስ ምን ሆነ? ያቺ...ያቺ ሴትስ? የት ነው ያሉት?”

ዴሚሪስ የካተሪንን ዓይኖች በትኩረት ተመለከተ ። “ተገደሉ ።”

ፊቷ ደም መስሎ ሲቀላ ተመለከታት ። ትንሽ ድምፅ አሰማች ። ከመቀጽበት ተዝለፈለፈችና መቆም አቅቷት ወንበር ላይ ዘፍ አለች ።

“መንግሥት ነው የረሸናቸው ካተሪን ።”

“ግን ... ለምን?”

ጥንቃቄ ። አደጋ ። “ሊገድሉሽ ስለሞከሩ ።”

ካተሪን ግንባሯን ቋጠረች ። “አልገባኝም ። መንግሥት የሚገድላቸው ለምንድነው? እኔ በሕይወት አለሁ!...”

አቋረጣት ። “ካተሪን ፣ የግሪክ ሕግ በጣም ጥብቅ ነው ። እዚህ አገር ፍትሕ ወዲያው ይገኛል ። በግልጽ ችሎት ለፍርድ ቀርበው ነው የተወሰነባቸው ። ባለቤትሽና ኖኤሌ ፖጂ ሊገድሉሽ መሞከራቸውን ብዙ ሰው ስለመሰከረባቸው ወንጀላቸው ተረጋግጦ ነው ሞት የተፈረደባቸው።”

“ለማመን ያስቸግራል” አለችና ካተሪን ከተቀመጠችበት ፈዛ ቀረች ። “ነገሩ በፍርድ ቤት የታየው...”

ኮንስታንቲን ወደእርሷ ሄደና እጁን ትከሻዋ ላይ ጣል አደረገ ። “ያለፈውን ከአእምሮሽ ማውጣት አለብሽ ። ክፉና አስቃቂ ነገር ሊፈጽሙብሽ ሞክረው ነው ዋጋቸውን ያገኙት ።” የእርካታ በሚመስል አነጋገር “አንቺና እኔ ስለወደፊቱ መወያየት ያለብን ይመስለኛል ። እቅዶች አሉሽ?”

ያለውን አልሰማችውም ። ‘ላሪ’ አለች በአሳቧ ። ‘የላሪ ፊት ቆንጆ ነው ፣ ሳቂታ ፣ የላሪ ክንዶች ፣ ድምጹም...’

“ካተሪን” አላት ።

ቀና ብላ ተመለከተችው “ይቅርታ”

“ስለወደፊቱ ኑሮሽ አስበሽ ታውቂያለሽ?”

“አላውቅም ...ምን እንደማደርግ የማውቀው ነገር የለም ። አቴንስ ውስጥ የምቆይ ይመስለኛል ።”

“አይሆንም” አለ ዴሚሪስ ጠንከር ባለ አነጋገር ። “ይሄ ጥሩ አሳብ ሊሆን አይችልም ። ደስ የማያሰኙ ትውስታዎችን ሊያመጣብሽ ይችላል ። ግሪክን እንድትለቂ አሳብ አቀርባለሁ ።”

“ግንኮ መሄጃ የለኝም ።”

“ግድየለም እኔ አስቤበታለሁ” አላት ዴሚሪስ ። “ለንደን ውስጥ ቢሮ አለኝ ። በነገራችን ላይ በአንድ ወቅት ዊሊያም ፍሬዘር ከተባለ ሰው ጋር ዋሽንግተን ውስጥ ሠርተሽ እንደነበረ ታስታውሽዋለሽ?”

“ዊሊያም ...?” ወዲያው አስታወሰችው ። ያ ወቅት በሕይወቷ ውስጥ ካጋጠማት አስደሳች ጊዜያቶች መካከል አንዱ ነበር ።

“እንደመሰለኝ የአስተዳደር ረዳቱ ነበርሽ ።”

“አዎ እኔ...”

“በለንደንም ተመሳሳይ ተግባር ልታከናውኚልኝ ትችያለሽ ።”

አመነታች ። “እኔ እንጃ ፣ ብድር መላሽ ላለመሆን አይደለም ግን...”

“ይገባኛል ። ትንሽ ፈጠንኩብሽ መሰለኝ?” አላት ዴሚሪስ አባባሏን የደገፈ በመምሰል ። “ስለዚህ ለማሰብ ትንሽ ጊዜ ያስፈልግሻል። በክፍልሽ ውስጥ ጥሩ እራት ተመግበሽ ለምን ስለዝርዝር ሁኔታው ጠዋት አንወያይም?”

በክፍሏ ውስጥ እራት እንድትመገብ የመጠየቁ ነገር በመጨረሻ ላይ የተከሰተለት አሳብ ነው ። ሚስቱ እንድታየው ጨርሶ አልፈለገም ።

“በጣም አሳቢ ነህ” አለችው ካተሪን ።

‘በጣም ደግ ሰው ፣ ልብሶቹም ...’

እጇን መታ መታ አደረገና ለትንሽ ጊዜ ያዝ አድርጓት ቆየ ። "ለራሴ ደስታ ብዬ ነው ።"

መኝታ ቤቷ ውስጥ እንዳለች ጠራራ የነበረችው ፀሐይ አንፀባራቂ ቀለም እየሰጠች በሰማያዊው ባሕር ላይ መጥለቅ መቃረቧን የሚያሳይ ምልክት ስትፈነጥቅ ተመለከተች ። ያለፈውን ማስታወሱ ዋጋ የለውም ። ማሰብ የሚገባው ለወደፊቱ ነው ። 'ኮንስታንቲን ዴሚሪስን ስለሰጠኝ እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ ።' ሕይወቷ የተንጠላጠለው በእርሱ ላይ ነው ። እርሱን ባታገኝ የምትሄድበት ምንም አማራጭ አልነበራትም ። ለንደን ውስጥ ሥራ ሰጥቷታል ። 'ሥራውን ልቀበለው ነው?' በሩ እንደተንኳኳ ሃሳቧ ተቋረጠ ። "እራትሽን አምጥተናል ሚስ ።"

ካተሪን ከሄደች በኋላ ሁለቱም ስላደረጉት ውይይት ኮንስታንቲን ዴሚሪስ በቤተ መጻሕፍቱ ውስጥ ለረዥም ጊዜ ተቀምጦ አስቧል ። ኖኤል ። ዴሚሪስ በሕይወቱ ውስጥ አንዷ ብቻ ስሜቱን መቆጣጠር ተስኖት ነበር ። በኖኤሌ ፓጂ ፍቅር ክፉኛ ተጠምዶ ቅምጡ አድርጓት ነበር ። እንደ እርሷ ዓይነት ሴትም አጋጥሞት አያውቅም ። ስለ ኪነጥበብ፣ ስለሙዚቃና ስለንግድ ሥራ በደንብ አድርጋ የምታውቅ ሲሆን የሚስተካከላት ሰው ከቶ አልነበረም ። ስለኖኤሌ አንድ ለብቻው ተመዝዞ የሚደነቅ ነገር ለማውጣት ይከብደው ነበር ። ሁሌ ነገሯ የሚያጓጓና የሚያስደንቀውም ነበር ። ከማንኛውም ነገር አስበልጦ ያፈቅራታል ። እስካሁን ካጋጠሙት ሴቶች በጣም ቆንጆዋና ፍላጎቱንም የምታረካ እንስት እሷ ናት ። የመድረክ ተዋናይነት ተግባሯን አቁማ ጊዜዋን በሙሉ ከእርሱ ጋር ታሳልፍ ነበር ። ኖኤሌ ከዚህ ቀደም ተሰምቶት የማያውቀውን የስሜት ረመጥ ጭራበታለች ። ፍቅረኛው ፣ የልብ ወዳጁና ጓደኛው ነበረች ። ዴሚሪስ ከልቡ አምኗት እያለ ወደላሪ ዶግላስ በመኮብለል ክድታዋለች ። ኖኤሌንም ለሞት የዳረጋት ጥፋቷ ይሄው ነበር ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ከግሪክ ባለሥልጣናት ጋር ተነጋግሮ አስከሬኗ በግል ደሴቱ ውስጥ በሚገኘው መካነ መቃብር እንዲቀበር አድርጓል ። እንዴት ዓይነት ማራኪ ቁመና እንደነበራት ያላደነቀ ሰው የለም ። እውነት ለመናገር ፣ ዴሚሪስ የቀብሯ ቦታ እዚያ እንዲሆን ያሴረው በዚያች



ውሻ መቃብር ላይ ዘወትር መረማመዱ ልዩ ደስታን ስለሚሰጠው ነው ። ከዴሚሪስ መኝታ ክፍል ውስጥ ከአልጋው ጐን ኖኤሌ አምራ ደምቃ ወደ እሱ በፈገግታ እያየች የተነሳችው ፎቶግራፍ ተቀምጧል ። በጊዜ የጠፋ የዘለዓለም ፈገግታ ።

ዓመት ቢያልፋትም ዴሚሪስ ዛሬም ስለእርሷ ማሰብን ከአእምሮው ሊያስወግድ አልቻለም ። ማንም ዶክተር አክሞ ሊያድንለት የማይችል የቆላ ቁስል ሆናበታለች ።

"ለምን ኖኤሌ? ለምን? ሁሉን ነገር ሰጥቼሽ ነበር ። አፈቅርሽ ነበር ፣ አንቺ ውሻ! በጣም ወድጄሽ ነበር ። አሁንም እወድሻለሁ ።"

እና ሌላው ላሪ ዶግላስ ነበር ። እሱም ተሰቃይቷል ። ቢሆንም ዴሚሪስ በዚያ ብቻ ሊያበቃ አልፈለገም ። ሌላ የበቀል እቅድ አልሟል ። በደንብ የታሰበበትና ዒላማውን የማይስት እቅድ ። ዶግላስ ኖኤሌን እንዳማገጠበት እርሱም በተራው የዶግላስን ሚስት አማግጦ በበቀል የመንፈስ እርካታ ሊያገኝ ነው ። ከዚያ በኋላ ካተሪንን ወደ ባሏ ይሰዳታል ።

"ኮስታ..."

ድምፁ የሚስቱ ነበር ።

ሜሊና ወደቤተ መጻሕፍቱ ገባች ።

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ከጥንታዊ የግሪክ መሳፍንታዊ ቤተሰብ የተገኘችዋን ውቧን ሜሊና ላምብሩን አግብቶ ነበር ። ሴትዮዋ ረዘም ያለች ሸንቃጣና ደርባባ ናት ።

"ኮስታ ፣ እዚህ ቤት ውስጥ ያየኋት ሴት ማን ናት?" ድምጿ ያስፈራ ነበር ።

ጥያቄዋ ወዲያው ገባው ። "ምን አልሽ? እ! የአንድ የንግድ ሸሪኬ ጓደኛ ናት" አለ ዴሚሪስ ። "ለንደን ከሚገኘው ቢሮዬ ሄዳ ልትሠራ ነው።"

"በጨረፍታ አይቻት ነበር ። የማውቃት — የማውቃት ይመስለኛል ።"

"እረ?"

"አዎ" ሜሊና አመነታች ። "አንተ ዘንድ ይሠራ የነበረውን አውሮፕላን ነጂ ሚስት መስላ ታየችኝ ። ቢሆንም እሷን ልትሆን አትችልም ። እነርሱ ገድለዋት የለም እንዴ?"

"አዎ" ሲል ኮንስታንቲን ዴሚሪስ በአባባሏ ተስማማ ። "ገደሏት።"

ሜሊና ተመልሳ ስትሄድ ትኩር ብሎ ተመለከታት ። ጥንቃቄ ማድረግ አለበት ። ሜሊና ሞኝ አይደለችም ። 'እርሷንኮ ማግባት አልነበረብኝም' አለ ዴሚሪስ በአሳቡ ። 'ትልቅ ስሕተት ነው...'

ከአሥር ዓመታት በፊት የሜሊና ላምብሩና የኮንስታንቲን ዴሚሪስ መጋባት ከአቴና ጀምሮ እስከ ሪቬራና ኒው ፖርት ባለው ነጋዴና ሌላም ሕብረተሰብ ዘንድ ትልቅ አስደንጋጭ ወሬ ሆኖ ሰንብቷል ። ጋብቻውን አስገራሚ ያደረገው ሙሽሪቷ ከመዳሯ ከአንድ ወር በፊት ሌላ ሰው ለማግባት ታጭታ የነበረ መሆኑ ነው ።

ሜሊና ላምብሩም በሕጻንነቷ ወቅት ቤተሰቦቿ ፍላጐቷን እንዲ ያሟሉላት በጣሙን ታስጨንቃቸው ነበር ።

ዕድሜዋ አሥር ዓመት ሲሞላው መርከበኛ ለመሆን ምኞት አደረባት ። በወደብ ላይ ከቆመው መርከብ ላይ ለመሳፈር ስትሸሎከሎክ የቤተሰቡ ሹፌር አይቷት አዋርዶ ነው ወደቤት የመለሳት ። ከሁለት ዓመት በኋላ ከተዘዋዋሪ የሰርከስ ትርዒተኞች ጋር ለመኮብለል ሞክራለች። ዕድሜዋ አሥራ ሰባት ሲሞላ ደግሞ ቁንጅናዋና ሥፍር ቁጥር የሌለው ሀብቷ ፣ እንዲሁም የሚሃሊስ ላምብሩ ሴት ልጅ መሆኗ ያኩራራት ጀመር ። ጋዜጦች ስለእርሷ መጻፍ ደስ ይላቸዋል። እንደተረት ውስጥ ገፀ ባሕርያት አጫዋች ባልንጀሮቿ ልዕልቶችና ልዑላን ነበሩ ። እንደዚህ ሆኖም በተአምር እንደሌሎቹ ከመበላሸት ድናለች ። ሜሊና በአሥር ዓመት ከሚበልጣት ወንድሟ ከስፒሮስ ጋር በጣም ትዋደድ ነበር። ሜሊና አሥራ ሦስት ዓመት ሲሞላት ወላጆቻቸው በጀልባ አደጋ ስለሞቱ ያሳደጋት ወንድሟ ነው ።



ሜሊና ፣ ስፒሮስ ሲንከባከባት ከመጠን እንደሚያሳልፍ ተሰምቷታል ። ሜሊና ለአቅመ ሔዋን እንደደረሰች ማን ሊመጥናት እንደሚችል ከመጨነቁም ሌላ ለጋብቻ ሊጠይቃት የሚቀርበውን ሰው ማንነት በጥንቃቄ ያጠና ነበር ። እንዳጋጣሚ ከቀረቡት መካከል አጥጋቢ መስለው የታዩት አልነበሩም ። "ጥንቃቄ ማድረግ አለብሽ" ይላታል ሁሌ ሲመክራት ። "ወጣት ፣ ሀብታምና ቆንጆ ከመሆንሽም በላይ ዝነኛም ነሽና በዓለም ውስጥ ላሉ ሀብት አሳዳጆች ዒላማ ነሽ ።"

"ብራቮ ውድ ወንድሜ ። ይሄ ሁሉ ምክርህ ዕድሜዬ ሰማንያ ዓመት ሞልቶ አርጅቼ አፍጅቼ እስክሞት ድረስ ይበቃኛል ።"

"አታስቢ ሜሊና ላንቺ የሚገባ ሰው ወደፊት ይመጣል ።"

ካውንት ቫሲሊ ማኖስ ይባላል ። ዕድሜው አርባ አምስት ገደማ ሲሆን ፣ ከተከበረ ጥንታዊ የግሪክ ቤተሰብ የወጣ የታወቀ ነጋዴ ነው ። ካውንት ቆንጆዋንና ወጣቷን ሜሊና እንዳያት ወዲያው በፍቅር ተያዘ ። ለጋብቻ ጥያቄ ያቀረበላትም እንደተዋወቁ በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ነበር።

"ላንቺ የሚስማማ ሰው ነው" አላት ስፒሮስ በደስታ ። "ማኖስ የተደላደለ ከመሆኑም ሌላ በፍቅር ከንፎልሻል ።"

ሜሊና አባባሉ እምብዛም ስሜት አልሰጣትም ። "አይማርከኝም ስፒሮስ! በተገናኘን ቁጥር ስለንግድ ነው የሚያወራው ። ንግድ፣ ንግድ ፣ ንግድ ። ለፍቅር ግምት የሚሰጥ ሰው ቢሆን ምንኛ ደስ ባለኝ ነበር ።"

ወንድሟ ኰስተር ብሎ "ፍቅር ብቻውን ለጋብቻ የሚበቃ ነገር አይደለም ። ላንቺ የሚያስፈልግሽ ባል ፣ የተደላደለ የማይለዋወጥና ጊዜውን ሁሉ ለአንቺ የሚሰዋ መሆን አለበት" አላት ። በመጨረሻ ሜሊና የካውንት ማኖስን ልመና እሺ እንድትል ተገደደች ።

መንፈሱ በደስታ የተነካው ካውንት "በዓለም ውስጥ ካሉት ደስተኛ ሰዎች አንዱ አደረግሽኝ" አላት ። "አዲስ ያቋቋምኩትን ኩባንያ ሜሊና ኢንተርናሽናል ብዬ ሰይሜዋለሁ ።"

የጽጌረዳ አበቦች እንደሚሻላት አስታወቀችው ። የሠርጉ ቀን ተወሰነ ፤ ለአንድ ሺህ ሰዎች የጥሪ ወረቀት ተላከ ፤ ዝርዝር እቅዶ ተነደፉ ።

ከዚያ በኋላ ነበር ኮንስታንቲን ዴሚሪስ በሜሊና ላምብሩ ሕይወት ውስጥ የገባው ።

የተገናኙትም ለእጮኛሞቹ የቀለበት በዓል ክብር ከሚደገሱት በርካታ ግብዣዎች ውስጥ ባንዱ ላይ ነበር ።

አስተናጋጅዋ አስተዋወቀቻቸው ። "ሜሊና ላምብሩ ትባላለች — ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ።"

ዴሚሪስ በትናንሽ ጥቁር ዓይኖቹ ትኩር ብሎ አያት ። "ምን ያህል ጊዜ ያቆዩሻል?" ሲል ጠየቃት ።

"ምን አሉኝ?"

"ውበት ምን እንደሆነ ለኛ ለአላፊዎቹ እንድትመሰክሪ ከገነት የተላክሽ ሳትሆኚ አትቀሪም ።"

ሜሊና ሳቅ አለች ። "በሀሰት ሰው ካቢ ነዎት ሚስተር ዴሚሪስ ።"

ጭንቅላቱን ነቀነቀ ። "እንቺን በሀሰት ልካብ ማለት አይቻልም። የምናገራቸው ማንኛቸውም ቃላት በትክክል ማንነትሽን ሊወክሉ እንኳ አቅም የላቸውም ።"

በዚህን ጊዜ ካውንት ማኖስ ወደነሱ ቀርቦ ንግግራቸውን አቋረጠ ።

ያን ዕለት ሌሊት በእንቅልፍ ከመወሰዷ በፊት ሜሊና ስለዴሚሪስ አስባ ነበር ። ከዚህ ቀደምም ፤ ስውዬው ሀብታም ፤ ሚስቱ የሞተችበት ፤ ሴት አሽቃባጭና ጨካኝ ነጋዴ ነው እየተባለ ሲወራበት ሰምታለች ።

'እንኳን ከእርሱ ጋር ድሮ አልተነካካሁ' አለች ሜሊና በአሳቧ። አማልክቱ ይስቁ ነበር ።

ግብዣው በተደረገ በማግስቱ የሜሊና የልፍኝ አሽከር ቁርስ ወደምትመገብበት ክፍል ገባ ። "የሚስተር ዴሚሪስ ሹፌር አንድ ጥቅል ዕቃ አምጥቶልሻል ሚስ ላምብሩ ።"



"እስቲ ወዲህ አምጣው ።"

'መስሎታል ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ በሀብቱ የሚስበኝ ይመስለዋል ። ምናለ ታዲያ በገዛ እጁ የሚያበሳጨውን ነገር እያዘጋጀ ነው። የፈለገውን ነገር ቢልክ…ለምን የከበረ ዕንቁ ወይንም ፡ ወይንም እጅግ ውድ የሆነ ጥንታዊ ቅርስ አይሆንም…አሁኑኑ መልሼ ነው የምልክለት።'

ፓኮው ትንሽና ሞላላ ሲሆን ባማረ ሁኔታ ተጠቅልሏል ። ምን እንደሆነ ለማወቅ በመጓጓት ሜሊና ጥቅሉን ፈታችው ። በውስጡ ያለው ካርድ ላይ "የላኩልሽ የምትወጂው ስለመሰለኝ ነው ፡ ኮንስታንቲን ።" የሚል ተጽፏል ።

ስጦታው በቆዳ የተጠረዘ በኒኮስ ካዛንዛኪስ የተጻፈ ቶዳ ራባ የተሰኘ መጽሐፍ ነው ። ሜሊና ይህን ደራሲ እንደምትወድ እንዴት ሊያውቅ ቻለ?

ሜሊና ትሕትና የተሞላበት ምስጋና ጻፈችና አስላሰለች ። 'እንዲህ ነው እንግዲህ ።'

በሚቀጥለው ቀን ሌላ ጥቅል መጣ ። የአሁኑ ደግሞ በምትወደው ሙዚቃ ቀማሪ የተደረሰ ዴሊአስ የተሰኘ ዘፈን ያለበት ሸክላ ነው ። አብሮት ያለው ማስታወሻ "ይህንን እያዳመጥሽ ቶዳ ራባን ስታነቢ ደስ እንደሚልሽ አምናለሁ" ይላል ።

ከዚያን ዕለት ጀምሮ ስጦታ በየዕለቱ ጐረፈ ። የምትወደው አበባ ፡ ሽቶ ፡ ሙዚቃና ፡ መጻሕፍት ተዥጎደጎዱ ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ፍላጐቷ ምን እንደሆነ ለማጥናት ያላደረገው ጥረት አልነበረም ። እሷም በሚደረገው ሁሉ ከመታለል በስተቀር ምንም ለማድረግ አልቻለችም ።

ሜሊና ምስጋና ልታቀርብ እንደደወለች "ከዚህ የበለጠ ለአንቺ የሚሆን ባደርግ ምንኛ ደስ ይለኝ ነበር" አላት ።

'ከዚህ ቀደም እንዲህ ዓይነቶቹን ቃላት በስንቶቹ ሴቶች ጆሮ አንቆርቁሮ ይሆን?'

"ሜሊና ፡ አብረሽኝ ምሳ ልትበዪ ትችያለሽ?"

እምቢ ለማለት ፈለገችና እንደገና አሰበች ። "ከሰውዬው ጋር ምሳ ብበላ ምን አጎዳለሁ ። ለኔ አሳቢዬ ነው ።"

"በጣም ጥሩ ።"

ከኮንስታንቲን ዴሚሪስ ጋር ምሳ ልትመገብ መዘጋጀቷን ለካውንት ማኖስ በገለፀችበት ወቅት ተቃውሞዋት ነበር ።

"የኔ ፍቅር ምን ያስፈልጋል? ከዚያ አደገኛ ሰውዬ ጋር የሚያግባባችሁ ነገር ያለ አይመስለኝም ። እርሱ ዘንድ የምትሄጂው ለምንድን ነው?"

"ቫሲሊስ ፡ በየዕለቱ ጥቃቅን ስጦታዎችን ይልክልኝ ስለነበረ ይህንኑ እንዲያቆም ልነግረው ነው ።" ሜሊና እነኚህን ቃላት እንደ ተናገረች 'ይህንንማ በስልክ ልነግረው እችል ነበር' አለች በልቧ ።

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ፓኔፒስቲሙ ጎዳና ላይ ከሚገኘው ፍሎካ ሬስቶራንት ፡ አስቀድሞ ቦታ እንዲያዝ አዘዘና ሜሊና ስትደርስ ቀድሞ ጠበቃት ።

ከተቀመጠበት ተነሳ ። "መጣሽ? አሳብሽን ትቀይሪአለሽ ብዬ ሰግቼ ነበር ።"

"ሁል ጊዜ ቃሌን እጠብቃለሁ ።"

ወደ እርሷ እየተመለከተ ፊቱን ኮስተር አደረገ ። "እኔም ቃሌን የምጠብቅ ሰው ነኝ ። አገባሻለሁ ።"

ሜሊና በከፊል በደስታ ፡ በከፊል በንዴት ተውጣ ጭንቅላቷን ነቀነቀች ። "ሚስተር ዴሚሪስ ፡ ሌላ ሰው ለማግባትኮ ታጭቻለሁ።"

"ማኖስን?" የማጥላላት ዓይነት ምልክት በእጁ አሳየት ።

"እርሱ ለአንቺ የሚስማማሽ ሰው አይደለም ።"

"እረ ። ለምን ይሆን?"

"ስለ እርሱ በደንብ አጣርቻለሁ ። በቤተሰባቸው ውስጥ የንክነት በሽታ አለ ። የደም ሥር በሽታም አለበት ። ብሩሰልስ ውስጥም ሕገወጥ ወሲብ ፈጽመሐል ተብሎ በፖሊሶች እየተፈለገ ነው። በዚህ ላይ አደገኛ የሆነ የቴኒስ ኳስ ተጫዋች ነው ።"

ሜሊና ሳቋን ልታቆም አልቻለችም ። "አንተስ?" ብላ ጠየቀችው ።

"እኔ ቴኒስ አልጫወትም ።"

"ገባኝ ፡ ታዲያ አንተን ማግባት ያለብኝ ለዚህ ነዋ!"

"አይደለም ። እኔን የምታገቢው እስካሁን በዓለም ላይ ከነበ



ሩት ሴቶች ሁሉ ይልቅ በጣም ደስተኛ ሴት ስለማደርግሽ ነው ።"

"ሚስተር ዴሚሪስ..."

እጇን እጇ ላይ ጫነና "ኮስታ" አለ ።

እጇን ከእጁ ሥር ስባ አወጣች ። "ሚስተር ዴሚሪስ ፡ ዛሬ እዚህ የመጣሁት በየጊዜው የምትልክልኝን የስጦታ በረከት እንድታቆም ልነግርህ ነው ። ሁለተኛ ላይህ ፈቃደኛ አይደለሁም ።"

ረዘም ላለ ጊዜ ትኩር ብሎ አያትና "እርግጠኛ ነኝ ጨካኝ ሴት እንዳልሆንሽ ።"

"እንዳልሆንኩ እተማመናለሁ ።"

ፈገግ አለና "ጥሩ ፡ ስለዚህ ልቤን አታቆስዪውም" ሲል ተናገረ ።

"ልብህ ያንን ያህል በቀላሉ ለመቁሰል እጠራጠራለሁ ። ሰፊ ልምድ ያለህ ይመስለኛል ።"

"ያማ ካንቺ ጋር ከመተዋወቄ በፊት ነበር ። ስለአንቺ ለረዥም ጊዜ ሳልም እንደነበረ ታውቂያለሽ?"

ሜሊና ከት ብላ ሳቀች ።

"የምሬን ነው ። በዕድሜ ወጣትበነበርኩ ጊዜ ስለ ላም
ብሩ ቤተሰቦች አነብ ነበር ። ያኔ አንቺ ሀብታም እኔም መናጢ ደሀ ነበርኩ ። ምንም አልነበረኝም ። የምኖረው ከእጅ ወደአፍ በሆነ ሥራ ነበር ። አባቴ በፒራኡስ ወደብ ላይ የሚሠራ ተሸካሚ ነበር ። አሥራ አራት ወንድሞችና እህቶች ነበሩኝ ። እና የምንፈልገውን ለማግኘት ሁሌ ትንቅንቅ ማድረግ ነበረብን ።"

አነጋገሩ በጣም ነካት ። "እና አሁን ሀብታም ነህ?"

"አዎ ፡ ግን ገና መንካት ከሚገባኝ ጣራ አልደረስኩም ።"

"ረሀብ ይርበኝ ነበር ። አሁንም ይርበኛል ።"

እውነትን ከዓይኑ ውስጥ ለማንበብ ችላለች ። "እንዴት...እንዴት አድርገህ ነው የተነሳኸው?"

"በእውነት ለማወቅ ትፈልጊያለሽ?"

ሜሊና ሳታውቀው ከአፏ አምልጦ "በእውነት ለማወቅ እፈልጋለሁ" አለች ።"

"አሥራ ሰባት ዓመት እንደሞላኝ ለአንድ የነዳጅ ኩባንያ ለመሥራት ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ተቀጥሬ ሄድኩ ። ደስ የሚል

አልነበረም። አንድ ቀን ማታ በትልቅ የነዳጅ ኩባንያ ውስጥ ከሚሠራ ወጣት የሥነ አፈር ተመራማሪ ጋር እራት ተመግቤ ነበር ። እኔ ስቴክ ሥጋ እንዲቀርብልኝ ሳዝ እርሱ ሾርባ ብቻ ነበር የጠጣው። ስቴክ ሥጋ ለምን አላዘዝክም ብዬ ስጠይቀው የመንጋጋ ጥርስ ስለሌለኝና ለማስተከልም ስለማልችል ነው ብሎ መለሰልኝ ። ሰው ሰራሽ የመንጋጋ ጥርስ እንዲገዛ ሃምሳ ዶላር ሰጠሁት ። ከወር በኋላ እኩለ ሌሊት ላይ ስልክ ደውሎ አዲስ የነዳጅ ዘይት ክምችት ማግኘቱን ገለጠልኝ ። ስለጉዳዩ ለአሠሪውም አልገለጠም ነበር ። በነገታው ከየቦታው ገንዘብ ተበዳድሬ ነዳጁ ተገኘበት የተባለውን መሬት ገዛሁ ። በዓለም ውስጥ ከፍተኛው የነዳጅ ዘይት ክምችት የሚገኝበት ሆኖ ተገኘ ።”

ሜሊና በጣም አጓጊ የሆነውን ንግግሩን በጥሞና ታዳምጥ ነበር።

“መነሻዬ ይሄ ነው ። የነዳጅ ዘይት ማጓጓዣ ስላስፈለገኝ ብዙ መርከቦች ገዛሁ ። ከዚያ ማጣሪያ ፡ ቀጥሎ አውሮፕላን ።” ነቅነቅ አለ ። “እንዲያ እያለ ሄደ ።”

ስለስቴክ ሥጋው የነገራት ታሪክ ሐሰት መሆኑን ተጋብተው ብዙ ጊዜ አስከቆዩ ጊዜ ድረስ ሜሊና አላወቀችም ነበር ።

ሜሊና ላምብሩ ኮንስታንቲን ዴሚሪስን ደግሞ ለመገናኘት ምንም ፍላጐት አልነበራትም ። ዴሚሪስ ሆን ብሎ በተቀናበረ ፣ ግን አጋጣሚ መስሎ በሚታይ ሁኔታ ሜሊና በምትገኝበት ፓርቲ ፣ ትያትርና የበጎ አድራጐት ድርጅት ስብሰባ ላይ ይገኛል ። ባየችው ቁጥር የሰውዬው የመስህብ ኃይል ጉድ እያረጋት መሆኑ ይሰማታል። ከሱ ሌላ በተለይ ቫሲሊስ ማኖስ ምን ያህል እንዳስጠላት ለማመን ፈራች ።

ሜሊና ላምብሩ የጀርመኖችን ሥዕል በጣም ትወዳለች ። በብሩኤሄል የተሳለው ሃንተርስ ኢን ዘ ስኖው የተሰኘው ሥዕል ገበያ ላይ ሲውል ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ቀድሟት ገዝቶ በስጦታ መልክ ላከላት ።



ሜሊና ፍላጐቷን ቀድሞ የማወቅ ረቂቅ ችሎታውን በጣም አደነቀች ። “እንዲህ ዓይነት ውድ ስጦታ ከአንተ መቀበል አልችልም” ስትል ተቃውሞዋን ገለጸችለት ።

“እ! ስጦታክ አይደለም ብድር ነው ። ዛሬ ከኔ ጋር እራት በመብላት ትከፍይኛለሽ ።”

በመጨረሻ ተስማማች ። ሰውዬው ሊቋቋሙት የሚችሉት አይደለም ። ከሳምንት በኋላ ሜሊና ለካውንት ማኖስ የገባቸውን የጋብቻ ቃል ኪዳን አፈረሰች ።

ሜሊና ስለዚሁ ውሳኔዋ ለወንድሟ ስትነግረው ክው አለ ።

“በእግዚአብሔር ለምን?” ብሎ ጠየቃት ስፒሮስ ። “ግን ለምን?”

“ኮንስታንቲን ዴሚሪስን ስለማገባ!”

በጣም ተረበሸና “አብደሻል ልበል? ዴሚሪስን ልታገቢው አትችይም ። ሰውዬው ጭራቅ ነው ፤ ያጠፋሻል ። ምናልባት ....”

“ስለእርሱ ያለህ አመለካከት የተሳሳተ ነው ። ስፒሮስ በጣም ጥሩ ሰው ነው ። ደግሞ ተዋደናል ። .....”

“ተዋዳችሁ ሞታችኋል” አለ በማሽሟጠጥ ። “አንድ ጥቅም ይኖረዋል እንጂ ለፍቅር ብሎ አይደለም። ከዚህ ቀደም ሴቶችን ምን ያደርግ እንደነበር ታውቂያለሽ? እርሱ ...”

“ያ ያለፈ ታሪክ ነው ስፒሮስ ፤ ሚስቱ ለመሆን ወስኛለሁ ።”

እህቱን ከጋብቻው ለማከላከል ሊያደርግ የሚችለው ምንም ነገር አልነበረም ።

ከአንድ ወር በኋላ ሜሊና ላምብሩና ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ተጋቡ ።

በመጀመሪያ ሲታይ ትዳራቸው የተዋጣላት ይመስል ነበር ። ኮንስታንቲንም አስደሳች ፣ ትሁት ፣ አንጀት የሚበላና የጋለ የፍቅር ስሜት ያለው ፍቅረኛ ነበር ። ያልታሰበ አስደሳች ስጦታዎች በማቅረብና ለሽርሽር ብርቅ ወደሆኑ ሥፍራዎች ይዟት በመሄድ ያስደስታታል ።

በጫጉላ ጊዜያቸው የመጀመሪያዋ ምሽት “የመጀመሪያዋ ሚስቴ ልጅ ልትወልድልኝ አልቻለችም ነበር ። አሁን ግን ብዙ ወንድ ልጆች ይኖሩናል” አላት ።

“ሴት ልጅስ አያስፈልገንም?” ብላ በሽሙጥ ጠየቀችው ።

"ደስ ካለሽ ጥሩ ። ግን መጀመሪያ ወንድ ልጅ ።"

ሜሊና ቅሪት መያዟን ስታውቅ ኮንስታንቲን በጣም ነበር የፈነደቀው ።

"ይተካኛል ። ግዛቴን ይወርሳል" አለ በደስታ ።

በሦስተኛው ወር ሜሊናን አስወረዳት ። ይህ ሲፈጸም ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ከግሪክ ውጭ ነበረ ። ከሄደበት ሥፍራ ተመልሶ ነገሩን ሲሰማ እብድ ሆነ ።

"ምንድን ነው ያደረግሽው?" ሲል ጮኸባት ። "እንዴት ሊያስወርድሽ ቻለ?"

"ኮስታ ፣ እኔ ……"

"ግድየለሽ ነበርሽ ማለት ነው ።"

"በፍፁም ፣ እምልልሃለሁ …."

አየር በኃይል ወደ ውስጥ ሳበና "መልካም ፡ የሆነው ሆኗል ። ሌላ ወንድ ልጅ ይኖረናል" አላት ።

"እኔ ….እኔ አልችልም" አለች ዓይኑን ማየት እያፈረች ።

"ምንድንነው የምትዪው?"

"በኦፕራሲዮን ማኅፀኔን ስለዘጉት ከእንግዲህ ልወልድ አልችልም።"

እዚያው እቆመበት እንደበረዶ ቀዘቀዘና የኋሊት ዞሮ ቃል ሳይተነፍስ ውልቅ አለ ።

ከዚያች ደቂቃ አንስቶ የሜሊና ሕይወት ምድራዊ ሲኦል ሆነባት ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ሚስቱ ሆና ብላ ጽንሱን ያስወጣች መስሎት ጨርሶ ዘጋትና ሌሎች ሴቶችን ማባረር ጀመረ ።

ለሜሊና ውርደቱ በይበልጥ እንዲሰማት ያደረገው ባሏ ከሌሎች ሴቶች ጋር ያለው ግንኙነት ይፋ እንዲወጣ የሚያደርገው ጥረትና ይኸው ተግባሩ ይሰጠው የነበረው እርካታ ነው ። ከፊልም ተዋናዮች ፣ ከኦፔራ ዘፋኞች ፣ ከጓደኞቹ ሚስቶች ጋር በግልጽ ይማግጥ ነበር ። ፍቅረኞቹን በቺኦስ አካባቢ ወዳለው የግል ደሴቱ ፣ ወደ መንሸራሸሪያ ጀልባውና የሕዝብ መዝናኛ ሥፍራዎች ይዟቸው ይሄዳል ። ይህንኑ የማተራመስ ተግባሩን ጋዜጦች በደስታ ያራግቡለታል ።



በአንድ የታወቀ ባንከኛ ቤት በእራት ላይ ተገኝተው ነበር ።

"አንተና ሜሊና መምጣት አለባችሁ" ባንከኛው ስላለው ነበር ባለቤቱን ይዞ የመጣው ። "በዓለም ላይ ተወዳዳሪ የማይገኝለትን የቻይናውያን ምግብ መስራት የሚችል የወጥ ቤት ቀጥሬያለሁ ።"

ለግብዣው የተጠሩት ሰዎች ታላላቅና ዝነኛ የተባሉት ነበሩ ። የሥነ ጥበብ ባለሙያዎች ፡ የፖለቲካ ሰዎችና ባለኢንዱስትሪዎች ተገኝተዋል ። በእርግጥ ምግቡ በጣም ቆንጆ ነበር ። የዓሣ ሾርባ ፡ ከተፈልቃቂ ዓሣ የተሠራ ሳምቡሳ ፡ የአሳማ ሥጋ ፡ የፔኪንግ ዳኪዬ ፡ የጎድን ጥብስ ፡ ከእንቁላልና ሥጋ የተዘጋጀ ጥብስና ሌሎችም በርካታ ምግቦችን ወጥ ቤቱ አቅርቧል ።

ሜሊና ከደጋሹ ጎን ስትቀመጥ ባልዋ ደግሞ ከደጋሿ ጎን ነበር የተቀመጠው ። ከዴሚሪስ በስተቀኝ መልከ ቀና የሆነች የፊልም ተዋናይ ተቀምጣለች ። ዴሚሪስ ሰዎች አዩኝ ብሎ ሳይጨነቅ ተዋናይዋን ማሽኮርመም ጀመረ ። ከተዋናይዋ ጋር ይለዋወጣቸው ከነበሩት ቃላት ጥቂቱ ሜሊና ጆሮ ገቡ ።

"የፊልም ሥራሽን እንደጨረስሽ በጀልባዬ እንድንንሸራሸር ጋብዤሻለሁ ። በጣም ደስ የሚያሰኝ የእረፍት ጊዜ ይኖርሻል ። እስከዳልማቲያን የባሕር ጠረፍ ድረስ አብረን እንንሸራሸራለን ። …."

ሜሊና ለነገሩ ጆሮዋን ላለመስጠት ሞክራ ነበር ፡ ግን አልቻለችም። ዴሚሪስም ድምጹን ለመቀነስ ጥረት አላሳየም ። "ወደ ካሳራ ሄደሽ ታውቂያለሽ ወይ? ከሌሎች ሥፍራዎች የተለየች ደስ የምታሰኝ ደሴት ናት። በጣም ትወጂያታለሽ ።" ሜሊና ተጠቅልላ ጠረጴዛው ሥር ብትገባ ደስ ባላት ነበር ። ሆኖም ከዚህ የሚብሰውም ሊመጣ አይደል!

የጎድን አጥንቱን ግጠው እንደጨረሱ በጎድጓዳ የብር ሳህን ፍራፍሬ መዞር ጀመረ ።

አስተናባሪዎቹ ፍራፍሬውን ለወጣቷ የፊልም ተዋናይ እንዳቀረቡ ዴሚሪስ "ይህ ለአንቺ የሚያስፈልግ አይደለም" ሲል ፈገግ እያለ እጇን ወደ ላይ አነሳ ። ጣቶቿን በተራ እየላሰ ወጡን ሲያደርቅላት ተጋባዦቹ ሁሉ በመገረም ተመለከቱት ።

ሜሊና ብድግ ብላ ወደ ጋባዡ ባንከኛ ዞር አለች ። "ይቅርታ አድርግልኝ እራስ …. እራስ ምታት አሞኛል ።"

ከግብዣ አዳራሹ ውልቅ ስትል ተጋባዦች አዩዋት ። ዴሚሪስ ያን ዕለትም ሆነ በሚቀጥለው ቀን ፣ ማታ ወደቤት አልሄደም ።

ስፒሮስ ያን ዕለት ምሽት የተፈጸመውን ድርጊት ሲሰማ ሰውነቱ ተለዋወጠ ። “እባክሽ ፍቀጅልኝ” አላት ወንድሟ ። “ይህን የውሻ ልጅ ልግደለው ።”

“ወዶ አይደለም” አለች ሜሊና ለባሏ ስትከላከል ። “ተፈጥሮው ነው ።”

“ተፈጥሮው ነው ትያለሽ? ከብትነት ነው እንጂ ፤ እሱን ማስወገድ አለብሽ ። ለምን አትፈቺውም?”

ይሄ ሜሊና ዴሚሪስ ለረዥም ጊዜያት በብቸኝነት በምታሳልፋቸው ምሽቶች ደጋግማ ለእራሷ የምታቀርበው ጥያቄ ነው ። ምላሿ ዞሮ ዞሮ አንድ ዓይነት ይሆንባታል ። “እወደዋለሁ ።”

ከንጋቱ በአሥራ አንድ ሰዓት ተኩል ይቅርታ ጠይቃ ወደ ክፍሏ የገባችው ሠራተኛ ካተሪንን ከእንቅልፏ ቀሰቀሰቻት ።

“እንደምን አደርሽ ፤ ሚስ ...”

ካተሪን ዓይኗን ገልጣ ግራ በመጋባት ዙሪያዋን ቃኘች ። በገዳሙ ውስጥ ካለች ጠባብ ክፍል ውስጥ ሳይሆን በጣም በተዋበ የመኝታ ክፍል ውስጥ ነው ያለችው ።

ትውስታዋ እየተፍለቀለቀ መጣ ። ‘ወደ አቴንስ ያደረገችው ጉዞ ... አንቺ ካተሪን ዶግላስ ነሽ... የተገደሉት በመንግሥት ነው ...’

“ሚስ ...”

“አቤት?”

“ሚስተር ዴሚሪስ ከበረንዳው ላይ አብረሻቸው ቁርስ እንድታደርጊ ጋብዘውሻል ።”

ካተሪን በእንቅልፍ ልቧ ሠራተኛዋን ትኩር ብላ ተመለከተች ። አንጎሏ በመተረማመስ እስከሌሊቱ አሥር ሰዓት ድረስ እንቅልፍ የሚባል ነገር በዓይኗ አልዞረም ነበር ።

“አመሰግናለሁ ፤ እንደምመጣ ለሚስተር ዴሚሪስ ንገሪልኝ ።”

ከሃያ ደቂቃ በኋላ የእልፍኝ አሽከሩ ለባሕሩ ትይዩ ወደሆነው ሰፊ በረንዳ መርቶ ወሰዳት ። በረንዳው የታጠረበት የድንጋይ ግንብ አጭር በመሆኑ ከሃያ ጫማ ከማይበልጥ ርቀት ላይ ያለውን አትክልት አሻግሮ መመልከት ይቻላል ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ተቀምጦ ጠበቃት ። ካተሪን



ወደሱ ስትራመድ አተኩሮ አያት ። ልብ የሚነካ የዋህነት ከፊቷ ይነበባል። ይህ የዋህነቷን ሊወስድ ፣ የግሉ ሊያደርግ ነው ። ራቁቷን አልጋ ላይ ስትታይ ምን ልትመስል እንደምትችል እያሰበ ኖኤሌንና ላሪን ዳግመኛ ለመቅጣት እንዴት ሊረዳው እንደሚችል ታየው ። ዴሚሪስ ከተቀመጠበት ተነሳ ።

“እንደምን አደርሽ? ሳይነጋ ከእንቅልፍሽ ስለቀሰቀስኩሽ ይቅርታ እጠይቃለሁ ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ወደቢሮ መሄድ ስላለብኝ ካንቺ ጋር ትንሽ ለማውራት ጊዜ እንዲኖረን ብዬ ነው በሌሊት ያስጠራሁሽ ።”

“ደስ ይለኛል” አለች ካተሪን ። ከፊትለፊቱ ካለው ወንበር ላይ ከእብነበረድ ከተሠራው ጠረጴዛ አጠገብ ከባሕሩ ትይዩ የማለዳዋ ዠምበር ብቅ ብላ ብዙ ሺህ ጨረሮቿን ከባህሩ ላይ ታዘንባለች ።

“ምን ዓይነት ቁርስ ትፈልጊያለሽ?”

ጭንቅላቷን ነቀነቀች ። “አልራበኝም ።”

“ቡናስ?”

“እሺ አመሰግናለሁ ።”

የእልፍኝ አሽከሩ በስኒ ቡና ቀዳላት ።

“መልካም ፣ ካተሪን” ሲል ዴሚሪስ ንግግሩን ጀመረ ። “ስለትናንቱ ጭውውታችን አስበሽበታል?”

ካተሪን ሌሊቱን በሙሉ ስለዚሁ ጉዳይ እንጂ ስለሌላ ነገር አላሰበችም ። በአቴንስ ውስጥ የቀራት ምንም ነገር የለም ። ሌላ መሄጃ ሥፍራም የላትም ። ‘ወደገዳሙ እንደሆነ ተመልሼ አልሄድ!’ አለች በልቧ። ለንደን በሚገኘው ቢሮው ውስጥ እንድትሠራ ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ያቀረበው ጥያቄ ቸል የሚባልም አይደለም ። ‘እንዲያውም የሚያጓጓ ነው’ አለች በልቧ ። ‘የአዲስ ሕይወት መጀመሪያ ሊሆን ይችላል ።’

“አዎ” አለች ካተሪን ። “አስቤበታለሁ ።”

“እና ?”

“ል — ልሞክረው እፈልጋለሁ ።”

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ በውስጡ የተሰማውን የእፎይታ መንፈስ ለማመቅ ሞከረ ። “ጐሽ በጣም ደስ አለኝ ። ለመሆኑ ከዚህ በፊት ለንደን ሄደሽ ነበር?”

“አይ ፣ ያንን ሥፍራ — የማውቀው አይመስለኝም ።” ‘ለምንድ

ነው ግን የማላውቀው?’ አእምሮዋ ውስጥ ከሚጉላሉት ነገሮች አኳያ ፍርሃት አድሮባታል ። ‘ስንትስ ተጨማሪ አዳዲስ ነገሮች ይከሰቱልኝ ይሆን?’

“በዓለም ውስጥ በሥልጣኔ በጣም ከገፉ ከተሞች መካከል የቀረች ልን አንዷ ለንደን ናት ። “እርግጠኛ ነኝ በጣም ትወጂያታለሽ ።” አለ ዴሚሪስ ።

ካተሪን እንደማመንታት አለች ። “ሚስተር ዴሚሪስ ለእኔ ብለው ይህን ያህል የሚቸገሩት ለምንድነው?”

“ኃላፊነት ስለሚሰማኝ ነው” ለንግግሩ ፋታ ሰጠና “ባለቤትሽን ከኖኤሌ ፓጂ ጋር ያስተዋወቅኩ እኔ ነበርኩ ።” አላት ።

“አሃ” አለች ካተሪን በለሆሳስ ። ‘ኖኤሌ ፓጂ ።’ ይህን ስም ስትሰማ አንድ ነገር ሰውነቷን ወረራት ። ‘አንደኛው ለሌላኛው ሲል ነው ሁለቱም የሞቱት ። ላሪ በጣም ሳያፈቅራት አልቀረም ።’

ካተሪን ሌሊቱን ሙሉ አእምሮዋን ያስጨንቅ ስለነበረው ጉዳይ ልትጠይቀው ፈለገች ። “እንዴት .... እንዴት ነበር አገዳደላቸው?”

ለትንሽ ጊዜ ዝምታ ሰፈነ ። “በተኳሽ ቡድን ጥይት ተደብድ በው ።”

“ውይ” አለች ። የጥይቷ እርሳስ የላሪን ሥጋ በጣጥሳ ወደ ውስጥ ስትሰምጥ ታየቻት ። በአንድ ወቅት በጣም ትወደው የነበረውን ሰው ገላ ጥይቷ ስትበጣጥሰው ማስታወሱ ዘገነናት ። ጥያቄውን ማቅረቧ መልሶ ፀፀታት ።

“እስቲ ትንሽ ምክር ልስጥሽ ። ስላለፈው አታስቢ ትርፉ ጉዳት ብቻ ነው ። ያለፈውን ሁሉ ከኋላሽ መወርወር ይገባሻል ።”

ካተሪን ባነሰ ድምፅ “እውነትዎን ነው ። እሞክራለሁ ።” አለች ።

“መልካም ፣ ዛሬ ጠዋት ወደ ለንደን የሚበር አውሮፕላን አለ ። በቶሎ ልትዘጋጂ ትችያለሽ?” ሲል ጠየቃት ።

ካተሪን ከላሪ ጋር ለመጓዝ ዝግጅት ስታደርግ ፣ ዕቃ ስትጠቀልል ይሰፍንባት የነበረውን ጉጉት አስታወሰች ።

አሁን ግን አብሯት የሚጓዝ ሰው የለም ፤የሚጠቀለልም ዕቃ በጣም ጥቂት ነው ፤ በአጠቃላይ ሰፊ ዝግጅት የሚጠይቅ የጐላ ነገር የለም ። “አዎ በቶሎ መዘጋጀት እችላለሁ” አለች ።

“እጅግ በጣም ጥሩ ። በነገራችን ላይ” አለ ዴሚሪስ እግረ



መንገዱን። “አሁን የማስታወስ ችሎታሽ ተመልሷል ። ምናልባት ልትገናኚው የምታስቢውና ጤነኛ መሆንሽንም ልትገልጪለት የምትፈ ልጊው ወዳጅ ካለ?”

ዊልያም ፍሬዘር የሚል ስም በድንገት ብልጭ አለባት ። ካለፈው ሕይወቷ የሚታወሳትና አሁን በዓለም ላይ የሚገኝ እርሱ ብቻ ነው ። ሆኖም በአሁኑ ደረጃ ልትገናኘው ዝግጁ አይደለችም ። ‘ስረጋጋ ፣ እንደገና መሥራት ስጀምር ነው የምገናኘው’ ስትል አሰበች ።

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ መልሷን እስኪሰማ በጥሞና ተመለከታት ።

“የለም” አለች ካተሪን “ማንም የለም ።”

እንዲህ በማለቷ የዊልያም ፍሬዘርን ሕይወት እንዳተረፈች ግን አታውቅም ።

“ፓስፖርት እንዲዘጋጅልሽ አደርጋለሁ” አለና አንድ ፖስታ ሰጣት ። “ይህ የቅድሚያ ደመወዝሽ ነው ። ስለመኖሪያሽም መጨነቅ አይገባም ። ኩባንያው ለንደን ውስጥ ቤቶች ስላሉት እዚያ ውስጥ ትቀመጪያለሽ ።” አስገረማት ። “ከመጠን በላይ ደግ ነዎት ።”

እጇን ጨበጥ አድርጐ ያዘ ። “ወደፊት ትረጂያለሽ እኔ...” ለማለት የፈለገውን ቀየረ ።”ባሃሣቡም ‘በጥንቃቄ ያዛት’ የሚል መጣበት ። ‘በዝግታ፡ አስደንግጠህ ልታስበረግጋት አይገባም’ ያቋረጠውን ለመጨ ረስ ። “... ጥሩ ወዳጅሽ ልሆን እንደምችል ።”

“በጣም ጥሩ ወዳጅ ነዎት ።”

ዴሚሪስም ፈገግ አለ ። ‘ቆይ!’

ከሁለት ሰዓት በኋላ ኮንስታንቲን ዴሚሪስ በሮልስ ሮይስ መኪናው ውስጥ በስተኋላ አስቀመጣትና ወደ አውሮፕላን ማረፊያ ወሰዳት ።

“ለንደንን ተደሰቺበት” አላት ። “በየጊዜው እደውልልሻለሁ ።”

ከመኪናው ካወረዳት ፣ ከአምስት ደቂቃ በኋላ ዴሚሪስ ወደለንደን ስልክ ደወለ ።

“በመንገድ ላይ ነች ።”

# ምዕራፍ አምስት

አውሮፕላኑ ከሄሌኒኮን አውሮፕላን ጣቢያ የሚነሳው ከጠዋቱ 3 ሰዓት ላይ ነው ። በሀዋከር ስዲለይ አይሮፕላን ውስጥ ብቸኛ ተሳፋሪ መሆኗ ካተሪንን በጣም አስገርሟታል ። በመካከለኛው ዕድሜ ላይ የሚገኘው መልከ መልካሙ ግሪካዊ የአውሮፕላኑ ዋና አብራሪ ፓንቴሊስ ካተሪን በምቾት መቀመጧንና የወንበሩን መታጠቂያ ማሰሯን አረጋገጠ።

"ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ አውሮፕላኑ ከመሬት ይለቃል" አላት ።

"አመሰግናለሁ ።"

ዋና አብራሪው ፣ ረዳቱ ወዳለበት ክፍል ሲገባ እንዳየች ልቧ በድንገት በኃይል መምታት ጀመረ ። ይህን አውሮፕላን ላሪ ያበረው ነበር። በዚህ በተቀመጥኩበት መቀመጫ ለይ ኖኤሌ ፓጂ ተቀምጣ ይሆን? ከመቅጽበት የማጥወልወል ስሜት ተሰማት ። ብዥ አለባት ። ዓይኗን ከድና በኃይል ወደ ውስጥ ተነፈሰች ። 'አለቀ ደቀቀ' አለች በአሳቧ። 'ዴሚሪስ የተናገረው ልክ ነው ፤ ያ ያለፈ ነገር ነው እና የሚለውጠው ምንም ነገር የለም ።'

የሞተሩን ጩኸት እንደሰማች ዓይኗን ገለጠች ። አውሮፕላኑ እኰብኩቦ እንደተንሳፈፈ ወደሰሜናዊ ምዕራብ በማምራት ጉዞውን ወደ ለንደን ቀጠለ ። 'ላሪ በዚህ አውሮፕላን የበረረው ስንት ጊዜ ይሆን ?' "ላሪ" የሚለው ስም ባሳደረባት ስሜት ተሸበረች ። በትውስታውም ተብረከረከች ። ሊረሳ የማይቻል ግሩም የሆነ መከረኛ ትዝታ ...

ጊዜው የ1940 ሰመር ወቅት ነበር ። አሜሪካ ወደጦርነቱ ውስጥ ከመግባቷ በፊት መሆኑ ነው ። ካተሪን ከኖርዝ ዌስተርን ዩኒቨርስቲ እንደተመረቀች ወዲያው ሥራ ለመጀመር ከቺካጐ ወደ ዋሽንግተን ዲሲ ሄደች ።



የመኝታ ክፍል ደባሏ "ሥራ ከፈለግሽ ክፍት የሥራ ቦታ እንዳለ ሰምቻለሁ ። ትላንት ማታ ፓርቲ ላይ ያገኘኋት አንዲት ልጅ ሥራዋን ሊቃ ወደ ቴክሳስ እንደምትመለስ ገልጻልኛለች ። ቤል ፍሬዘር ነው የቀጠራት። በመንግሥት ጽ/ቤት የሕዝብ ግንኙነት ክፍል ሃላፊ ነው ። ወደዚያ ሄደሽ ሌሎቹን ተወዳዳሪዎችሽን በማሸነፍ ሥራውን ልታገኚ ትችያለሽ" አለቻት ።

ካተሪን ተጣድፋ ወደተባለው ሥፍራ ተጓዘች ። ፍሬዘር ከሚገኝበት ቢሮ የመስተንግዶ ክፍል ብዙ ተወዳዳሪዎች ተኮልኩለው አየች ። 'ዕድሉን የማገኝ አይመስለኝም' ስትል አሰበች ። የውስጠኛው ቢሮ በር እንደተከፈተ ዊልያም ፍሬዘር ወጣ ። ረዘም ያለ ፣ ወርቅማ ፀጉር ያለው ፣ የዓይኑ ብሌን ወደ ብሩህ ሰማያዊነት የሚያደላ ፣ የፈረጠመ መንጋጋ ያለው ዓይነ—ግብ ሰው ነው ።

ለአስተናጋጅዋ "የላይፍ መጽሔት አንድ ቅጅ እፈልጋለሁ ። ከሦስት ወይም ከአራት ሳምንት በፊት የወጣውን እትም ። በሽፋኑ ላይ የስታሊን ፎቶግራፍ አለበት ።" አላት ።

"እንዲመጣ አዛለሁ ሚስተር ፍሬዘር" ብላ መለሰች አስተናጋጅዋ።

"ሳሊ ፣ ሴናተር ቦራህ በስልክ መሥመር ላይ ስላሉ ከዚያ እትም ላይ አንዱን አንቀጽ ላነብላቸው እፈልጋለሁ ። መጽሔቱን በሁለት ደቂቃ ውስጥ ልታገኚልኝ ይገባል ።" ተመልሶ ወደቢሮው ገብቶ በሩን ዘጋ ።

አመልካቾቹ እርስ በእርስ እየተያዩ ትከሻቸውን ይነቀንቃሉ ።

ካተሪን እዚያው ቆማ አሰበች ። ዞራም ከቢሮው ወጣች ። ከተወዳዳሪ ሴቶቹ መካከል አንዷ "ጐሽ ፣ አንድ ተፎካካሪ ተቀነሰ" ስትል ካተሪን ሰማቻት ።

ከሦስት ደቂቃዎች በኋላ ካተሪን በሽፋኑ ላይ የስታሊን ፎቶግራፍ ያለበትን የላይፍ መጽሔት አንድ ኮፒ ይዛ ተመለሰችና ለአስተናጋጅዋ ሰጠች ። ከአምስት ደቂቃ በኋላ ወደ ዊልያም ፍሬዘር ቢሮ ተጠርታ ገብታ ቆሞ አለች ።

"መጽሔቱን እንዳመጣሽው ሳሊ ነገረችኝ ።"

"አዎ ጌታዬ"

"ከወጣ ሦስት ሳምንት ያለፈውን መጽሔት በቦርሳሽ ውስጥ ይዘሽው እንደማትዞሪ መቼም እርግጠኛ ነኝ ።"

"በቦርሳዬ ውስጥ አልነበረም ጌታዬ"

"ታዲያ እንዴት በፍጥነት ልታገኚው ቻልሽ ?"

"ወጥቼ ወደፀጉር አስተካካይ ቤት ሄድኩ ። ፀጉር አስተካካዮችና የጥርስ ሐኪሞች ዘንድ ብዙ ጊዜ የቆየ መጽሔት ይገኛል ።"

"ለሁሉም ነገር እንዲሁ ፈጣን የማሰብ ችሎታ አለሽ ?"

"የለኝም ጌታዬ"

"እስቲ እናየዋለን" አላት ዊልያም ፍሬዘር ። ተቀጠረች ።

ካተሪን ከፍሬዘር ጋር መሥራቱ በጣም ደስ አሰኛት ። ሰውዬው ወንደላጤ ሲሆን ከሰዎች ጋር ጥሩ የመግባባት ችሎታ ያለውና ሀብታም ነው ። በዚህም የተነሳ በዋሽንግተን ውስጥ ከብዙ ሰዎች ጋር ይተዋወቃል። የታይም መጽሔትም "የዓመቱ ብቃት ያለው ወንደላጤ" ብሎታል ።

ካተሪን ከዊልያም ፍሬዘር ጋር መሥራት በጀመረች በስድስተኛው ወር ሁለቱም በፍቅር አበዱ ።

ካተሪን በመኝታ ቤቱ ውስጥ ፣ "አንድ ነገር ልነግርህ እፈልጋለሁ ፤ ድንግል ነኝ" አለችው ። ፍሬዘር በመገረም ጭንቅላቱን አወዛወዘ ። "የማይመስል ነገር ! ዋሽንግተን ከተማ ውስጥ ያለች አንዲቷ ድንግል እንዴት ልታጋጥመኝ ትችላለች ?"

አንድ ቀን ዊልያም ፍሬዘር ካተሪንን እንዲህ አላት፡— "ለአየር ኃይል ተቀጣሪዎች መመልመያ የሚሆን ፊልም ሆሊውድ ውስጥ በኤም ጂ ኤም እስቱዲዮ ስለሚቀረጽ መሥሪያ ቤታችን ሥራውን እንዲከታተል ተጠይቀናል ። እኔ ለንደን ስለምሄድ አንቺ የዚህን ሃላፊነት እንድትወስጂ እፈልጋለሁ ።"

"እኔ እንዴት ብዬ ፣ እኔኮ በፎቶግራፍ ማንሻ ውስጥ ፊልም ማጉረስ እንኳን አልችልም ። ስለማሰልጠኛ ፊልም አሠራር ምን የማውቀው ነገር አለ ?"

ፍሬዘር ኮስተር አለ ። "ማንኛውም ሰው የሚያውቀውን ያህል



ታውቂያለሽ ። የሚያሳስብሽ ነገር የለም ። የፊልም አዘጋጅ አላቸው ። አላን ቤንጃሚን ይባላል ። ሠራዊቱ ከሲቪሉ ወገን ተዋንያን ለመምረጥ ሃሣብ አለው ።"

"ለምን ?"

"ወታደሮች የወታደርን ገፀ—ባሕርይ ወክለው ቢጫወቱ ትወናው ተዓማኒነት አይኖረውም ብለው በመገመታቸው ይመስለኛል ።"

"ይሄ ወታደራዊ አመለካከት ይመስላል"

ካተሪን የማሰልጠኛውን የፊልም ቀረፃ ለመከታተል ወደ ሆሊውድ በረረች ።

የድምፅ ማቀናበሪያው መድረክ የወታደር መለዮዎችን አንጋደው በለበሱ ሰዎች ተሞልቷል ።

"ይቅርታ" አለችው ካተሪን አጠገቧ ያልፍ የነበረውን ሰው ። "ሚስተር አላን ቤንጃሚን እዚህ ይገኝ ይሆን ?"

"ትንሹ ያሥር አለቃ ?" በጣቱ አመለከተ ። "ያው እዚያ ።"

ካተሪን ዞር እንዳለች ክንዱ ላይ የአሥር አለቃ ምልክት የለጠፈ ኰስማና ሰው አየች ። የአሥር አለቃው የጄኔራልን ኮከብ በደረደረው ሰው ላይ ይጮህበታል ።

"የማይረባ የተዋናይ መልማይ ሁሉ ያለህን እርሳው ። እኔ ስለጀኔራሎች አብጠርጥሬ ነው የማውቀው ። ማንም እንዲህ አድርግ እንዲለኝ አልፈልግም ።" በቅሬታ እጁን በማወራጨት "ሁሉም አለቃ ልሁን ባይ ነው ። ተራ ሆኖ ለመሥራት የሚፈልግ የለም" አላት ።

"ይቅርታ" አለች ካተሪን ። "ካተሪን አሌክሳንደር እባላለሁ ።"

"ተመስገን አምላኬ" አላት አጭሩ ሰውዬ ። "በይ ሥራውን ተረከቢኝ ። ምን እንደማደርግ ግራ ገብቶኝ ነበር ! ዶርቦርን ሳለሁ በዓመት ሦስት ሺህ አምስት መቶ ዶላር እየተከፈለኝ የጠረጴዛና የመቀመጫ ንግድ የማስታወቂያ መጽሔቶች አዘጋጅ ሆኜ እሰራ ነበር ። ከዚያ በወታደራዊ መገናኛ ክፍል ባልደረባነት መልምለውኝ ለማሠልጠኛ ፊልም የሚሆን ጽሑፍ እንዳዘጋጅ ላኩኝ ። እኔ ስለፊልም አቅርቦት ሆነ ዝግጅት ምን የማውቀው ነገር አለ ? ይሄ የአንቺ ተግባር ነው ።" ካተሪንን ካለችበት ትቷት ተጣድፎ ወደበሩ ገሠገሠ ።

ከወደፀጉሩ የሸበተ ሹራብ የለበሰ ቀጭን ሰው ወደርሷ ቀርቦ የመገረም ፈገግታ አሳያት ። "እንድረዳሽ የምትፈልጊው ነገር አለ ?"

"የምፈልገው ተአምር እንዲወርድልኝ ነው" አለች ካተሪን ። "የፊልሙን ሥራ በበላይነት እንድመራ ተልኬአለሁ ። ግን እንዴት እንደሚሠራ የማውቀው ነገር የለም ።"

ፈገግ አለ ። "እንኳን ወደሆሊውድ በደህና መጣሽ ። ቶም አብሪን እባላለሁ ። ረዳት የፊልሙ አዘጋጅ ነኝ ።"

"ይህንን ፊልም ለማዘጋጀት የምትችል ይመስልሃል ?"

ከንፈሩ ሲንቀሳቀስ አየች ። "እሞክራለሁ ። ከዊሊ ዋይለር ጋር ስድስት ፊልሞች ሠርቻለሁ ። የሚፈራውን ያህል አስቸጋሪ አይደለም ። ትንሽ ቅንብር ነው የሚያስፈልገው ፤ ጽሑፉና መቸቱ ተጠናቀዋል ።"

ካተሪን ወደ ድምፅ ቅንብሩ መድረክ ተመለከተች ። "ከእነኚህ የወታደር አልባሳት ውስጥ አንዳንዶቹ የተስተካከሉ አይደሉም ። የተሻለ ነገር ለማድረግ እንሞክር እስቲ !"

አብሪን ጭንቅላቱን በማወዛወዝ ተስማማ ። "ትክክል ነሽ" አላት ።

ካተሪንና አብሪን ወደተዋንያኑ ሄዱ ።

በሰፊ መድረክ ላይ የሚሰማው ጫጫታ ጆሮን ያደነቁራል ።

"ጫጫታውን እናቁም ጐበዝ" አለ አብሪን ትዕዛዝ በተመላበት አነጋገር ። "የምታዩዋት ሚስ አሌክሳንደር ትባላለች ። እዚህ የሚካሄደ ውን ሥራ በበላይነት የምትመራና የምትቆጣጠር እርሷ ናት ።"

ካተሪን "እስቲ በደንብ እንድናያችሁ እንዴ ተሠለፉ" አለች ።

አብሪን በወጣገባ መሥመር አሰለፋቸው ። ካተሪን ሳቅና ሹክሹክታ እንደሰማች ተናዳ ዞር አለች ። አንድ ዩኒፎርም የለበሰ ተዋናይ ለትዕዛዙ ደንታ ሳይኖረው ከጥግ ቆሞ ልጃገረዶችን እያሳቀ ይበቃል ። የሰውዬው ሁኔታ ካተሪንን አበሳጫት ።

"ይቅርታ ፣ እንዴ ወዲህ ትመጣልን ?"

ዞር ብሎ በግዴለሽነት "እኔን ነው ?"

"አዎ ፣ ሥራውን ቶሎ ለመጀመር እንፈልጋለን ።"

ሰውዬው ከመጠን በላይ መልከ መልካም ነው ። ረዥምና ቁመናው ያማረ ሲሆን የሚያማምሩ ዓይኖቹ ብሌን ጠቆር ያለ ሆኖ ፣ ፀጉሩ ጥቁር ሰማያዊ ነው ። የደንብ ልብሱ ተስማምቶታል ። በትከሻው ላይ



የሻምበልነት ምልክት ይታያል ። ደረቱ ላይ የተንጠለጠሉት ሜዳሊያ ዎች ያብረቀርቃሉ ። ካተሪን አተኩራ አየችው ። "እነኚህ ሜዳሊ ያዎች ..."

"ይህን ያህል የሚማርኩ ናቸው ?" የፌዝ አነጋገር ነበር ።

"ብታወልቃቸው ይሻላል"

"ለምን ? ለፊልሙ የበለጠ ድምቀት ይሰጠዋል ብዬ ስላሰብኩ ነው ያደረግኩት ።"

"አንድ የዘነጋኸው ነገር አለ ። አሜሪካ እስካሁን ድረስ በጦርነት ረመጥ ውስጥ አለመግባቷን ረስተሃል ። ታዲያ ይህን ሜዳሊያ የተሸለም ከው በመዝናኛ በዓልዋ ላይ ነው ?"

"እዚህ ላይ ልክ ነሽ ። ይህን ልብ አላልኩም ነበር ። እሺ ከላዩ ትንሽ እነሳለታለሁ ።"

"ሁሉንም አውልቃቸው" አለች ካተሪን በቁጣ ።

የጠዋቱ የፊልም ቀረፃ ሥራ ተጠናቆ ካተሪን በስቱዲዮው አካባቢ ባለው ካፊቴሪያ ውስጥ ቁጭ ብላ ምሳዋን ስትመገብ ወደ እርሷ ቀርቦ "ዛሬ ጠዋት ሥራዬ እንዴት እንደነበረ ልጠይቅሽ ብዬ ነው የመጣሁት ። አተዋወኔ ተዓማኒነት ነበረው ?" አላት ።

ሥነ ሥርዓቱ አስፈራት ። "አንተን ደስ የሚልህ ያንን የደንብ ልብስ ለብሰህ ልጃገረዶች አጠገብ መንጐራደድ ብቻ መሰለኝ ። ለመሆኑ ወታደር ለመሆን አስበህ ታውቃለህ ? ።"

ደንገጥ አለ ። "በናይት ለመሞት ? ሥራ የሞኞች ነው ።"

ካተሪን በንዴት ገነፈለች ። "ቅሌታም ትመስለኛለህ !"

"ለምን ?"

"ለምን እንደሆነ አላውቅም ለምን እንደሆነ ልነልፅልህ አልች ልም !"

"ለምን አትሞክሪም ? ዛሬ እራት ጋብዘሽኝ ለምን አትነግሪኝም ። እቤትሽ ልምጣ ። ለመሆኑ ምግብ የማብሰል ሙያ አለሽ ?"

"ከእንግዲህ ወደሥራ ቦታ ተመልሰህ ለመምጣት እታስብ" አለችው ካተሪን ። "ዛሬ ጠዋት ለሠራኸው ሥራ ክፍያ ሚስተር አብሪን ቼክ እንዲልክልህ እነግረዋለሁ ። ለመሆኑ ስምህ ማነው ?"

"ዱግላስ ፣ ላሪ ዱግላስ ።"

ወጣቱ ተዋናይ ያሳያት የብልግና ጠባይ ካተሪንን ቢያሳስባትም ቅሬታዋን ለመርሳት ወሰነች ። ሆኖም ባላወቀችው ምክንያት ጉብሉን ከአእምሮዋ ለማውጣት ተሳናት ።

ካተሪን ወደ ዋሽንግተን እንደተመለሰች ዊልያም ፍሬዘር "እንዴት ናፍቄሽ ነበር መሰለሽ? ስለ አንቺ ብዙ ሳስብ ነበር ። ትወጂኛለሽ?" አላት ።

"በጣም አድርጌ ነዋ ቢል !"

"እኔም እወድሻለሁ ። ዛሬ ማታ አብረን ወጥተን ለምን አንደ ሰትም ?"

ካተሪን ያን ዕለት ምሽት ቢል ለጋብቻ እንደሚጠይቃት አስቀድማ አውቃለች ።

ልዩ ወደሆነው የጄፈርሰን ክለብ ሄዱ ። እራት በመብላት ላይ ሳሉ ላሪ ዱግላስ የአየር ኃይል የደንብ ልብሱን ለብሶ ፣ ሜዳሊያዎቹን ደርድሮ ብቅ አለ ። ወደነሱ ሲያመራ ካተሪን ዓይኗን ማመን ተሳናት ። ለእሷ ሰላምታ ሳይሰጥ ፍሬዘርን ነበር የጨበጠው ።

ቢል ፍሬዘር ከተቀመጠበት ተነሳና "ካቲ ፣ ተዋወቂ ። ሻምበል ሎውሬንስ ዱግላስ ይባላል ። ላሪ ፣ እሷም ሚስ አሌክሳንደር ካተሪን ትባላለች ። ላሪ የሮያል አየር ኃይል አብራሪ ነው ። የአሜሪካ የጦር አውሮፕላን ቡድን መሪም ነበር ። ልጆቻችንን ለጦርነቱ ለማዘጋጀት ዋሽንግተን ውስጥ የጦር ሠፈር እንዲያቋቁም ኃላፊነቱን የወሰደ እሱ ነው ።"

ያረጀ ፊልም ወደኋላ እንደሚጠነጠን ሁሉ ካተሪን በሃሳቧ ወደኋላ ተመልሳ ሜዳሊያዎች እንዲያወልቅ ስታዘውና እርሱም በፈገግታ ሲታዘዛት ታወሳት ። ያሳየችው ንቀትና "ፈሪ" ብላ በተዘዋዋሪ የሰደበችው አሳፈራት ። ተጠቅልላ ጠረጴዛ ሥር ብትገባ አትጠላም ነበር ።

በሚቀጥለው ቀን ላሪ ዱግላስ ካተሪን ቢሮ ስልክ ደወለ ። ልታነጋግረው ግን ፈቃደኛ አልሆነችም ። ሥራዋን ጨርሳ ስትወጣ እውጭ ቆሞ ጠበቃት ። ሜዳሊያዎቹን አውልቆ የምክትል መቶ አለቃ ልብስ ለብሷል ።

ፈገግ እያለ ተጠጋት ። "አሁንሳ ፣ እንዲህ አይሻልም ?" ብሎ ጠየቃት ።

ካተሪን ትኩር ብላ አየችው ። "አግባ ... አግባብ ያልሆነውን የደንብ ልብስ መልበሱ ከሕግ ውጪ አያሰኝም ?"

"እኔ እንጃ ። ይሄ ሁሉ በኃላፊነት የሚመለከተው አንቺን መስሎኝ ።"

ትኩር ብላ እንዳየችው አንድ ልብ የሚሰውር ነገር እንዳለው ተሰማት ። ሊቋቋሙት የማይችሉት ማግኔታዊ ስበት ከውስጡ ይፈል ቃል ።

"ከእኔ የምትፈልገው ምንድር ነው ?"

"ሁሉንም ። የምፈልገው አንቺን ነው ።"

ወደ አፓርትመንቱ ሄዱና ፍቅር ሠሩ ። ያልገመተችውን ልዩ እርካታና ደስታ ነበር ካተሪን ያገኘችው ። ተያይዞ በፍቅር ልዩ ዓለም ውስጥ መንጐድ ። ምልዐተ ዓለምን የሚነቀንቅ ምትሐት ውስጥ መስጠም ፣ ማለቂያ የሌለው ጥልቅ ፍንደቃን የሚያስከትል ፍንዳታ ፤ ሰውነትን ከሚያነካክትና ከሚያደቅ ረዥም ጉዞ ደርሶ መልስ ። ከመጨረሻ ደረስኩ ሲባል እንደገና ወደ መጀመሪያው መመለስ ። እንዳይሄድ ባት፣ ስሜቱ እንዳይደክምባት ከተኛበት ተጠመጠመችበት ።

ከአምስት ሰዓት በኋላ በሜሪላንድ ጋብቻቸውን ፈጸሙ ።

አዲሱን ሕይወቷን ለመጀመር በአይሮፕላን ወደለንደን ስትጓዝ ካተሪን እንዲህ እያለች ታስብ ነበር፡ በጣም ደስተኛ እንኳን ነበር ። ታዲያ ምን አበላሽው? የፍቅር ፊልሞችና የፍቅር ዘፈኖች ፣ ስለፍቅር የሚያወሳው ነገር ፍፃሜው ያማረ ፣ ፍቅርና የጦር መሣሪያ የታጠቀ ወታደር እንደማይሞት አስመስለው በማታለል አሳምነውናል ። የደምስን የሚያስደስት ሕይወት እንዳየን ስቴምርት እና ዶና ሪድ በእውነትም ደስ የሚል ኑሮ የሚኖሩ ናቸው ብለን ተቀብለናል ። "አንድ ማታ እንዲህ ሆነ" የሚለው ፊልም እንዳለቀም ክለርክ ጋብልና ክልውዳት ክልበርት ለዘለዓለም በፍቅር እንደሚቆዩ ገመትን ። "የሕይወታችን ቆንጆው ዘመናት" በሚለው ፊልም ውስጥ ፍሬድሪክ ማርች ከሚርና ሎይ ጋር ሲታረቅ እንባችንን አፍሰናል ። በሬቤካ ፊልምም ውስጥ ጆአን ፎንቴን በሎሬንስ ኦሊቭር እቅፍ ውስጥ ሳለች ደስታ ለማግኘቷ አልተጠራጠርንም ነበር ። ግን ይሄ ሁሉ ውሸት ነው ። ሁሉም ውሸት ። ዘፈኖቹስ ቢሆኑ እወድሻለሁ ለዘለዓለም ። እስኪ ዘለዓለም መውደድን በምን ይለኩታል ? መስፈርት አበጅተውለታል ? የውቅያኖስ ጥልቀቱ ምን ያህል ነው? እስቲ ኸርሺንግ በርሊን ምን ማለቱ ይሆን ? አንድ ጫማ ርቀት ? ወይንስ ሁለት ጫማ ርቀት እንዲባል ፈልጎ ነው ? ... መሄዴ ነው ። ሰማንያዬ እንዲቀደድ እፈልጋለሁ ። ምን ማለትሽ ነው ? ይልቅስ ቶዝሽን ተራራ ላይ ለሽርሽር እንውጣ ። አንተ ፣ ያ ሌሊትና ሙዚቃ ። የሆቴሉ ሥራ አስኪያጅ ባጠገባችን ያለውን ቀሻ ስለሚመስለው ቀሻ

አሚወተኝ … ስሜቴን ስለነካህ ነው የምወድህ ። ማንም ቢሆን … አሁን እንቅልፍ ላይ እያለች ። ፍቅርዬ እዚሁ ሁኚ ። አብረን ሙዚቃ ሰማን ፤ ሲኒማ አየን ። ሕይወትን በትክክል ያሳዩን ይመስል። ባሌ ላይ ከፍተኛ እምነት ነበረኝ ። አሁን ሌላ ሰው ማመን እችላለሁ ? ግን ምን አድርጌው ነው እንደዚያ ሊያርደኝ የፈለገው ።"

"ሚስ አሌክሳንደር …"

ካተሪን በብዥታ ውስጥ ሆና በድንጋጤ ቀና አለች ።

አውሮፕላን ነጂው ከአጠገቧ ቆሟል ። "በሰላም ደርሰናል ። እንኳን በደህና ወደለንደን ገባሽ ።"

በአውሮፕላን ማረፊያው ሊሞሲን መኪና ቆሞ ካተሪንን ይጠብቃል ። ሹፌሩም "ሚስ አሌክሳንደር ሻንጣሽንም እኔው እይዝልሻለሁ ። ስሜ አልፍሬድ ይባላል ፤ በቀጥታ ወደቪላሽ ለመሄድ ትፈልጊያለሽ ?" ብሎ ጠየቃት ።

'ቪላዬ!' "መልካም ይሻላል ።"

ካተሪን ተመቻችታ ተቀመጠች ። ያጋጠማትን ሁሉ ለማመን አስቸግሯታል ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ የግል አውሮፕላን ለብቻዋ መድቦላት መኖሪያ ቤትም አዘጋጅቶላታል ። የመጨረሻው ደግ ሰው ነው፤ ወይንም…። ሌላ አማራጭ ስላልነበረው ነው ። 'የለም ፣ የለም ፡ በዓለም ውስጥ ተወዳዳሪ የማይገኝለት ደግ ሰው ስለሆነ ለእሱ ያለኝን አድናቆትና ምስጋናዬን የምገልጽበት አንድ አመቺ ዘዴ መፈለግ ይኖርብኛል ።' አለች ።

በኤሊዛቤት ጎዳና ላይ ከሚገኘው የኢቶን አደባባይ አካባቢ ያለው ቪላ በጣም ምቹት አለው ። እውስጥ ሲገባ እንደሳሎን የሚያገለግለው ሰፊው አዳራሽ በፎቴና በወንበሮች ያጌጠ ነው ። የሳሎኑ ግድግዳ እንደመስታወት በሚያብረቀርቁ ውድ ድንጋዮች የተሠራ ነው ። ውብ የሆነ ባለጌጥ መብራትም ቊንጠልጥሎ ይታያል ። ቤቱ የተሟላ ቤተመጻሕፍት ፣ ምግብ የተትረፈረፈበት ኩሺና ፣ በጣም ያማሩና የተዋቡ ሦስት መኝታ ክፍሎችና የሠራተኛ መኖሪያ ቤት አካትቷል ።

ካተሪን ወደቤቱ ገና እንደደረሰች ጥቁር ልብስ የለበሰች አንዲት ዕድሜዋ ወደ አርባው የሚገመት ሴት ከበሩ ላይ ሆና ሰላምታ አቀረበችላት ። "እንደምን ዋልሽ ሚስ አሌክሳንደር ። አና እባላለሁ ። የቤት ሠራተኛሽ ነኝ ።"

'የቤት ሠራተኛዬ?' ካተሪን ሁሉንም ነገር በእርጋታ መቀበል ጀመረች ።



"እንደምን አለሽ?"

ሾፌሩ የካተሪንን ሻንጣዎች መኝታ ቤቷ ውስጥ አስገባ ። "ሊሞሲኑን በፈለግሽ ጊዜ ልትጠቀሚበት ትችያለሽ" አላት ። "ወደቢሮ ለመሄድ ዝግጁ ስትሆኚ ለአና ንገሪያትና መጥቼ እወስድሻለሁ ።"

'ሊሞሲኑን በፈለግኩ ጊዜ መጠቀም እችላለሁ ። በሚገባ ።' "አመሰግናለሁ!" አለች ።

"ሻንጣሽን ከፍቼ ልብሶችሽን ላደራጅ ነው ። ሌላም የምትፈልጊው ነገር ካለ ንገሪኝ" አለቻት አና ።

"ለጊዜው ምንም አልፈልግም።" እውነቷን ነበር ።

አና ልብሶቹን ከሻንጣዎቹ ውስጥ አውጥታ እስክትጨርስ ካተሪን ቪላውን ተዟዙራ ጐበኘች ። ወደመኝታ ቤቷም እንደገባች ዴሚሪስ የገዛላትን የተዋቡ ልብሶች ተመልክታ 'ይህ መቼም ሕልም መሆን አለበት ።' ብላ አሰበች ። 'የምታየውን ሁሉ ለማመን ተሳናት ። ከአርባ ስምንት ሰዓታት በፊት በሴቶቹ ገዳም ውስጥ የሮዝ አበቦችን ውሀ ታጠጣ እንዳልነበረ ሁሉ አሁን ደግሞ የልዕልት ኑሮ ትኖራለች ። 'ሥራው ምን ዓይነት ይሆን' ብላ አሰበች ። ደግ ሰው ስለሆነ በደንብ እሠራለሁ ። ጨርሶ አላሳፍረውም ።' አለች በልቧ ። ድካም ተሰምቷት ከምቹው አልጋ ላይ ጋደም አለች ። 'እስቲ ትንሽ ልረፍ' ብላ ዓይኗን ከደነች ።

ውሃ ሊበላት ሲል የድረሱልኝ ጩኸት አስተጋባች ። ላሪ እየዋኘ አጠገቧ ደርሶ ወደውስጥ ደፈቃት ። በጨለማ ዋሻ ውስጥ ነች ። የሌሊት ወፎች ፀጉሯን ለመንጩት ይሞክራሉ ፤ በዚያ አስቀያሚ ክንፋቸው ፊቷን ያሎሉ ። ካተሪን በድንጋጤ ከእንቅልፏ ነቅታ አልጋዋ ላይ በመቀመጥ መንዘፍዘፍ ጀመረች ።

እራሷን ለማረጋጋት ብላ አየር ወደውስጥ ሳበች ። 'አብቅቷል' አለች በአሳቧ ። 'ያከትማል ። ያ ትላንት ነው ። አሁን ደግሞ ዛሬ ነው ። ማንም ሰው ሊጎዳኝ አይችልም ። ማንም ሰው ።'

ጩኸቷ ከመኝታ ክፍሏ አልፎ ለቤት ሠራተኛዋ ለአናም ተሰማት ። ጩኸቱ እንዳበቃ ሁኔታውን ለኮንስታንቲን ዴሚሪስ ለማሳወቅ አና ወደ ሳሎኑ ገብታ ስልክ አነሳች ።

ሄሌኒክ የንግድ ኮርፖሬሽን የሚገኘው ከፒካዴሊ ራቅ ብሎ ፣ በ217 የቦንድ ጐዳና ላይ በሚገኘው ፣ በቅርቡ ወደቢሮነት በተለወጠው አሮጌው የመንግሥት ሕንፃ ውስጥ ነው ። የሕንፃው የውጭ ክፍል በጣም የተዋበ የአርኪቴክት ውጤት ሲሆን ዓይን የሚስብና ልብ ደንገጥ የሚያደርግም ነው ።

ካተሪን ወደዚህ ሥፍራ ስትደርስ የቢሮ ሠራተኞቹ ተሰብስበው እርሷን በመጠባበቅ ላይ ነበሩ ። ጥቂት ሰዎች ሊቀበሏት ተሰልፈው ከበሩ ላይ ቆመዋል ።

"እንኳን ደህና መጣሽ ፣ ሚስ አሌክሳንደር ። ኤቬሊን ኬይ እባላለሁ። እነኚህም ካርል ... ታከር... ማቲው... ጃኒ..."

ስሞቹና ፊቶች በዙባት ።

"ጤና ይስጥልኝ ።"

"ቢሮሽ ተዘጋጅቷል ። ወደዚያው ልውሰድሽ?"

"አመሰግናለሁ ።"

የእንግዳ መቀበያው ክፍል በሚያማምሩ ወንበሮች ተሞልቷል ። ምንጣፍ በተነጠፈበት ረዥም ኮሪዶር በኩል አልፈው በቆዳ መቀመጫ ዎች ወዳማረ ሰፊ ቢሮ ገቡ ።

"ይህ ያንቺ ነው ።"

"በጣም ደስ ይላል" አለች ድምጿን ዝቅ አድርጋ ።

በጠረጴዛው ላይ ትኩስ አበቦች አየች ።

"ከሚስተር ዴሚሪስ የተላከ"

'በጣም የሚያስብልኝ ሰው ነው' አለች በልቧ ።

ቢሮውን አዙራ ያስጐበኘቻት ኤቬሊን ኬይ ፣ ደልዳላ ሰውነትና ድንቡሽቡሽ ፊት ኖሯት በመካከለኛ ዕድሜ ላይ የምትገኝ ጠባየ ሸጋ ሴት ናት ።

"ለመልመድ ጥቂት ቀናት ይወስድብሽ ይሆናል ፣ ሥራው ግን በጣም ቀላል ነው ። ቢሆንም ለዚያ ሁሉ የዴሚሪስ የሥራ መስክ የነርቭ ማዕከሎቹ እኛ ነን ማለት ይቻላል ። ከመላ ዓለም የሚመጡ ሪፖርቶችን አቀነባብረን አቴንስ ወደሚገኘው ዋናው መሥሪያ ቤት እናስተላልፋ ለን። እኔ የቢሮው ኃላፊና ሥራ አስኪያጅ ስሆን አንቺ ደግሞ የእኔ ረዳት ትሆኚያለሽ" አለቻት ኬይ ።

'አሃ' አለች ካተሪን በአሳቧ ። 'እና የሥራ አስኪያጅ ረዳት ሆንኩኝ



ማለት ነው?' ካተሪን ከእርሷ ምን እንደሚጠበቅ አታውቅም ። ደግሞ ሁሉም የሕልም ዓለም ይመስላታል ። የግል አውሮፕላን ፣ ሊሞሲን መኪና ፣ ያማረ ቪላ ፣ የቤት ሠራተኛ...

"ዊም ቫንዲን ልዩ ተሰጥኦና ችሎታ ያለው የሒሳብ ሠራተኛችን ነው ። ወጪና ገቢውን በዋናው የሒሣብ ማጠናቀሪያ መዘርዝር ላይ የሚያሰፍረው በጭንቅላቱ እያሰላ ነው ። እንኳሉ ከብዙዎቹ የሒሳብ ማስሊያ መሣሪያዎች በበለጠ ፍጥነት ይሠራል ። ወደቢሮው ልውሰድሽና ተዋወቂው ።"

በኮሪዶሩ አልፈው ከአዳራሹ ቀጥሎ ከጥግ ካለው ቢሮ ደረሱ ። ኤቬሊን ሳታንኳኳ የቢሮውን በር ከፈተች ።

"ዊም ፣ ከአዲሷ ረዳቴ ጋር ተዋወቁ ።"

ካተሪን ቆማ ቀረች ። ዊን ቫንዲን በመጀመሪያዎቹ የሰላሣ ዕድሜ አካባቢ የሚገኝ ሲሆን ቀጠን ብሎ ሾል ያለ አገጭ ያለው ፈዛዛ መሳይ ሰው ነው ። ጐንበስ ብሎ እግሩን እያየ ነበር ።

"ዊም ፣ ዊም! ከካተሪን አሌክሳንደር ጋር ተዋወቁ"

ቀና አለና በማይጨበጥ ፍጥነት መናገር ጀመረ — "የመጀመሪያው ካተሪን የሚል ስም የማርታ ስኮውሮንካ ስም ነበር ። በ1684 የተወለደ ችው ይህች ሴት በሩሲያኖች ተማርካ የቤት ሠራተኛ ሆነች ። ቀዳማዊ ፒተርን አግብታ ከ1725 እስከ 1727 የመጀመሪያዋ የሩሲያ ንግሥት ሆነች ። የጀርመን ልዑል ልጅ የነበረችው ታላቋ ካተሪን ደግሞ በ1729 ተወለደች ። ኋላ በ1762 ንጉሥ ፒተርን አገባችና እርሱን በማስገደል ዙፋኑን ወሰደች ። በእርሷ አገዛዝ ወቅት ፖላንድ በሦስት ተከፍላ ነበር ። ከቱርኮች ጋር የተካሄደ ጦርነትም መርታለች ። ..." ንግግሩ ሳያቋርጥ እንደፏፏቴ ይወርድ ነበር ።

ካተሪን ፈዝዛ ቀረች ። "... የሚገርም ነው ።" የሚለውን ቃል እንደምንም ለመናገር ተሳካላት ። ዊም ቫንዲን ተመልሶ አቀረቀረ ። ኤቬሊን "ዊም ዓይናፋር ነው" አለቻት ።

'ዓይናፋር' አለች ካተሪን በልቧ ። "የሚያስገርም ፍጡር ነው ። ልዩ የሆነ ብሩህ አእምሮ ያለው ።"

ኰንስታንቲን ዴሚሪስ አቴንስ ውስጥ በአጊኡ ጀሮንዳ ጐዳና ላይ

በሚገኘው ቢሮው ውስጥ ተቀምጦ አልፍሬድ ከለንደን በስልክ የሚያስተላልፍለትን ሪፖርት ያዳምጣል ።

“ሚስተር ዴሚሪስ ፤ ሚስ አሌክሳንደርን ከአውሮፕላን እንደወረደች በቀጥታ ወደማረፍያዋ ነው የወሰድኳት ። እርሷንም ባዘዙኝ መሰረት ሌላ ቦታ ለመሄድ ትፈልግ እንደሆን ጠይቄያት ነበር ። የትም ለመሄድ እንዳልፈለገች ነገረችኝ ።”

“ሌላ የምትተዋወቀው ሰው የለም ማለት ነው?”

“አይ ፤ ጌታዬ ። ምናልባት ካረፈችበት ቤት ሆና የስልክ ግንኙነት የምታደርግ ካልሆነ በቀር እስካሁን ምንም የለም ።”

እና ፤ የቤት ሠራተኛዋ የሆነውን ነገር ሁሉ ስለምትነግረው ኰንስታንቲን ዴሚሪስ ብዙም አልተጨነቀበትም ። በሰማው ሪፖርት ረክቶ ስልኩን ዘጋው ። ለጊዜው አደጋ የምታስከትል መስሎ ባይታየውም በዓይነ ቁራኛ ክትትል እንዲደረግባት አዟል ። በማታውቀው ዓለም ውስጥ ብቻዋን ትዋዥቃለች ። ከአጋዧና ከረዳቷ ከኮንስታንቲን ዴሚሪስ በቀር ምንም የላትም ። ‘ወደለንደን ለመጓዝ በቶሎ መዘጋጀት አለብኝ’ አለ ዴሚሪስ ደስታ እየተሰማው ። ‘ባስቸኳይ ።’

ካተሪን አሌክሳንደር አዲሱ ሥራዋ የሚያስደስታት ሆኖ አግኝታዋለች ። በርካታ ሪፖርቶች በዓለም ዙሪያ ከሚገኙ የኮንስታንቲን ዴሚሪስ ድርጅቶች በየዕለቱ ይጐርፋሉ ። ኢንዲያና ከሚገኘው የብረት ኢንዱስትሪ የተላከ የማስጫኛ ክፍያ ሰነድ ፤ ኢጣሊያ ካለው የአውቶሞቢል ኢንዱስትሪ የመጣ የኦዲት ሪፖርት ፤ አውስትራሊያ ከሚገኝ የጋዜጣ አሳታሚ ድርጅት ፤ ከወርቅ ማዕድናትና ከኢንሹራንስ ኩባንያዎች የመጡ በርካታ የሽያጭ ዘገባዎችን የመሳሰሉት ። ካተሪን ይህን ሁሉ ሰብስባ በቀጥታ ለዊም ቫንዴን ትልካለች ። ሪፖርቶቹን ሁሉ ወዲያው ያነባቸውና እንደ ኮምፒዩተር በሚሠራው ጭንቅላቱ ሽምድዶ በማውጠንጠን ኩባንያውን የገጠመውን የትርፍና የኪሳራ ስሌት በቃሉ ያወጣል ።

ካተሪን ከሥራ ባልደረቦቿ ጋር በመተዋወቋና የምትሰራበት የሕንጻ ውበት ደስ አሰኛት ።

በተለይም ስለሕንጻው የተሰማትን ባንድ ወቅት ዊም ባለበት ለኤቬሊን ኬይ አንስታ ስትናገር ዊምም “ይህ ሕንጻ የመንግሥት



የጉምሩክ ቢሮ ነበር ። በ1721 የሕንጻው ዲዛይን የተነደፈው ሰር ክሪስቶፈር ሬን በተባለ ሰው ነበር ። ከለንደን የእሳት አደጋ ወዲህ ክሪስቶፈር ሬን የሃምሳ አብያተ ክርስቲያናትን ዲዛይን ነድፏል ። ከእነኚህም መካከል የቅዱስ ጳውሎስ ፤ የቅዱስ ሚካኤልና የቅዱስ ብራይድ አብያተ ክርስቲያናት ጥቂቶቹ ናቸው ። የሮያል ባንክንና የቡኪንግሃም ሃውስን ዲዛይን አቅዶ በ1723 ከዚህ ዓለም በሞት በመለየት በቅዱስ ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን መካነ መቃብር ተቀበረ ። ይህም ቤት በ1907 ወደመንግሥት ቢሮነት ተለውጦ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት መንግሥት የአየር ድብደባ መከላከያ ጣቢያ ሆኗል ብሎ አወጀ ።”

ለቦምብ የማይበገረው የአየር ድብደባ መከላከያው ሥፍራ በጠንካራው የብረት በር በኩል ታልፎ ከምድር ቤቱ ቀጥሎ ይገኛል ። ካተሪን ጠንካራውን ምሽግ አየችው ። የሂትለር አውሮፕላኖች ቦንብ እንደበረዶ በሚያዘንቡበት ወቅት በዚህ ምሽግ ውስጥ መጠለያ ይዘው የነበሩት የብሪታንያ ወንዶች ፤ ሴቶችና ሕጻናት በኅሊናዋ ታዩዋት ።

ምድር ቤቱም ቢሆን ውስጥ ለውስጥ ረዥም ሆኖ የሕንጻውን ያህል ስፋት አለው ። ሕንጻውን በሙሉ የሚያሞቅ ትልቅ ማሞቂያ ያለው እዚህ ውስጥ ነው ። ከዚህም ሌላ የኤሌትሮኒክና የስልክ መሣሪያዎችንም ይዟል። ማሞቂያው እራሱ ችግር ፈጣሪ ነው ። ብዙ ጊዜ እንዲጠግኑት ካተሪን ባለሙያዎችን አስመጥታ አስመርምረዋለች ። ግን የሚመጣው ሁሉ ነካ — ነካ አድርጎት ተሠርቷል ብሎ ይሄዳል ።

“በጣም አደገኛ ነው ማለት ነው” አለች ካተሪን “የመፈንዳት አዝማሚያ ይኖረው ይሆን?”

“አትጨነቂ ሚስ ፣ አይዞሽ አይፈነዳም ። እዚሁ ያለውን የአደጋ ጊዜ መቆጣጠሪያ ታይዋለሽ? ጥሩ ፤ ቦይለሩ ድንገት ከሞቀ እንኳ በውስጡ ያለውን እንፋሎት ወደውጭ ይለቅና ያቀዘቅዘዋል ። ችግር አይኖርም ።”

ለንደን ከተማ ውስጥ ቅዳሜና እሁድ የአስደናቂ ቲያትሮች ፤ የአስደሳች የባሌት ዳንሶችና ድንቅ የሙዚቃ ዝግጅቶች ሥዕላዊ ማስታወቂያዎች ይለጠፋሉ ። እንደነሃቻርድስና ፎይሌስ የመሳሰሉ ግሩም የመጻሕፍት መደብሮች አሉ ። በርካታ ሙዚየሞች ፤ የብርቅ ዕቃ መደብሮችና ሬስቶራንቶች በብዛት ይገኛሉ ። ካተሪን ወደ ሴሲል ኮርት ሄዳ የድንጋይና የብረት ላይ ጽሑፎች የሚሸጡበትን መደብር ጐበኘች ። ከሃሮድስ ፤ ከፎርትነም ፤ ከማሶን ፤ ከማርክና ከስፔንሰር መደብሮች

የተለያዩ ዕቃዎችን ገዛች ። እሁድም ወደሳሽይ ሄዳ ሻይ ጠጣች ።

በየጊዜው ፣ ልታስወግዳቸው የማትችላቸው አሳቦች በካተሪን አእምሮ ውስጥ መጉላላት ቀጠሉ ። ስለላሪ እንድታስብና እንድታስታውስ የሚያስገድዷት ብዙ ነገሮች ነበሩ ። ድምፅ፣...ቃላት.... የአነጋገር ዘይቤ. ... ሙዚቃ ። 'አይሆንም ያለፈው አልፏል ። ጠቃሚው የወደፊቱ ነው' ትላለች በአሳቧ ። በየዕለቱም ጠንካራ እየሆነች ሄደች ።

ካተሪንና ኤቬሊን ኬዬ ጓደኞሞች ሆኑ ። አንዳንዴም አብረው ወጣ ይላሉ ። አንድ እሁድም በቴምስ ገላጣ ሥፍራ የሥዕል ኤግዚቢሽን አዩ ። አቅራቢዎቹ በዕድሜ የገፉና ወጣት ሰዓሊያን ሲሆኑ ሥዕሎቻቸውን ሜዳው ላይ ደርድረው ነበር ለሕዝብ ያቀረቡት ። እነኚህ ሰዎች የጋራ የሆነ ነገር አላቸው ። ሁሉም ሥራዎቻቸው ተንቀባቸው በቋሚ ኤግዚቢሽን ውስጥ ለማሳየት ተቀባይነትን ያጡ ናቸው ። ሥዕሎቹ የሚረቡ አልነበሩም ። ካተሪን ለሰዎቹ ሀዘን ተሰምቷት አንዱን ሥዕል ገዛች ።

"የት ልታስቀምጪው ነው?" ስትል ኤቬሊን ጠየቀቻት ።

"ማሞቂያው ከሚገኝበት ክፍል ውስጥ" አለች ካተሪን ።

በለንደን ጐዳናዎች ላይ ሲጓዙ የመንገድ ዳር ሰዓሊዎች አጋጠሙዋቸው ። ሰዓሊዎቹ የተለያዩ ቀለም ባሏቸው ጠመኔዎች በእግረኛው መንገድ ላይ ሥዕሎችን ይስላሉ ። አንዳንዶቹ ሥራዎች ግሩም ናቸው ። በአጠገባቸው የሚያልፍ ሰው ሁሉ ቆም እያለ ሥዕሎቹን ያደንቅና ለሰዓሊዎቹ ጥቂት ሳንቲሞች ይጥልላቸዋል ። አንድ ቀን ከሰዓት በኋላ ካተሪን ምሣዋን ተመግባ ስትመለስ በጠመኔ ውብ የሆነ የመሬት አቀማመጥ ሲስል የነበረውን ሽማግሌ ለማየት ቆም አለች ። በርቶ ሊጨርስ ሲል ዝናብ መጥቶ ሥዕሉን ሲያጥበው ሽማግሌው ቆሞ የሥራውን መበላሸት ይመለከት ነበር ። 'ይህ ልክ እንዳለፈው ሕይወቴ ነው' ስትል ካተሪን አሰበች ።

ኤቬሊን ካተሪንን ወደ ቬፐርድ የዕቃ መደብር ይዛት ሄደች ። "መቼም ሥፍራውን ስታይው እንደምትወጂው እርግጠኛ ነኝ ።" ብላ ነበር ኤቬሊን ቃል የገባችላት ጉዞ ከመጀመራቸው በፊት ።



በእርግጥም ደስ የሚያሰኝ ነበር ። የሦስት መቶ ዓመታት ዕድሜ ያለው የቲዲ ዶልስ ሬስቶራንት ፣ የጦር መሣሪያ መሸጫ ፣ የቁንጅና ሳሎን፣ ዳቦ ቤት ፣ የብርቅ ዕቃዎች መደብር እንዲሁም ባለሁለትና ሦስት ፎቅ መኖሪያ ቤቶች ይገኙበታል ።

በአንዳንድ ሱቆች ላይ የተለጠፉ ስሞች ግራ የሚያጋቡ ናቸው ። አንዱ "ሄለን" ይልና ከሥሩ "የፈረንሣይኛ ትምህርት" የሚል ተጽፎበታል ። ሌላው "ሮሲ" ብሎ ዝቅ ይልና "ግሪክኛ እዚህ እናስተምራለን" ይላል ።

"ይህ የማስተማሪያ አካባቢ ነው?" ካተሪን ስትል ጠየቀች ።

ኤቬሊን ከት ብላ ሳቀች ። "ነገሩማ ይመስላል ። ብቻ እነኚህ ልጃገረዶች የሚያስተምሩት በሌላው ትምህርት ቤት የሚያስተምሩትን ትምህርት ዓይነት አይደለም ።"

ካተሪን ግራ ገብቷት ስታያት ኤቬሊን ከት ብላ ሳቀች ።

ካተሪን ብዙውን ጊዜ ብቻዋን ብትሆንም ብቸኝነት እንዳይሰማት እራሷን ሁሌ በሥራ ትጠምዳለች ። ባለፈው ሕይወቷ ያለአግባብ የባከነውን ጊዜ ለማሟላት የምትጥር ትመስላለች ። እያንዳንዱን ቀን በፀጋና በደስታ ነው የምትቀበለው ። ስላለፈውም ሆነ ስለወደፊቱ ላለመጨነቅ ወስናለች ። የዊንድሶርን ግንብ ፣ የካንተርበሪን ካቴድራልና የሃምተንን ፍርድ ቤት በየተራ ጐብኝታለች ። ቅዳሜና እሁድ ሲመጣ ወደ ገጠር ወጣ ብላ አነስተኛ ሆቴል ውስጥ ከተዝናናች በኋላ ለመናፈስ ረጅም ጉዞ ታደርጋለች ።

"ሕይወቴ እንደሆነ ተርፏል" ትላለች እራሷን ስታጽናና ። "ማንም ሰውኮ ደስተኛ ሆኖ አልተፈጠረም ። ማንም ሰው ፣ ሰው ሁሉ ፣ የእራሱን መደሰቻ እራሱ መፍጠር ይኖርበታል ። ዛሬ ወጣትና ጤናማ ነኝ ። ወደፊት ደግሞ ብሩህ ዕድል ይጠብቀኛል ።"

ሰኞ ወደሥራዋ ትመለሳለች ። ከኤቬሊን ፣ ከሌሎቹ ሴቶችና ከዊም ቫንዴንም ትገናኛለች ።

ዊም ቫንዴን እንደተአምር የሚታይ ፍጡር ነው ።

ካተሪንን ከዚህ በፊት እንደእርሱ ዓይነት ሰው አጋጥሟት አያውቅም ። በዚያች ቢሮ ውስጥ ሃያ ሠራተኞች ይገኛሉ ። ቫንዴን የሒሳብ

መማሪያ ሳይጠቀም የእያንዳንዱን ሠራተኛ የደመወዝ መጠን ፣ የኢንሹራንስ ቁጥሩን ፣ እንዲሁም ተቀናናሽ ሂሳቦችን በቃሉ ያውቃል ። የኩባንያው ሪኮርድ በፋይል የሚያዝ ቢሆንም እርሱ ሁሉንም በአእምሮው ይይዛል ። የየወሩን የገንዘብ ፍሴት በቃሉ ከማወቁ ሌላ ያሁኑን ወር ካለፈው ወር ጋርና አልፎ ተርፎም ከአምስት ዓመት በፊት ሥራ ሲጀምር ከነበረው ሂሳብ ጋር በቃሉ ማወዳደር ይችላል ።

ዊም ቫንዴን ከዚህ በፊት ያየውን ፣ የሰማውንና ያነበበውን ሁሉ የሚረሳ አይደለም ። የዕውቀት አድማሱ ድምበር የለውም ። ሆኖም ከሰዎች ጋር ያለው ግንኙነትና ቅርበት ደካማ ነው ።

ካተሪን ስለዊም ከኤቬሊን ጋር ስታወራ "እኔኮ የዊም ባሕሪይ ጨርሶ አይገባኝም" አለቻት ።

"ዊምኮ ከማናችንም የተለየ ልዩ ሰው ነው" አለች ኤቬሊን ።" ይህንን ባሕሪውን እንዳለ መቀበል አለብሽ ። እርሱን ደስ የሚያሰኙት ቁጥሮች ብቻ ናቸው ። ስለሰዎች ደንታ ያለው አይመስለኝም ።"

"ጓደኞች አሉት?"

"የሉትም ።"

"ከልጃገረድ ጋር ወጥቶ ያውቃል?"

"አይመስለኝም ።"

ዊም ብቸኛና ከሌሎች የተገለለ በመሆኑ ካተሪንን ተሰማት ። የእራሷ ወገን አድርጋም ቆጠረችው ።

የዊም የዕውቀት አድማስ ካተሪንን በጣም አስደንቋታል ። አንድ ቀን ጠዋት የጀሮ ሕመም ተሰማት ።

ዊም ጐርነን ባለ ድምፅ "ይህ የአየር ጠባይ ሕመሙን ያብሰዋል ። ስለዚህ የጆሮ ሐኪም ብታናግሪ ጥሩ ይመስለኛል" አላት ።

"አመሰግናለሁ ዊም ..."

"የጆሮ ክፍሎች" አለ ዊም እንደ ዳዊት እያምበለበለ ። "የጆሮ ክፍሎች ተቀባይ ገንዳ ፣ የጆሮ ታምቡር ፣ ጥምጥሚ ፡ መሀከለኛ ጆሮ ፣ ወዶሺት ፣ ወስፌት ፣ ሴብቻዊ ቦይ ፣ ወጭኛ ቦይ ፡ ክብ መስኮት ፡ እዩስቻት ቦይ ፣ ስሜታዊ ነርቭ ፣ እርካቢት ፣ እዝን ናቸው ።" ብሎ ዞሮ ወጣ ።

በሌላ ቀን ካተሪንና ኤቬሊን ዊምን ይዘው በአካባቢው ወደሚገኘው ራምስ ሄድ ወደተባለው አነስተኛ ሆቴል ወስደው ምሳ ጋበዙት ። ከሆቴሉ ጓሮ ጥቂት ሰዎች ግድግዳው ላይ የተሰቀለውን የዳርት ቁጥር



እየወጉ ይጫወታሉ ።

"ዊም ስፖርት ትወዳለህ?" ስትል ካተሪን ጠየቀችው ። "የቤሲቦል ጨዋታስ አይተህ ታውቃለህ?"

"ቤሲቦል" አለ ዊም "የቤሲቦል ኳስ ዙሪያ ስፋት ዘጠኝ ኢንች ከሩብ ነው ። ኳሱ የተሠራው ከሱፍ ክር ሲሆን ክሩ የተጠመጠመው በጠንካራ ላስቲክ ላይ ነው ። የኳሱ የውጭ አካልም የተሸፈነው በነጭ ቆዳ ነው ። ኳሷን ለመለጋት የሚያገለግለው እንጨት ስፋት ከሦስት ኢንች ከሩብ የማይበልጥ ፣ ርዝመቱ 42 ኢንች የሆነ ነው ።"

'መጠኑንም ጭምር ያውቃል' ብላ ተገረመች ካተሪን በአሳቧ ። 'ግን ጨዋታውን በአካል ለመጫወት ፍላጎትና ስሜት ያለው አይመስለኝም ።'

"በስፖርት ጨዋታ ተካፍለህ ታውቃለህ? ለምሳሌ በቅርጫት ኳስ"

"የቅርጫት ኳስ ጨዋታ ሊካሄድ የሚችለው በጣውላ ወይም በአስፋልት ወለል ላይ ነው ። ኳሱ የተሸፈነው በቆዳ ሲሆን የኳሱ ዙሪያ ስፋት ሰላሳ አንድ ኢንች ነው ። ከኳሱ ውስጥ የላስቲክ ፊኛ አለ ። ከፊኛው ውስጥ ያለው የታመቀው የአየር ክብደት አሥራ ሦስት ፓውንድ ይመዝናል ። የኳሱም ክብደት በአጠቃላይ ከሃያ እስከ ሃያ ሁለት አውንዝ ይሆናል ። በ1891 የቅርጫት ኳስን የፈለሰፈው ጄምስ ናኢስሚዝ ይባላል ።"

ካተሪን ለጥያቄዋ ምላሽ አገኘች ።

* * *

አንዳንድ ጊዜ ከዊም ጋር መሄድ በሰው ፊት ያሳፍራል ። አንድ እሑድ ቀን ካተሪንና ኤቬሊን ዊምን ይዘው ወደ ሜኢዴንሂድ እንደሄዱ ርቧቸው ምሳ ለመብላት ወደ ሬስቶራንት ገቡ ። አሳላፊው ወደተቀመጡበት ሥፍራ መጣና "ዛሬ ለምሳ የሚሆን ትኩስ የቀፎ ዓሣ አለን!" አላቸው ።

ካተሪን ወደዊም ዞር አለችና "የቀፎ ዓሣ ትወዳለህ?" አለችው ። ዊምም ሲመልስ፦ "የቀፎ ዓሣ ዓይነት፦ ረዥም ቀፎ ዓሣ ፡ አለትማው የሰሜን አሜሪካ ቀፎ ዓሣ ፡ ክብ ቀፎ ዓሣ ፡ ባለስለት ቀፎ ዓሣ ፡ እንዲሁም ደማም ቀፎ ዓሣ ናቸው ።"

አሳላፊው ትኩር ብሎ “የሚፈልጉትን ቢያዙ ጌታዬ !” አለው ። “ቀፎ ዓሣ አልወድም” አለ ዊም መልሶ ።

ካተሪን አብሯት የሚሠሩትን ሠራተኞች ሁሉ ወደደቻቸው ። ለዊምም ያላት ፍቅር ልዩ ነበር ። ከግምቷ በላይ ብልህና ብሩህ አእምሮ ያለው ሆኖ አይተዋለች ። ሆኖም ብቸኛና የተገለለ ነው ።

ካተሪን አንድ ቀን ኤቬሊንን “ዊም የተደላደለ ኑሮ ሊኖር የሚችልበት ሁኔታ ሊፈጠር የሚችል ይመስልሻል ? ለፍቅር ተምበርክኮ ለማግባትስ ያስብ ይሆን?” ብላ ጠየቀቻት ።

ኤቬሊን በትካዜ “ነግሬሽ ነበር ፤ ሰውዬው ውስጣዊ ስሜት የሚባል ነገር አልተፈጠረበትም ። ከማንም ጋር ልብ ለልብ ሊገጥም አይቻለውም ።”

የተናገረችውን ካተሪን አልተቀበለቻትም ። ከአንዴ ሁለቴ የፍላጎት ፤ የፍቅርና የመሳቅ ብልጭታዎችን ከዊም ፊት ላይ አንብባለች ። የሚቻላትን ሁሉ ልትረዳው ፈለገች ። ግን ግምቷ ልክ ነው ወይንስ የተሳሳተ ?

አንድ ቀን የቢሮው ሠራተኞች በሳቮይ በሚደረግ ግብዣ ላይ እንዲገኙ ጥሪ ደረሳቸው ።

ካተሪን ወደዊም ቢሮ ገባችና “ዊም ዳንስ ትወዳለህ ?” ብላ ጠየቀችው ።

ትኩር ብሎ አያት ። “ዳንስ ለመደነስ በመጀመሪያ ዋታዎቹ ...” አለና እንደልማዱ ተነተነው ። ከሙዚቃ ኖቶች አደራደር ጀምሮ በየትኛው ሙዚቃ ምን ዓይነት ዳንስ እንደሚደነስ ፤ ሰውዬው ወይንም ሴትዮዋ መጀመሪያ የሚያንቀሳቅሱትን እግር ፣ የሚከተሉትን አቅጣጫ አዘነበላት።

ካተሪን የምትናገረው ጠፍቷት ተገትራ ቀረች ። “ዝርዝሩን ሁሉ ያውቃል ፤ ምን ያደርጋል ታዲያ ትርጉሙን አያውቅ ።”

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ስልክ ደወለ ። በጣም መሽቶ ስለነበረ ካተሪን ለመተኛት እየተዘጋጀች ነው ።

“እንዳልረበሽኩሽ እርግጠኛ የሆንኩ ይመስለኛል ። ኮስታ ነኝ ።”

“አይ ፣ አልረበሹኝም ...” ድምፁን በመስማቷ ደስ አላት ። ምክሩን



ለመጠየቅም ሆነ በአጠቃላይ ከእርሱ ጋር ለመወያየት ለረዥም ጊዜ አልቻለችም ነበር ። እውነቱን ለመናገር ያለፈውን ታሪኳን በሙሉ ጠንቅቆ የሚያውቅ በዓለም ውስጥ ያለ እርሱ ብቻ ነው ። የቅርብ ወዳጇ የደወለላት መስሎ ተሰማት ።

“ካተሪን ስለአንቺ ሳስብ ነበር ። ለንደን ብቸኝነት እንዲሰማሽ የሚያደርግ ሥፍራ ይሆናል የሚል ስጋት አስጨንቀኝ ። በተለይም እዚያ የምታውቂውም ሰው ባለመኖሩ ። ”

“አንዳንዴ ብቸኝነት ይሰማኛል” ብላ ካተሪን እውነቱን ነገረችው። “ቢሆንም እንዳይሰማኝ እየጣርኩ ነው ። እርስዎ ያሉኝን ለማስታወስ እየሞከርኩ ነኝ ። ስላለፈው እየረሳሁ ፤ ለወደፊቱ እኖራለሁ ።”

“ልክ ነሽ ስለወደፊቱ ለመወያየት ነገ ወደለንደን እመጣለሁ ። እራት አብረን ብንበላስ?”

“እጅግ በጣም ደስ ይለኛል” አለች ካተሪን በጉጉት ። ስትመኘው የነበረ ነው ። ምን ያህል ባለውለታዋ እንደሆነ ለመናገር መልካም አጋጣሚ ነው ።

ኮንስታንቲን ዴሚሪስ የስልኩን እጀታ መልሶ ሲያስቀምጥ ፈገግ አለ ።

‘የቼዝ ጨዋታው እንግዲህ ተጀመረ’ ሲል ለእራሱ ተናገረ ።

በሪትዝ ሆቴል እራት በሉ ። የምግብ አዳራሹ ውብና ያማረ ሲሆን ምግቡም በጣም ጣፋጭ ነበር ። ካተሪን ግን ስለዚህ ሁሉ ደንታ ሳይኖራት፡ ትኩረቷ ፣ አሳቧና አድናቆቷ ከፊት ለፊት ከተቀመጠው ጋባዥ ላይ ነበር ። ብዙ ልትነግረው ያስበቻቸው ነገሮች ነበሩ ።

“ግሩም የቢሮ ሠራተኞች አሉዎት ።” አለችው ካተሪን ። “ዊምም አስደናቂ ፍጡር ነው ። ከዚህ በፊት እንዲህ ዓይነት ሰው አይቼ አላውቅም። ...”

ዴሚሪስ የምትናገረውን ነገር አላዳመጣትም ። እያጠናት ነው ። ምን ያህል ቆንጆና ተወዳጅ እንደነበረች አስታወሰ ። ‘እንዳስቸኩላት አያስፈልግም’ ሲል ዴሚሪስ በሀሳቡ ወሰነ ። ‘ጨዋታውን ቀስ እያልኩ እየተጫወትኩ በድል አድራጊነት እፈጽማለሁ ። ኖኤሌ ፣ ይህ ሁሉ የሚደረገው ለአንቺና ለፍቅረኛሽ ተብሎ ነው ።’

“ለንደን ብዙ ይቆያሉ ?” ስትል ካተሪን ጠየቀችው ።”

“ለአንድ ወይም ለሁለት ቀን ብቻ ። አንድ የማከናውነው ሥራ

አለኝ ሆ” በእውነት የሚያከናውነው ነገር አለውን? ይህንን ሁሉ በስልክ መጨረስ እንደሚችል ያውቃል ። ግን አመጣጡ ካተሪን የበለጠ እንድትቀርበውና ስሜቷ ለእርሱ ሙሉ በሙሉ ተገዥ እንዲሆን ዘመቻ ለ° ድረግ ነው ። ወደፊቷ ቀረብ አለ ። “ካተሪን በሳዑዲት ዓረብ የነዳጅ ነምችት ሥፍራዎች ስለሰራሁባቸው ጊዜያት አጫውቼሻለሁ ... ?” ብሎ ጠየቃት ።

ዴሚሪስ ካተሪንን በሚቀጥለውም ምሽት እራት ጋበዛት ።

“በቢሮው ውስጥ ምን ያህል ቀልጣፋ ሥራ እንደምታከናውኚ ኤቬሊን አጫውታኛለች ። የደሞዝ ጭማሪ ላደርግልሽ ነው ።”

“ከዚህ በፊትም ብዙ ውለታ ውለውልኝ የለ? ...” ካተሪን ጭማሪውን መቃወሟ ነበር ።

ዴሚሪስ ትኩር ብሎ የውስጥ ዓይኗን አየ ። “ምን ያህል ውለታ ዋይ ሰው ልሆን እንደምችል አታውቂም!”

ካተሪን በአነጋገሩ መልሳ አፈረች ።

‘ሰውዬው በቃ ደግ ነው ።’ አለች በአሳቧ ። ‘ሌላ ነገር ማሰብ አይገባኝም ።’

በሚቀጥለው ቀን ዴሚሪስ ወደግሪክ ለመመለስ ተነሳ ። “ካተሪን ፣ ወደ አውሮፕላን ማረፊያ አብረን ብንሄድስ?”

“እሺ”

ደስ የሚልና ልብ የሚመስጥ ሰው ሆኖ አግኝታዋለች ። አስደናቂና ብልህ ከመሆኑ ሌላ እንደሚያስብላት በመረዳቷም ተታልላለች ።

አውሮፕላን ማረፊያው እንደደረሱ ዴሚሪስ ለስለስ አድርጎ ጉንጯ ላይ ሳማት ።

“አብረን የበለጠ ጊዜ ብናሳልፍ ደስ ባለኝ ነበር ካተሪን” አላት ።

“እኔም እንዲሁ ። አመሰግናለሁ ኮስታ” ብላ መለሰች ።

እዚያው ቆማ አውሮፕላኑ መሬቱን እስኪለቅ ተመለከተች ‘ልዩ ሰው ነው’ አለች በአሳቧ ። ‘ከሱ ተለይቶ መኖር ይከብዳል ።’



# ምዕራፍ ስድስት

ኮንስታንቲን ዴሚሪስና ቆርሳው ስፒሮስ ላምብሩ በመወዳጀታቸው ያልተደነቀ ሰው የለም ።

ስፒሮስ ላምብሩ ልክ እንደ ዴሚሪስ በጣም ሀብታምና ተሰሚነት ያለው ሰው ነው ። ዴሚሪስ በዓለም ላይ ትልቅ የሆነው የዕቃ ማጓጓዣ መርከብ ባለቤት ሲሆን የላምብሩ የዕቃ ማጓጓዣ መርከብ ከዴሚሪስ በመጠኑ አነስ ያለ ነው ። ኮንስታንቲን ዴሚሪስ የተለያዩ በርካታ የጋዜጦች ማሳተሚያና የአየር መንገድ ድርጅቶች ፣ የነዳጅ ማውጫ ሥፍራዎች ፣ የብረት ፋብሪካዎችና የወርቅ ማዕድናትም ባለቤት ነው ። ስፒሮስ ላምብሩም የኢንሹራንስ ኩባንያዎች ፣ የባንኮች ፣ የበርካታ ኢንዱስትሪዎችና የኬሚካል ማምረቻ ተቋሞች ባለቤት ነው ። ሁለቱም ወዳጅ የሚመስሉ ተፎካካሪዎች ሲሆኑ ከዚህ በይበልጥ ደግሞ የቅርብ ባደኞችም ሆነዋል ።

“ነገሩ አያስደንቅም?” ይላሉ ብዙ ሰዎች ። “በዓለም ውስጥ ያሉ ሁለቱ ታላላቅ ሰዎች ወዳጆች ሲሆኑ ።” ላይ ላዩን ላላየ ግን ሁለቱም የመጨረሻ ጠላቶች ናቸው ። አንዱ ሌላኛውን ይንቃል ። ስፒሮስ ላምብሩ 100 ጫማ ርዝመት ባለው የመንሸራሸሪያ ጀልባ የተኩራ እንደሆን ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ደግሞ ወዲያውኑ 150 ጫማ ርዝመት ያለው ፣ በውስጡ የመዋኛ ስፍራ ኖሮት 13 ሠራተኞች የሚሰሩበትና ሁለት ትናንሽ ፈጣን ጀልባዎችን የተሸከመ ባለ አራት ሞተር ተመሳሳይ መርከብ ይገዛል ።

የስፒሮስ ላምብሩ የዕቃ መጫኛ መርከቦች ቁጥር 12 ደርሶ የዕቃ መጫን አቅማቸውም ወደ 200,000 ቶን ከፍ ሲል ኮንስታንቲን ዴሚሪስ ደግሞ ያሉትን የጭነት መርከቦች ቁጥር ወደ 23 አሳደጓል ። እነዚህም መርከቦች የሚይዙት 650,000 ዕቃ ነበር ። ስፒሮስ ላምብሩ ለውድድር የሚሆኑ ፈረሶች እንደገዛ ዴሚሪስም የበለጠ ፈጣን ጋላቢ የሆኑ ፈረሶችን